ሁሉ ጊዜ ማባከን ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም፣ ተግባቦት መናገር ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ሰው መልእክቱን ሌላው በሚረዳበት መንገድ **የሚያቀርብበት** ነው::

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ይህንን እውነት ስለማይረዱ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው አብዛኛው ነገር ጊዜ ማባከን ሆኖ ይገኛል:: ለምሳሌ፣ መዘምራን ቢዘምሩና ነገር ግን የሙዚቃው ድምጽ በጣም ከፍ በማለቱ ምክንያት ምን እየተናገሩ እንደ ሆነ ሕዝቡ ባይሰማቸው፣ መግባባት እየተፈጠረ ነው ማለት አይቻልም:: ሕዝቡ የመዝሙሩን ፍች ላያገኝ ይችላልና:: አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች አማርኛ በማይናገሩባቸው የገጠር አካባቢዎች መዘምራን የአማርኛ መዝሙር ሊዘምሩ ይችላሉ:: መዘምራኑ ይህንን በማድረጋቸው መግባባትን ፈጥረናል ብለው ሊያስቡ ቢችሉም፣ ሰዎች የአማርኛ ቃላት ስለማይሰሙ፣ መግባባት አይቻልም:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሕዝባዊ አምልኮ ላይ የማይተረጎሙ ልሳናትን መናገር ተገቢ እንዳልሆነ ይናገራል:: ለዚህም ምክንያቱ መግባባት ሊፈጠር ስለማይችል ነው:: በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ከአእምሮአቸው ውስጥ የሚቀር መረጃ ሊያገኙ አይችሉም:: ይህ ማንም የማይረዳውን ድምጽ እንደሚሰጥ መለከት መሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ. 14:6-12)::

ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊረዱ ከሚገባቸው እጅግ ጠቃሚ ነገሮች አንዱ አንድን ነገር በመናገራችን ብቻ መግባባት ላይፈጠር እንደሚችል ነው:: መግባባት ሊፈጠር የሚችለው የተነገረውን ነገር የሰሙት ሰዎች ሲረዱ ነው:: ነገር ግን ሰሚዎቹ የሚነገረውን ነገር ባለመስማታቸው፣ ቋንቋው ስለማይገባቸው፣ ንግግሩ አሰልቺ በመሆኑ፣ ወይም በባህሉ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን የአነጋገር መንገዶች (ለምሳሌ፣ ታሪኮች፣ ምሳሌዎች፣ ቀልዶች) ባለመጠቀሙ ምክንያት ሰሚዎቹ ጆሮ ባይሰጡ፣ ከቃላት መነገር በቀር የመልእክት ልውውጥ አልተደረገም:: **በተናጋሪው አእምሮ ውስጥ ያለው መረጃና በልቡ ውስጥ ያለው በሚት በአድማጩ ግንዛቤ እስካላገኘ ድረስ፣ መግባባት አልተካሄደም**::



22ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው መግባባት የሌለባቸውን ቃላት በመናገሩ ምክንያት የተከሰተውን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) መግባባት እንዳይካሄድ ያደረገው ችግር ምንድን ነበር?

እውነተኛ መግባባት ሊካሄድ የሚችለው የሚከተሉት ነገሮች ሲኖሩ ነው:-

1. በአእምሯችን ውስጥ ያለው ፍች ለምንናገራቸው ሰዎች በትክክል ሲተላለፍ:: አሳባችን አድማጩ ከተረዳው ውጭ ከሆነ፣ መግባባት አልተካሄደም ማለት ነው:: «ነገ እመጣለሁ!» ብልና፣ አድማጮቹ፣ «ዛሬ እመጣለሁ፣» እንዳልኩ አድርገው ቢገነዘቡ፣ ተናግሬአለሁ እንጂ መልእክቱን አላስተላለፍኩም:: «ኢየሱስ ይወዳችኋል፣» ብልና፣ እነርሱ ግን፣ «ኢየሱስ ጥሩ ነገር የሚሠሩትን ሰዎች ብቻ ይወዳል!» የሚል ግንዛቤ ቢወስዱ፣ መልእክቴን አላስተላለፍኩም ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ሰዎች በአእምሯችን ውስጥ ያለውን ፍች እንዲወስዱ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለብን::

2. በድርጊታችን የምናስተላልፈው መልእክት የአፋችንን ቃል ማጠናከር አለበት:: መልእክትን የምናስተላልፈው በአፋችን ብቻ ሳይሆን፣ በድርጊታችንና ከፊታችን ላይ በሚታዩ ምልክቶች ጭምር ነው:: እንዲያውም፣ ምሁራን እንደሚሉት፣ አብዛኛው መልእክት የሚተላለፈው ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ነው:: በአፋችንና በድርጊታችን የምናስተላልፋቸው መልእክቶች ካልተጣጣሙ፣ ሰዎች ከቃላችን ይልቅ «ድርጊታችንን» ወደ መስማቱ ያዘነብላሉ:: ለምሳሌ፣ «ኢየሱስ ቅዱሳን እንድትሆኑና ከጋብቻ ውጭ ወሲብ እንዳትፈጽሙ ይፈልጋል፣» ብንልና ነገር ግን ሰሚዎቹ ከጋብቻ ውጭ ወሲብ እንደምንፈጽም ቢያውቁ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ የግንኙነት ችግር ካለብን ሰው ጋር እየተነጋገርን ነው እንበል:: ግለሰቡን ላለማየት ስንል ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንመለከታለን:: ይህም ድርጊት እውነት እየተናገርን አለመሆናችንን ሊያሳይ ይችላል:: አንድ ሰው ከእኛ ጋር ቢነጋገርና እኛ ግን መሬት መሬት ብናይ ወይም በመስኮት ወደ ውጭ ብንመለከት፣ ድርጊታችን የሚያሳየው ለመስማት

አለመፈለጋችንን ነው። ከማያምኑ ሰዎች ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ ኃጢአተኞች ቢሆኑም እንኳን ኢየሱስ እንደሚቀበላቸው ብንናገርና፣ ነገር ግን በድርጊታችን ሌላ መልእክት ብናስተላልፍ (ለምሳሌ፣ አንድ ለማኝ ወይም ሴተኛ አዳሪ ቢያጋጥሙንና ሰላምታ ለመስጠት ባንፈልግ)፣ ሰዎቹ ኢየሱስ ጥሩ የሆኑትን ሰዎች፣ ልብስና ገንዘብ ያላቸውን ብቻ ይቀበላል የሚል አሳብ ይኖራቸዋል። ኢየሱስ ይወዳችኋል የሚለውን መልእክት «ሊሰሙ» አይችሉም ማለት ነው።

የመግባባት ክህሎት እንዲኖረን ከተፈለገ፣ ቃላችንን የሚሰሙ ሰዎች ለማስተላለፍ የምንፈልገውን መልእክት መረዳታቸውን እንዴት እንደምናረጋግጥ ማሰብ አለብን። ይህንን እውን ለማድረግ ሰዎቹ የሚረዷቸውን ቃላትና አገላለጾች እንጠቀማለን። የምናናግራቸው ሰዎች አማርኛ የማይችሉ ከሆነ፣ ቀላል አማርኛን መናገር ወይም አስተርጓሚ መጠቀም አለብን። ድርጊታችንም ለማስተላለፍ ከምንፈልገው መልእክት ጋር መስማማት አለበት። አንድ ነገር አስፈላጊ ነው ብለን ካሰብን፣ ይህንኑ ተረድተው በጽሞና እንዲያዳምጡት በሚያስችል መንገድ መናገር አለብን። ለዚህም ከሚረዱን ነገሮች አንዱ የዓይን ለዓይን እይታ መኖሩ ነው፦ ነገር በዓይን ይገባል እንዲሉ። ጥሩ ተናጋሪዎችን በምንመለከትበት ጊዜ፣ ሁልጊዜም ሰዎች እንዲያደምጧቸው ለማድረግ ቃሎቻቸውንና እንቅስቃሴያቸውን ያዛምዳሉ።

3. የሚሰማንን ስሜት ወደ አድማጮቻችን በማስተላለፍ እነርሱም ስሜታችንን እንዲጋሩ ማድረግ። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠው ራእይ አስደስቶናል? እንዲህ ከሆነ፣ መልእክቱን አስተላለፍን የሚባለው ሰዎቹም በዚሁ ራእይ ምክንያት እንዲደሰቱ ለማድረግ ስንችል ብቻ ነው። ሰዎች በፈቃደኝነት የሚፈጽሙት ኃጢአት ያሳዝነናል? እንዲህ ከሆነ፣ መልእክቱን አስተላለፍን ማለት የሚቻለው እነርሱም በኃጢአታቸው ምክንያት ኀዘን እንዲሰማቸው ስናደርግ ነው። የተግባቦት ክህሎት እንዲኖረን ከተፈለገ፣ ሰዎች ስሜታችን እንዲሰማቸው አድርገን ራሳችንን መግለጽ አለብን። ምንም ዓይነት



ስሜት በሌለበት መንገድ የሚናገር ሰው ሰዎች በደስታ እንዲነሣሡ ወይም ክርስቶስን ለመከተል እንዲወስኑ ሊያደርግ አይችልም። ስሜትን ከእኛ ዘንድ አለማየታቸው የምንናገረው ነገር ብዙም አስፈላጊ አይደለም ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።

4. በመጨረሻም፣ ውጤታማ ተግባቦት ሊኖር የሚችለው ለማድረግ የምንፈልገውና በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚከሰተው ነገር አንድ ዓይነት ሲሆን ብቻ ነው። አንድ ቀን ሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራ መንገድ ላይ አንድ ሰው ፈወሱ። በዚህ ጊዜ እነርሱ ያሰቡት የክርስቶስን የፈውስ ኃይል ለሰዎች እንደሚያሳዩ ነበር። ሰዎቹ ግን እነ ጳውሎስን መላእክት አድርገው ቆጠሯቸው። ጳውሎስና በርናባስ ይህንን ባወቁ ጊዜ፣ እነርሱ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንጂ በሰው አምሳል የተገለጹ አማልክት አለመሆናቸውን አስረግጠው ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሊሰግድላቸው ተዘጋጅቶ የነበረው ሕዝብ ሊወግራቸው ድንጋይ አነሣ (የሐዋ. 14:8-20)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በመሠራቱ በጣም ተደስተው ከሆነና፣ ምእመናን ግን ካልተደሰቱ፣ መግባባት አልተፈጠረም ማለት ነው። ወይም ደግሞ አንድ ወንጌላዊ አንድ ሰው በክርስቶስ እንዲያምን ጥረት የሚያደርግ ከሆነና፣ ግለሰቡ ግን ከእርሱ የሚጠበቀው መጠጥ አለመጠጣት፣ እጆቹን ማንሣትና የተወሰኑ ቃላትን ማነብነብ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ መግባባት አልተቻለም ማለት ነው። የተግባቦት ግቡ ግለሰቡ የምንናገረውን ነገር መስማቱ ብቻ አይደለም። የውጤታማ ተግባቦት ግብ በተወሰነ መንገድ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ ማምጣት ነው። ይህ ካልሆነ፣ የምንሞክረው ነገር ከንቱ ቃላትን ማነብነብ ብቻ ይሆናል።

ቃላት እንደ መሪዎች የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ፣ ስሜታቸውን ለማነሣሣትና አኗኗራቸውን ለመቀየር የምንጠቀምባቸው «መሣሪያዎች» ናቸው። በመሆኑም፣ በአግባቡ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

(ማስታወሻ፦ የተግባቦትን ክህሎት መማር እንደ ሌሎች ማናቸውም ክህሎቶች ጥናትንና ልምምድን ይጠይቃል። ጥሩ ተ

ግባቦት (በተለይም በስብከትና በማስተማር በኩል) ለቤተ ክርስቲያን ወሳኝ ስለሆነ፣ ክህሎትን በተሳበሰ መንገድ መልእክትን ለማስተ ሳለፍ የሚያስችል ዕድል ከገጠመህ ተጠቀምበት:: ከሁሉም በላይ ግን፣ ከፍተኛ የተግባቦት ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ተመልከት:: «የዚህን ግለሰብ ተግባቦት ውጤታማ ያደረገው ምንድን ነው?» ብለህ ራስህን ጠይቅ:: የሰዎችን ቀልብ ለመያዝ ጥሩ መግቢያ ወሳኝ ስለሆነ፣ እንዴት ንግግራቸውን እንደሚጀምሩ አስተውለህ ተ መልከት:: ሰዎች ከሰሙት ነገር ውስጥ ምሳሌዎችን ሊያስታውሱና በእነርሱም ምክንያት የተላለፈውን መልእክት ሊገነዘቡ ስለሚችሉ፣ መልእክታቸውን እንዴት በምሳሌዎች እንደሚያዋዙ አጢን:: አድማጮች የሚነገረውን አሳብ በግልጽ ለመከታተል ይችሉ ዘንድ እንዴት የአሳብ ሂደቱ ጥርት ብሎ እንደሚወርድ አስተውል:: ንግግራቸውን እንዴት እንደሚያበቁም ልብ ብለህ አስተውል:: ጥሩ ማጠቃለያ ቀደም ሲል የተላለፈውን መልእክት ከመደምደሙም በላይ፣ አድማጮቹ ምላሽ እንዲሰጡ ይጋብዛል:: ከዚያም ስታስተ ምር፣ ስትሰብክ ወይም ማስታወቂያ ስትናገር እነዚህን ነገሮች ለመጠቀም ሞክር::)

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው አንድ ነገር ሲናገር አድማጮቹ ሌላ ግንዛቤ ያገኙበትን ሁኔታ ግለጽ:: ይህ በንግግርና መግባባት መካከል ስላለው ልዩነት ምን ያሳየናል? ለ) አንድ ሰው አንድ ዓይነት ስሜት ለመፍጠር ሲሞክር፣ ሰዎቹ መልእክቱን ባለመረዳታቸው ሌላ ዓይነት ምላሽ የሰጡበትን ሁኔታ ግለጽ:: |

የቤተ ክርስቲያን መሪ ሰዎች በአእምሮው ውስጥ ያለውን አሳብና ስሜት መረዳታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል:: ነገሮች በመድበስበሳቸው ምክንያት ሰዎች በተናጋሪው አእምሮ ውስጥ ያለውን አሳብ ለመገመት ከተገደዱ፣ ንግግሩ አሰልቺ በመሆኑ ምክንያት በደስታ ለመስማትና ውሳኔ ለመስጠት ካልቻሉ፣ መግባባት አልተቻለም ማለት ነው:: ያቀረብነው ስብከት፣ የተናገርነው ማስታወቂያ ወይም የሰጠነው የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ሰዎች እንዲሰላቹና ምንም ዓይነት ምላሽ እንዳይሰጡ የሚያደርግ ከሆነ፣ ተግባቦት አልተካሄደም ማለት ነው:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጥረታችንም ሆነ የሕዝቡ ጊዜ ባክኗል ማለት ነው:: ማስታወቂያ



ስንናገር ወይም ስንሰብክ እነዚህ አራት የተግባቦት መመዘኛዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የተከሰተውን ሁኔታ ማጤን አለብን::

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ:- ሀ) እነዚህን አራት የተግባቦት መመዘኛዎች በመጠቀም፣ ባለፈው ሳምንት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተሰጡትን ማስታወቂያ ዎች ገምግም:: ተግባቦት ነበር ወይስ ንግግር ብቻ? መልስህን አብራራ:: ለ) ቀደም ሲል የሰማሃቸውን ሦስት ስብከቶች አስታውስ:: 1) ብዙም ተ ግባቦት ያልታየበት ስብከት የትኛው ነበር? ምክንያቶችህን አብራራ:: 2) በክህሎት የተሞላ ተግባቦት የታየበት የትኛው ነበር? መልስህን አብራራ:: 3) አንደኛው ከሌላኛው በላይ ለምን እንዳስደሰተህ ለመመልከት ሦስቱን ስብከቶች አነጻጽር:: ከዚህ ክህሎት ስላለበት ተግባቦት ምን እንማራለን? 4) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የታወቀ የተግባቦት ችሎታ ያለው ማን ነው? የእርሱ ተግባቦት ከሌሎች የሚሻለው ለምንድን ነው? ክህሎት ያለው የተግባቦት ባለ ሙያ ስለ መሆን ይህ ምን ያስተምርሃል? |

## ብዙ የተግባቦት ጥረቶች የሚመክኑበት ምክንያት

በተግባቦት ውስጥ አብዛኞቹ ችግሮች የሚከሰቱት በተናጋሪው እአምሮ ውስጥ ያለውን ነገር አድማጮቹ ሳይረዱ በሚቀሩበት ጊዜ ነው:: ይህ ችግር የሚፈጠረው ከተናጋሪው ወይም ከአድማጩ ሊሆን ይችላል::

### *1. ተናጋሪው* በግልጽ ባለመናገሩ ምክንያት የሚፈጠር የተ ግባቦት ችግር::

አንድ ሰው የሚያስተላልፈውን መልእክት ሰዎች እንዳይረዱ የሚያግዱ አያሌ ጥፋቶች ሊፈጽም ይችላል:: ከእነዚህም መካከል አድማጮቹ በማይሰሙት ቋንቋ መናገር፣ እነርሱ የማያውቋቸውን ቃላት መጠቀም፣ ቃላትን እድማጮቹ ከሚያውቁት በተለየ አገባብ መጠቀም፣ አሳቡን በደንብ አለመግለጽ፣ ወይም አድማጮቹ የቃላቱ መሠረት የሆኑትን ሁኔታ አለማወቃቸው መግባባት እንዳይኖር ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው::

በቀዳሚነት በእርሱ በኩል ተግባቦቱ በትክክል መካሄዱን ማ ረጋገጥ የተናጋሪው (ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች) ኃላፊነት ነው:: አሳቦቹን ወደ ሌሎቹ ለማስተላለፍ የሚፈልገው እርሱ

በመሆኑ፣ ቃላቱና ቃላቱን የሚገልጽባቸው መንገዶች አድማጮቹ አሳቡን እንዲረዱ የሚያግዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ማስታወቂያ እንደ መናገርና የመሪዎችን ውሳኔዎች እንደ ማሳወቅ ካሉት ቀላል ነገሮች አንሥቶ፣ እንደ ስብከት ወይም ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ራእይ እንዲጨብጡ ለማድረግ እስከሚቀርቡ ውስብስብ ንግግሮች፣ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በክህሎት መልእክታቸውን ለማስተላለፍ ይጥራሉ። ሰዎች መልእክቱን ተረድተው እንዲለወጡ ለማስቻል የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥሩ ሁኔታ መልእክታቸውን ባለማስተላለፍ የራሳቸውንና የሚሰሟቸውን ሰዎች ጊዜ ለማባከን አይፈልጉም።

ክህሎት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ የተግባቦት መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ. ሰዎቹ የማያውቁትን እውነት ከማብራራታቸው በፊት ከሚታወቁ አሳቦች መጀመር። ብዙ ተናጋሪዎች ሰዎች ነገሮችን የሚረዱት ከሚያውቁት ጀምረን ወደማያውቁት ስንወስዳቸው የመሆኑን እውነት ይዘነጋሉ። አንዳንድ የተማሩ ሰዎች ሕዝቡ በሚረዳው መንገድ ለማቅረብ ስለማይችሉ፣ በገጠር አካባቢዎች ጥሩ ስብከት ለማቅረብ ይቸገራሉ። እነርሱ ስለ አውሮፕላን ይናገራሉ። ነገር ግን አድማጮቹ አውሮፕላን አያውቁም። ወይም ደግሞ ማንም ሰው በማይረዳው መንገድ ስለ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ያወራሉ። ብዙ የሥልጠና ፕሮግራሞች ስኬታማ የማይሆኑት ተናጋሪዎቹ እውነቶችን አድማጮቹ በሚረዱበት መንገድ ስለማይናገሩ ነው። ስለሆነም፣ በምንናገርበት ጊዜ፣ አድማጮቻችን የሚኖሩበትን ሁኔታ (ቃላቸው ምን እንደሚመስል) እና ከዚህ በፊት ምን እውነት እንደሚያውቁ፣ እንዲሁም የትምህርት ደረጃቸው ምን ያህል እንደ ሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ተናጋሪው ይህንን በሚረዳበት ጊዜ፣ ሕዝቡ የሚሰሙትን ዓይነት መልእክት ለማቅረብ አይቸገርም። ሰዎቹ ከሚያውቁት ይነሣና አዲሱን አሳብ ለማብራራት ቀደም ሲል የሚታወቀውን አሳብ ይጠቀማል። ምሳሌዎችን የሚጠቀመው



ከእነርሱ ሕይወት እንጂ ከራሱ አይሆንም። የሚፈልጋቸውን ነገሮች ከእነርሱ የመረዳት ችሎታ ጋር ያቻችለዋል።

ለ. ክህሎት ያላቸው ተግባቢዎች ታሪኮችን፣ ምሳሌዎችን፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. . . ይጠቀማሉ። የተግባቦት ምሁራን ካረጋገጧቸው ነገሮች አንዱ በዓለም ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች አብዛኞቹ በታሪኮች አማካኝነት እውነትን በጥሩ ሁኔታ እንደሚማሩ ነው። ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ሰዎች ግን እውነትን በቀጥታ ለመስማት ይመርጣሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ሰዎች ግን ቀጥተኛ ንግግሮችን ለመቀበል ያልተዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እውነቶችን የሚለዋወጡት በታሪኮች አማካኝነት ነው። ስለሆነም፣ አገልጋይ አግባቢዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ሰዎች ለመረዳት በሚቀልላቸው መንገድ እውነትን ማቅረብ ይኖርብናል። ይህ ማለት ደግሞ ብዙውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ለማስተማር ታሪኮችን መጠቀምን ይጠይቃል። ታሪኮች በምሳሌነት በሚሰጡበት ጊዜ፣ ሰዎች ራሳቸውን ከታሪኩ ገጸ ባሕርያት ጋር ስለሚያመሳስሉ፣ ተጨማሪ ጥቅም አላቸው። በመሆኑም፣ በታሪኩ አማካኝነት እውነቱ እንዴት ከሕይወታቸው ጋር እንደሚዛመድ የተሻለ ግንዛቤ ያገኛሉ፡ በተጨማሪም፣ ታሪኮች ከተራ ንግግር በበለጠ የአድማጭን ስሜት የመቀስቀስ ብቃት አላቸው። ስለ አንድ ሰው ታሪክ በምንሰማበት ጊዜ፣ እኛም የታሪኩ አካል እንሆናለን። በታሪኩ ውስጥ ባለው ገጸ ባሕርይ ላይ ክፉ ነገር ከደረሰበት፣ እናዝንለታለን። እግዚአብሔር አንድ ታላቅ ነገር ካደረገለት፣ በደስታችን ከባለ ታሪኩ ጋር እንካፈላለን። አብዛኞቹ ክህሎት ያላቸው ተግባቢዎች ታሪክ ነጋሪዎች ናቸው።

ሐ. ክህሎት ያላቸው ተግባቢዎች ሰዎች የሚነገረውን ነገር መስማታቸው ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነ መረዳታቸውን ያረጋግጣሉ። ብዙ የስብከትና የትምህርት ጥረቶች የሚመክኑት ሰዎች ትምህርት በምን በኩል ከእነርሱ ሕይወት ጋር እንደሚዛመድ ስለማያውቁ ነው። የአዋቂዎች የትምህርት ምሁራን እንደሚሉት፣ አዋቂዎች አንድን ነገር በጽሞና የሚሰሙት ይጠቅመናል ብለው ሲያስቡ ብቻ ነው። ከሕይወታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌ

ሰውን ንድፈ-አሳባዊ መረጃ ለመስማት ይቸገራሉ:: ስለሆነም፣ መምህራን ስለ ራእይ መግለጫዎች ቢያስተምሩና የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ የራእይ መግለጫዎች አመራራቸውን እንዴት ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ ካሳወቁ፣ ከሕይወቴ ጋር አዛምደዋለሁ የሚል ግብ ይዘው አያዳምጡም ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ስንሰብክና ስናስተምር እውነቱ በምን መንገድ እንደሚጠቅማቸው መረዳታቸውን ማረጋገጥ አለብን::

> 25ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰሰምትወደው ሰባኪ አስብ:: አድማጮቹ መልእክቱን እንዲረዱና እንዲወዱት ሰማድረግ የሚጠቀምባቸው የውጤታማ ተግባቦት መሣሪያዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ባለፈው ዓመት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ሲሰብክ ስለ ሰማኸው እጅግ ደካማ ሰባኪ አስብ:: መልእክቱን በሚገባ እንዳያስተላልፍ ያደረገው ነገር ምን ነበር?

2. ችግሩ ያለው *ከአድማጩ* ሊሆን ይችላል::

አንድ ሰው የሚተላለፈውን መልእክት ሰምቶ ምላሽ እንዳይሰጥ የሚከላከሉ አያሌ ነገሮች አሉ:: ምናልባትም አድማጭ ለተናጋሪው አሳብ ጆሮውን አላዋሰም ይሆናል:: ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ባለማግኘቱ፣ ቀልቡን ሰብስቦ ለማዳመጥ አቅም አጥሮት ይሆናል:: ምናልባትም የተናጋሪውን የልብ ዝንባሌ እየመረመረ ተናጋሪው ያሳሰበውን ነገር በማውጠንጠን ላይ ይሆናል:: ምናልባትም ስለ ሌላ ጉዳይ እያሰበ ይሆናል:: (ሚስቱ ስለ ታመመችበት፣ ተጨንቆ ሊሆን ይችላል::) ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ልጆች አሳቡን በትነውበት ይሆናል:: ወይም ደግሞ ስብከቱ በጣም ረዥም በመሆኑ፣ አእምሮው መከታተል ተስኖት ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም፣ ሰዎች የተናጋሪውን አሳብ እንዳያዳምጡ የሚከላከሉ የተለያዩ ነገሮች እንዳሉ መገንዘቡ ተገቢ ነው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች መልእክታቸውን እንዲያዳምጡ ሊያስገድዱ ባይችሉም፣ ሰዎች በተቻላቸው መጠን እንዲያዳምጡ ማድረጉ የመሪው ኃላፊነት ነው:: ምናልባትም ከድካማቸው የተነሣ መልእክቱን ለመከታተል የማይችሉትን ሰዎች ለመርዳት አንችልም ይሆናል:: ነገር ግን ሰዎች ሰምተው እንዲረዱና እንዲለወጡ ለማገዝ ልናደርጋቸው የምንችላቸው አያሌ



ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ ሰዎች መሰላቸታቸውን ወይም ለረዥም ጊዜ በትኩረት ለማዳመጥ አለመቻላቸውን በምንገነዘብበት ጊዜ፣ ክህሎት ያለን ተግባቢዎች ከሆንን፣ ብዙ ሰዓት ከመውሰድ ይልቅ፣ እውነትን ቶሎ ቶሎ ብለን በመናገር እንጨርሳለን:: ብዙ ስብከቶች በጣም ረዥም በመሆናቸው፣ ሰዎች የሚነገረውን ሲያዳምጡ ለመቆየት አይችሉም:: በመሆኑም፣ ከንቱ የጊዜ ማባከኛዎች ይሆናሉ:: ተናጋሪው መናገሩን ቢቀጥልም አድማጮቹ ሰዎች ማይሰሙት፣ ቃላቱና የመግባቢያ ዘዴዎቹ ሁሉ ከንቱ ሆነዋል ማለት ነው:: ተናጋሪው ሰዎች ቀልባቸውን በንግግሩ ላይ ለማቆየት ባለመቻላቸው ምክንያት ሲቅበጠበጡ ከተመለከተ፣ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ የሆነ ነገር ማድረግ አለበት:: ይህም ታሪክ ወይም ቀልድ መናገርን፣ ስብከቱን ቆም አድርጎ መዝሙር ማዘመርን ሊጨምር ይችላል:: ይህ ደግሞ ሰዎች እንደገና መልእክቱን ለማዳመጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል:: በተጨማሪም፣ ተናጋሪው በስሜትና ደስ በሚያሰኝ መንገድ መናገር እንጂ አሰልቺ የሆነ ዲስኩር ማሰማት የለበትም:: ወይም ደግሞ ከፍሉ ሞቃት በመሆኑ ምክንያት ሰዎች እንቅልፍ ቢተኙ፣ በቂ አየር እንዲገባ ለማስቻል መስኮቶችን መክፈት ያስፈልጋል:: ልጆች ወዲያ ወዲህ በማለታቸውና በማልቀሳቸው፣ ወይም የሰዎች ገባ ወጣ ማለታቸው ስብከቱን የሚሰሙትን ሰዎች ትኩረት ሊሰርቅ ስለሚችል፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዲሆኑ ወይም የልጆች የሰንበት ትምህርት ቤት እንዲዘጋጅ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ወይም ደግሞ ስብከቱ ሳይጠናቀቀቅ ወደ አዳራሹ መግባትም ሆነ መውጣት የተከለከለ መሆኑን ማሳወቅ ይቻላል:: የቋንቋ ችግር ካለ፣ አስተርጓሚ በመጠቀም የሚተላለፈው መልእክት በአግባቡ ወደ ሰዎች እንዲዳረስ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል::

የመለወጡ ኃላፊነት ሰዎች መልእክቱን እንዲረዱ በመፈለግ መልእክቱን የሚያስተላልፉት ሰዎች መሆኑን አትዘንጋ:: አድማጩ እኛን ለመረዳት እንዲችል ይሰወጣል ብለን መጠበቅ የለብንም:: «አገልጋይ» መሪ ሁልጊዜም ለሌሎች ሲል ይለወጣል እንጂ እነርሱ ለእኔ ብለው ይለወጣሉ በማለት አይጠብቅም:: «የገባው ይግባው:: ካልገባው ደግሞ የራሱ ችግር ነው!» ማለት የአገልጋይ መሪ አስተ

ሳሰብ ሊሆን አይችልም:: አይደለም! ምእመናን ካልገባቸው ችግሩ የራሳቸው ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነው:: አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሁልጊዜም፣ «ሰዎች በተሻለ መንገድ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ፣ እንዲረዱና እንዲለወጡ ምን ሳድርግ?» ከማለት ወደ ኋላ አይልም::

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ መልእክት አያስተላለፍክ ነኝ ብለህ ስታሰብ፣ ሌሎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱበትን ሁኔታ ጥቀስ:: ለ) በዚሀ ጊዜ ጥፋቱ የማን ነበር? የተናጋሪው ወይስ የአድማጮቹ? መልስህን አብራራ:: |

**ክህሎት ያለው ተግባቢ የተግባቦት ጥረቱን ከሁለቱም ወገን ይመረምራል:: ሰዎች ይረዱልኛል ብሎ በሚያስበው መንገድ መልእክቱን ያስተላልፋል:: አድማጩ ሰምቶ ተግባራዊ እርምጃ እንዳይወስድ ያደናቅፋሉ የሚላቸውንም ነገሮች ያስወግዳል::**

## አራተኛ ቀን

## ክህሎትን የተሞላ መግባባት ሰዎች እኛን ለመስማት እንዲፈልጉ በሚያደርጉ መልካም ግንኙነቶች ይጀምራል::

የሁሉም ጥሩ ተግባቦቶች መሠረቱ ተግባቦቱን ከምናካሂድባቸው ወገኖች ጋር ጤናማ ግንኙነት ያለን መሆናችን ነው:: በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል መተማመን ከሌለ፣ የተግባቦት ሂደቱ በጣም አስቸጋሪ ነው:: መተማመን ከሌለ፣ የምንናገረውን በቀጥታ ለመስማት ይቸገራሉ:: ወይም ደግሞ የሚሰሙን እንዴት እንደሚቃወሙን እያሰቡ ይሆናል:: ወይም ደግሞ ከንግግራችን ኋላ ተደብቋል ብለው የሚያስቡትን ነገር ሊናገሩ ይችላሉ::

ነገር ግን በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል መከባበርና መተማመን ካለ፣ መግባባቱ ቀላል ይሆናል:: ሰዎች የምንናገረውን ነገር የምናውቅ መሆናችንን ካረጋገጡ (በጉዳዩ ላይ «ባለሙያ» ከሆንን)፣ ይሰሙናል:: ሰዎች እውነቱን ተግባራዊ ያላደረገን ሰው ትምህርት ይጠራጠራሉ:: ሁላችንም በትምህርት ቤት ስለ ወንጌል ስርጭት ከተማረ ሰው ይልቅ ለብዙ ዓመታት በክህሎት ወንጌል ሲሰብክ የኖረን ሰው ትምህርት ብናዳምጥ እንመርጣለን:: ወይም ደግሞ



በመንፈሳዊ ባሕርያችን ምክንያት ሊያከብሩንና ሊያዳምጡን ይፈልጋሉ:: ሁልጊዜም ነገሮችን ለእግዚአብሔር ክብር እንደምናደርግ ወይም ለሰዎች ፍቅር ብለን የምናደርግ መሆናችንን ካወቁ፣ ለምንናገረው ነገር ጆሮ ይሰጡናል::

በቅርቡ አንድ አማኝ ክርክር በሌለው ሁኔታ ከአንድ ሼህ ጋር እየተነጋገረ ነበር:: ከጥቂት ደቂቃዎች ንግግር በኋላ አማኙ ለሼሁ ስለ መሠረታዊ የወንጌል እውነታዎች ነገራቸው:: ሼሁም፣ «ከአንተ ጋር በመነጋገሬ ደስ ብሎኛል:: ከእኔ ጋር ተቀምጠህ እንደ ሰው ልታውቀኝ ትሞክራለህ:: ለመናገር ብቻ ሳይሆን ለመስማትም ፈቃደኛ ነህ:: በቤቴ አጠገብ ሲያልፉ ጮክ ብለው፣ "በኢየሱስ ካላመንክ ወደ ሲኦል ትወርዳለህ!" እያሉ እንደሚያስፈራሩኝ ሌሎች ጴንጤዎች አይደለህም:: እነርሱን እጠላቸዋለሁ:: አንተ ግን ወደ ቤቴ እየመጣህ በፈልግክ ጊዜ ሁሉ ስለ እምነትህ ልትነግረኝ ትችላለህ» አሉት:: ለውጡን ያመጣው ምንድን ነበር? ሼሁ በአንዳንድ አማኞች እየተበሳጩ፣ በዚህኛው አማኝ ደስተኛ የሆኑት ለምንድን ነበር? ይህ የሆነው አማኙ ከሼሁ ጋር የግል ግንኙነት ለመመሥረጥ ጥረት ስላደረገ ነበር:: ከሰዎች ጋር ግንኙነት በምንመሠርትበት ጊዜ፣ ለእነርሱ አንድ ነገር መናገር ብቻ ሳይሆን፣ ከእነርሱም ለመስማት ፈቃደኞች እንሆናለን::

ይህ ማለት ክህሎት ያለን ተግባቢዎች ለመሆን ከፈለግን፣ በምንናገረው ነገር ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጋር በመተሳሰብና ፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መመሥረትም አለብን ማለት ነው:: እነርሱን ለመረዳትና የሕይወታቸውን ደስታና ትግሎች ሁሉ ለመረዳት መጣር አለብን:: በሚገባ በመዘጋጀት ለማስተላለፍ የምንፈልጋቸውን እውነቶች ማወቅ አለብን:: እንዲሁም ደግሞ ሰዎች እንዲያከብሩንና ከእኛ ለመስማት ፈቃደኞች እንዲሆኑ መንፈሳዊ ባሕርይ ሊኖረን ይገባል:: ሰዎች ሲያምኑንና ሲያከብሩን ከውጤታማ ተግባቦት ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ተቀረፈ ማለት ነው::

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከሕይወትህ ምሳሌ በመጠቀም፣ ከአንድ ሰው ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌለህ መሆኑ ተግባቦትህን እንዴት እንደ ገደበው ግለጽ። ለ) ከአንድ ሰው ጋር ጥሩ ግንኙነት መመሥረትህ በቀላሉ ለመግባባት እንድትችል ያደረገበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) ለማያምን ሰው ወንጌል ለማካፈል ጥሩ ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

## ክህሎት ያለው ተግባቢነትና ውጤታማ እረኛነት የሚጀምረው ጥሩ አድማጭ ከመሆን ነው።

28ኛ ጥያቄ፡- ምሳሌ 1:5፤ 10:19፤ 17:28፤ 12:15፤ 18:13፤ 19:20፤ 13:3፤ 20:15፤ ማቴ. 12:36፤ ያዕ. 1:19ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ሁልጊዜም ተናጋሪ ሆኖ ከመታወቅ ይልቅ አድማጭ ስለ መሆን ምን ያስተምሩናል?

1. ክህሎት ያላቸው መሪዎች ስለ ራሳቸው ብዙ አይናገሩም።

አንድ ጊዜ አንድ ሰባኪ፣ «እግዚአብሔር ሁለት ጆሮዎችና አንድ አፍ የሰጠኝ ከምናገረው እጥፍ ጊዜ እንዳዳምጥ ነው» ብሎ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ከመናገር ይልቅ መስማትን ይደግፋል። ሰሎሞን እንደተናገረው፣ አንድ ሰው አዋቂ ባይሆን እንኳን፣ ብዙ ካልተናገረ፣ ሰዎች አዋቂ ነው ብለው ይገምታሉ። እንዲያውም ብዙ ነገሮችን ስንናገር፣ ኃጢአትን ልንናገር እንደምንችል በመግለጽ ያስጠነቅቀናል። ስለ ራሳችን በምንናገርበት ጊዜ ኩራታችንን እየገለጽን ነው ማለት ነው። ወይም ደግሞ ሰዎች እንዲያዳምጡን ለማድረግ ስንል ስለ ራሳችን አሳብ እንነግራቸዋለን። እንደ መሪዎች ስለ ራሳችን ብዙ በምንናገርበት ጊዜ አስተሳሰባችን፣ «እኔ እየተናገርኩ ነኝ። እናንተ ማዳመጥ አለባችሁ። እኔ አስፈላጊ ሰው ነኝ» የሚል ይሆናል። ክርስቶስ ለምንናገረው ቃል መልስ እንደምንሰጥ ገልጾአል። የምንናገራቸው ነገሮች ደግሞ የልባችንን ማንነት ያሳያሉ። ክርስቶስ ለመናገር የዘገየንና ለመስማት የፈጠንን እንድንሆን አስተምሮናል። መናገርን ከመማራችን በፊት መስማትን እንድንማር መንፈሳዊ ጥበብ ያስተምረናል።

2. መሪዎች በቀዳሚነት አገልጋይ መሪዎች መሆናቸውን የሚያሳዩት ሰዎችን በማዳመጥ ነው።



ቀደም ሲል በተማርነው ትምህርት ውስጥ እንደ ተመለከትነው፣ እግዚአብሔር መሪዎችን የጠራው አገልጋይ መሪ ዎች እንዲሆኑለት ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንድናገለግል እኛን የጠራበትን አሳብ መያዝ አለብን ማለት ነው። በባህላችን መሪዎች መሆናችንን ለማሳየት «መናገሩን» እንመርጣለን፡ ከዚህም የተነሣ፣ በስብሰባዎች ላይ ሁሉም ሰው ለመናገር ይሽቀዳደማል። ይህም የሚሆነው ካልተናገርኩ እንደ መሪ አልቆጠርም የሚል አስተሳሰብ ስላላቸው ነው። ዋናው የሆነ ነገር መናገራችን እንጂ የተናገርነው አሳብ አዲስ መሆን አለመሆኑ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመናገር ለመምራት እንፈልጋለን። የሽማግሌዎችን ውሳኔ የምናሳውቀው እሁድ ቀን ማስታወቂያ በመናገር ነው። ሌላም ሌላም . . .

ነገር ግን ብዙ የምንናገር ከሆነ፣ እምብዛም አናዳምጥም ማለት ነው። ካላዳመጥን ደግሞ፣ ሰዎችን እያገለገልን አይደለም። በዚህም ጊዜ አስፈላጊዎቹ እኛ ስለሆንን፣ እኛኑ ስሙን ከሚለው ዓለም የተ ለየን አንሆንም። ሰዎችን «ብናዳምጥ»፣ እያገለገልናቸው መሆናችንን ያውቃሉ። አገልጋይ መሪዎች መሆናችንን የሚለካው ሰ ዎችን በሰማንበት ልክ ነው።

29ኛ ጥያቄ፡- ፊልጵ. 2:1-4ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ አለበት ይላል? ለ) ይህ ከመሪዎችና ተግባቦት ጋር እንዴት የሚገናኝ ይመስልሃል? ሐ) መሪዎች ውሳኔ ሰጭዎችና እነዚህኑ ውሳኔዎች ወደ ሌሎች የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ሳይሆን ሰዎችን ለማዳመጣቸውና በመርዳታቸው የሚታወቁ ቢሆን፣ በቤተ ክርስቲያንና በሰዎች የመስማት ፈቃደኝነት ላይ ምን ዓይነት ለውጥ የሚከሰት ይመስልሃል?

3. የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መጠበቅ ከሚቻልባቸው ነገሮች አንዱ እርስ በርስ ለመደማመጥ መፍቀድ ነው።

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክት ውስጥ የምናገ ኘው ትልቁ ትምህርት ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን ለማየት መሻቱ ነው። ሁለት ሴቶች ጸብ ላይ ነበሩ። ምናልባት ሌ ሎች የቤተ ክርስቲያኒቱን አንድነት የሚፈታተኑ ችግሮች የነበሩ

ይመስላል። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን መጠበቅ ከባድ እንደ ሆነም ያውቅ ነበር። አንድነት የሚመጣው ሰዎች የራስ ወዳድነት ፍላጎቶቻቸውን ትተው ሌላው ከእኔ ይሻላል የሚል አቋም ሲይዙ ነው። አማኞች ሌሎችን «ለማገልገል» ብለው በፍቅር እርስ በርሳቸው በሚደማመጡበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ይመሠረታል። አገልጋይ መሪዎች እንደ መሆናቸው መጠን፣ ሽማግሌዎች ሌሎችን የማገልገል ኃላፊነት እንዳለብን ማወቅ አለባቸው። ይህ ማለት ከራሳችን በላይ ሌሎችን እናከብራለን ማለት ነው (ፊልጵ. 2:3)። ሌሎችን ማክበር ማለት እነርሱ እንዲያዳምጡንና እንዲረዱን እንደምንፈልግ ሁሉ፣ እኛም እነርሱን ለመስማትና ለመረዳት እንሞክራለን ማለት ነው።

4. አገልጋይ መሪዎች ውጤታማ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ሌሎችን ሲያዳምጡ ብቻ ነው።

አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ከቤተ ክርስቲያን ምእመናንና መሪዎች ጋር የሚደረጉትን ውይይቶች የሚያካትት ነው። አብረን ጥሩ ውይይቶች ለማካሄድ እንሞክራለን። ምእመናን የሚጋፈጧቸውን ችግሮች ተወጥተው ክርስቶስን በመምሰል እንዲያድጉ እንፈልጋለን። በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ውስጥ መሪዎች የየራሳቸውን አስተሳሰቦች ማከላቸው የማይቀር ነው። መሪዎች ካልተጠነቀቅን፣ ሌሎች ምን ቢያስቡ ወይም ቢናገሩ ከቁም ነገር ሳንቆጥር የራሳችንን አሳብ በሌሎች (በተለይ በተቀጠሩ ሠራተኞችና በምእመናን) ላይ ለመጫን ልንሞክር እንችላለን። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ግን ሰዎች ችግሮቻቸውን እንዲቀርፉና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምናደርግበትን ዕድል ያጠብበዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኞች መሆናቸውን ይናገራል (1ኛ ጴጥ. 5:1-3)። አብዛኛው የመሪዎች የእረኝነት አገልግሎት በሁለት ሁኔታዎች ላይ ያተኩራል።

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ስለ አሳሳቢ ጉዳዮች ለመወያየትና ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመስጠት ከሰዎች ጋር መገናኘትን ያካትታል። ሰዎችና አመለካከታቸው ስለሚለያይ፣ በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ



የአሳብ ልዩነት ይንጸባረቃል። እነዚህ የአሳብ ልዩነቶች በመንፈሳዊ መንገድ ካልተያዙ፣ ጸብን ሊጋብዙ ይችላሉ። ክፍፍል መፈጠር አለመፈጠሩ የሚወሰነው በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ከሰዎች ጋር ለመግባባት በምንወሰዳቸው እርምጃዎች ላይ ነው። ምርጥ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ከመናገራችን በፊት ስናዳምጥ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ሰዎች ይበልጥ ክርስቶስን እየመሰሉ እንዲሄዱ መምራት አለብን። አባሎቻችን እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ዓይነት ሰዎች ሆነው እንዲገኙልን እንፈልጋለን። ሰዎች እንዲያድጉ ለማድረግ ወይም ጸብ እንዲፈጥሩ በመገፋፋት የሰይጣን መሣሪያዎች ልንሆን የምንችለው ለሰዎች በምንሰጣቸው መልእክቶችና ማበረታቻዎች ነው። እንደ መሪዎች፣ መልሶችን ይዘን ለመምጣት ወይም ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማዘዝ እንፈተናለን። ይህ ግን እምብዛም አይረዳንም። የሰዎችን ችግሮች ልንረዳ የምንችለው ስናዳምጣቸው ነው።

የእግዚአብሔር ሥራ ወደፊት ይቀጥል ዘንድ አንድ መሪ እንዴት ማዳመጥና አሳቡን በግልጽ ማስተላለፍ ይኖርበታል። ይህ አስፈላጊ ከሚሆንባቸው ሁኔታዎች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡

ሀ. በኮሚቴና ቦርድ ስብሰባዎች ውስጥ የሚገኙ መሪዎች አንድን አገልግሎት የሚያካሂዱት በተለያዩ መንገዶች ሊሆን ይችላል። በመሆኑም፣ በግልጽ በመወያየት በእነርሱም ሆነ በምእመናን ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ምርጥ አሳብ መውሰድ ይኖርባቸዋል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ እርስ በርሳቸው በሚገባ ሲደማመጡና እግዚአብሔር በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ጠቃሚ አሳብ እንዲያገኙ ያስችላቸው ዘንድ ሲጸልዩ ነው።

ለ. አንድ ወንጌላዊ ሽማግሌዎች እንደማያከብሩትና እንደ ቅጥር ሠራተኛ እንደሚመለከቱት ያስባል። ይህም ትክክል እንዳልሆነ በመግለጽ ሽማግሌዎችን መውቀስ ይጀምራል። በዚህ ጊዜ የስሜት መጎዳቱ ሊፈወስና ሽማግሌዎች ከወንጌላዊው ጋር አብረው በመሥራት የእግዚአብሔር ሥራ እርሱን በሚያስከብር

መንገድ እንዲከናወን ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ሽማግሌዎቹ የወንጌላዊውን የተጎዳ ስሜት ለማዳመጥ ሲችሉ ብቻ ነው::

ሐ. ወጣቶች ሽማግሌዎች እንዲቆጣጠሯቸውና በፈለጉት መንገድ እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ እንዲያደርጓቸው አይፈልጉም:: ወጣቶች የሚፈልጉት አስደሳችና ስሜታዊነት የታከለበትን አምልኮ ነው:: ሽማግሌዎች ደግሞ ጠበቅ ያለ አምልኮ ያስደስታቸዋል:: በዚህ የፍላጎት መጣረስ ሳቢያ ጥላቻ ይጎለብታል:: አንዱ ሌላውን መንፈሳዊ አይደለም በማለት ይወቅሳል:: የሽማግሌዎቹ ስብሰባ ይህንን ችግር መፍታት እንዳለበት ያውቃል:: ችግሩን ለመፍታት የሚመለከታቸው ሁሉ (ወጣቶቹም ሽማግሌዎቹም) ተቀራርበው በግልጽ መወያየት አለባቸው:: ይህ በቦርድ ውሳኔ የሚፈታ ችግር አይደለም:: ሰላም ሊመጣ የሚችለው ሽማግሌዎቹ የወጣቶቹን አሳብ ካዳመጡና ወጣቶቹም የሽማግሌዎቹን አሳብ ካዳመጡ ብቻ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ሕጎችና ደንቦች ይወጣሉ:: መታወቅ ያለበት እንዲህ ዓይነት ነገሮች በሕግና ደንብ የማይፈቱ መሆናቸው ነው::

መ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልጅ ለመውሰድ ያልቻሉ ባለትዳሮች አሉ:: በዚህ ጊዜ ባል መካንነቱ የሚስቱ ችግር እንደ ሆነ ስላሰበ፣ እርሷን ፈትቶ ሌላ ሚስት ለማግባት ይፈልጋል:: ሽማግሌው ይህንን ችግር በጥንቃቄ ካልያዘው፣ ባል ተናድዶ የፈለገውን ሊያደርግ እንደሚችል ይገነዘባል:: ነገር ግን ባል ቀሪ ዘመኑን ከሚስቱ ጋር እንደሚያሳልፍ ለእግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ኪዳን ካፈረሰ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊዳከም እንደሚችል ይረዳል:: ስለሆነም፣ ሽማግሌው ወደ ባለ ትዳሮቹ ቤት በመሄድ ስለ ጉዳዩ በግልጽ ያወያያቸዋል:: ባለትዳሮቹ የሽማግሌውን ምክር መቀበል የሚጀምሩት (በአሳባቸው ባይስማማም) ችግራቸውን እንዳዳመጠ እርግጠኛ ሲሆኑ ብቻ ነው::



> 30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሽማግሌዎች ብዙውን ጊዜ የሚጋፈጧቸውንና ሰዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ የሚያግዙባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች ግለጽ:: ለ) ከላይ ለቀረቡት ሁኔታዎች መፍትሔዎችን ማምጣት የሚቻለው መሪው መናገር ከመጀመሩ በፊት ማዳመጥ ሲችል የሚሆንበትን መንገድ አብራራ::

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናንን በሚያዳምጡበት ጊዜ ምን ይከሰታል?

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰዎችን ጥልቅ ፍላጎቶችና አሳቦች በሚያዳምጡበት ጊዜ፣ ችግሮችንና የችግሮችን መፍትሔዎች ለመረዳት ይችላሉ:: ሰዎች ገመናቸውን ወዲያውኑ አይዘረግፉም:: ይህንን የሚያደርጉት የሚያዳምጣቸውን ሰው ሲያምኑትና ችግራቸውን ለመካፈል ፍላጎት እንዳለው ሲያረጋግጡ ብቻ ነው:: ማንኛውም ሐኪም ለበሽተኞች መድኃኒት የሚሰጠው ከበሽተኛው ጋር ከተነጋገረና በሽታው ምን እንደ ሆነ ካወቀ በኋላ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የምእመኖቻቸውን ጥልቅ ችግሮች ከመረዳታቸው በፊት የእግዚአብሔርን ቃል መድኃኒት አያዝዙላቸውም:: ምእመናን በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር ካልተናገሩና መሪዎች ምእመናኑ የሚያምኑት ነገር ምን እንደ ሆነና አስተምህሮአዊ ትክክለኛነቱም ምን ያህል እንደ ሆነ ለመረዳት አይችሉም:: ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል ትምህርት ሊያዘጋጁ የሚችሉት የሰዎችን «ድብቅ» ችግሮችና ጥያቄዎች ከተገነዘቡ በኋላ ነው::

ለ. ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደሚያዳምጧቸው በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ እነርሱም የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ የሚናገሩትን ለመስማት ፈቃደኞች ይሆናሉ:: መሪዎች የሰዎችን እመኔታ ሊያገኙ ከሚችሉባቸው ዐበይት መንገዶች አንዱ የሚናገሩትን ማዳመጥ ነው:: ምእመናን በመሪዎች ላይ እመኔታ በሚኖራቸው ጊዜ ደግሞ፣ መሪዎቹ የሚሰጧቸውን መንፈሳዊ ምክሮች ለመቀበል ይፈቅዳሉ::

ሐ. ሰዎች መሪዎች አመለካከታቸውን እንዳዳመጡ በሚረዱበት ጊዜ፣ መሪዎች የሚያቀርቡትን የተለየ አሳብ ለመስማት

ዝግጁዎች ይሆናሉ። ነገር ግን ሰዎች መሪዎች በጉዳዩ ላይ የነበራቸውን አመለካከት እንዳላዳመጡና መሪዎች በራስ ወዳድነት የሚፈልጉትን ለማሳካት እየተሯሯጡ ናቸው የሚል ግምት ካሳቸው፣ ከያዙት አሳብ ንቅንቅ ሳለማለትና መሪዎቹ የሚያቀርቡትን ምክንያት ሳለመቀበል ይቆርጣሉ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በትሕትና መጀመሪያ የእነርሱን አሳብ ከሰሙ፣ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በአጽንኦት የያዙትን አሳብ በመተው የመሪዎ ቻቸውን አሳብ ይቀበላሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ ወጣቶች አይሰሙንም፣ አይታዘዙንም ሲሉ ያማርራሉ። ምናልባትም እዚህ ላይ መሪዎች ወጣቶችን ለመረዳት መሞከር ይኖርባቸዋል። ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊረዷቸው የሚሞክሩ መሆናቸውን ካወቁ፣ መሪዎችን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ሰው አሳባችንን ለማዳመጥ ፈቃደኛ መሆኑን ካወቅን፣ መታዘዙ ቀላል ነው።

በመሆኑም፣ አገልጋይ መሪዎች መሆናችንን ከምናሳይባቸው ዐበይት መንገዶች አንዱ የራሳችንን አሳብ ለማስተላለፍ ከመጀመራችን በፊት የሰዎችን አሳብ ለማዳመጥ መፍቀዳችን ነው። ምእመናንን ለማወቅ ጊዜ ከሌለን፣ ወይም ምእመናን በልባቸው ውስጥ ያለውን አሳብ እንዲያካፍሉን ካላበረታታን፣ ይሰሙናል ብለን መጠበቅ የለብንም።

6. መሪዎች ሁለት ደረጃዎች ያሉትን ሂደት በመጠቀም ምእመናን የግል ችግሮቻቸውን እንዲፈቱና ክርስቶስን በመምሰል እንዲያድጉ ሊረዷቸው ይችላሉ።

መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ፣ ጥሩ ውሳኔ ዎችን እንዲሰጡና በእምነታቸው እንዲያድጉ ያግዝ ዘንድ አንድን መሪ የሚጠቀመው እንዴት ነው? ሰዎች ጥሩ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ፣ ለአለመግባባቶች መፍትሔዎችን እንዲያመጡ ወይም በእምነታቸው እንዲያድጉ የሚያድረጉ ክሁሎት ሁለት ደረጃዎች ባሉት ሂደት ላይ የተመሠረተ ነው፦



ሀ. ሰዎችን መርዳት የሚጀምረው አሳባቸውንና ስሜታቸውን ከመረዳት ነው። ይህም ግለሰቡ (ወይም ቡድኑ) የሚናገራቸውን ቃላትና በልቡ ውስጥ የተደበቁትን ነገሮች ማወቅን ይጨምራል። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ችግሮችን ለመፍታት እስተዋጽኦ አደርጋለሁ ብሎ በሚመጣበት ጊዜ መጀመሪያ ከግለሰቡ አይታ አንጻር ጉዳዩን በጥልቀት ለመረዳት መሞከር አለበት። ግለሰቡን የሚያዳምጠው መፍትሔ ለማምጣት ወይም እንደ ዳኛ ብያኔ ለመስጠት ሳይሆን፣ ለመርዳት እንደሚፈልግ ወዳጅ መሆን አለበት።

አንድ መሪ ለግለሰብ ወይም ለቡድን ችግሮች መፍትሔ ለማምጣት ከመሞከሩ በፊት፣ ችግሩን በጥሞና ማዳመጡ እንዴት አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያሳዩ ሦስት ምሳሌዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1) በአንድ የቦርድ ስብሰባ ላይ አጀንዳዎችን በተመለከተ የአሳብ ልዩነት ተነሣ። የቤተ ክርስቲያን መሪው ጥሩ ውሳኔ የመስጠት ፍላጎት ስለ ነበረው፣ ሁሉም ሰው አሳቡን እንዲሰጥ ጠየቀ። የሚናገሩትን ቃል ብቻ ሳይሆን፣ ስሜታቸውን ጭምር ለማዳመጥ ሞከረ። አንድ ሰው አንድን አሳብ በሚቃወምበት ጊዜ፣ መሪው ግለሰቡ ነገሩን እንዳይረዳ የሚያደርገውን ድብቅ ፍላጎት ለመረዳት ይሞክራል። ግለሰቡ መሪዎቹ ድብቅ ችግሮቹን እንደ ተ ረዱለት እስካላረጋገጠ ድረስ፣ የእነርሱን አሳብ ለመስማትም ሆነ ከእርሱ የተለየውን አሳብ በጸጋ ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም። ሰ ዎች ብዙውን ጊዜ አንድን ውሳኔ የሚቃወሙት ውሳኔውን ስለማይወዱት ሳይሆን፣ በሌላ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ግለሰቡ የቀረበውን አሳብ የሚቃወመው የወከሉት ሰዎች እንዴት ለሌሎች ሰዎች አሳብ ትንበረከካለህ? ብለው እንዳይወቅሉት በመፍራት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ስለ ውሳኔው ብቻ ሳይሆን፣ የላኩት ሰዎች እንደ ደካማ መሪ ይቆጥሩኛል የሚለውንም ፍርሃት ለማስወገድ መጣር አለበት ማለት ነው። ስለሆነም፣ ጉዳዩ ውሳኔውን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፣ የላኩት ሰዎች መሪውን የሚረዱበትንም መንገድ

የሚጨምር ይሆናል፡፡ ይህንን መረዳት የሚቻለው ደግሞ በግለሰቡ ልብ ውስጥ የተደበቀውን አሳብ በማዳመጥ ይሆናል፡፡ (ማስታወሻ፡- ይህ ማለት መሪው ወደ ስብሰባው ከመምጣቱ በፊት ሰዎች የቀረበውን አሳብ ሊቃወሙ የሚችሉባቸውን «ድብቅ» ምክንያቶች መገመት አለበት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም፣ ከስብሰባው በፊት በግል በመገናኘት ወይም በመግቢያ ላይ ሰዎቹ ውሳኔውን በተመለከተ ያላቸውን ፍርሃት ለማስወገድ መጣር ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ፣ ውሳኔው እንዲሰጥ በሚያደርገው ጥረት ችግሮች ሊገጥሙትና ድብቅ አሳብ ካላቸው ወገኖች ተቃውሞ ሊደርስበት ይችላል፡፡)

2) መሪው ጸበኛ ክርስቲያኖችን ለማስታረቅ የሚሞክር ከሆነ፣ ችግሩን በጥልቀት ለመረዳት ይችል ዘንድ መጀመሪያ ሰዎቹ እርስ በርሳቸው እንዲደማመጡ ማድረግ አለበት፡፡ መሪው መጀመር ያለበት መፍትሔ በመስጠት ሳይሆን፣ የግለሰቡን ወይም የቡድኑን ችግር ለመረዳት በመጣር መሆን አለበት፡፡ ሰዎቹ እርስ በርሳቸው ሳይወቃቀሱ የተፈጠረውን ችግር ለመረዳት እንዲችሉ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ መሪውና ሌላው ወገን አመለካከቱን እንዳዳመጠ ካረጋገጠ በኋላ ነው ለማዳመጥና የሌላውን ሰው አመለካከት ለመረዳት የሚሞክረው፡፡ ከዚህ በኋላ ብቻ ይሆናል መሪው የሚያቀርበውን የውሳኔ አሳብ ለመስማት የሚፈቅዱት፡፡

3) መሪው ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የሚጥር ከሆነ፣ ምእመናን ለምን የተወሰኑ ነገሮችን እንደሚያከናውኑ መረዳት አለበት፡፡ ሰዎች እነዚህን ነገሮች ለምን እንደሚያደርጉ ካረጋገጠ በኋላ ብቻ ነው ሁኔታውን እንዲረዱ ሊያግዛቸው የሚችለው፡፡ ይህ ማለት ሰዎች ለምን በሰዓቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደማይመጡ ወይም ለምን የአልኮል መጠጥ እንደሚፈትናቸው መጠየቅ አለበት ማለት ነው፡፡ ሁኔታውን ከተገነዘበ በኋላ እድገታቸውን የሚገታውን መሠረታዊ ችግር በማስወገድ ሊረዳቸው ይችላል፡፡



ጥሩ አድማጭ ለመሆን የቤተ ክርስቲያን መሪው በፍጥነት የመናገርና መፍትሔ የመስጠት ተፈጥሮአዊ ፈተናውን መቋቋም አለበት፡፡ የአለቅነት ስሜት ተሰምቶት ሰዎችን «እንዲህ አድርጉ! በዚህ ግቡ! በዚህ ውጡ!» ከማለት መቆጠብ አለበት፡፡ እንዲሁም ደግሞ ራሱን እንደ ሊቅ በመቁጠር ለችግሮቻቸው ሁሉ መፍትሔዎችን ለመስጠት መጣር የለበትም፡፡ ይልቁንም፣ እግዚአብሔር እነርሱን እንዲያገለግል የላከው አገልጋይ መሪ መሆኑን ማስታወስ አለበት፡፡ የቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ሊረዳ የሚችለው በሚገባ ሊረዳቸውና እነርሱም ይወድደናል ብለው ሲያስቡ ብቻ ነው፡፡ እነርሱን ለመረዳትና ይወድደናል ብለው እንዲያስቡ ለማድረግ መጀመሪያ ሊያዳምጣቸው ይገባል፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ መፍትሔ በመስጠት አንድን ሰው ወይም ቡድን ሊረዳ የሚችለው መጀመሪያ ያሉበትን ሁኔታ በጥልቀት ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ያዳመጣቸው እንደ ሆነ ብቻ ነው፡፡

ለ. ከዚያ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪው ሰዎቹ እንዲያድጉና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔርን እውነት ያካፍላቸዋል፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሰዎችን ወደ ትክክለኛ ውሳኔ ሊመራ፣ ወይም ክፍፍሉን በፈጠረው ጉዳይ ላይ መልስ ለመስጠት፣ ወይም ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማደግ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማገዝ የሚችለው በሚገባ ያዳመጣቸው እንደ ሆነ ብቻ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን መሪው እነዚህን ቅደም ተከተሎች አለማቀያየሩ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አንድን ሰው መርዳት የምንችለው ቃላቱንና ከሁኔታው ጋር የተያያዙትን ስሜቶች በሚገባ ስናጤናቸው ነው፡፡ ሰዎች አሳባችንን እንድናካፍላቸው የሚፈቅዱት እኛ አሳባቸውን ከተካፈልንላቸው በኋላ ነው፡፡

## የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን የሚያዳምጡባቸው አምስት መንገዶች፡፡

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሁለት ጆሮዎችና አንድ አፍ ቢሰጠንም፣ ከመናገር ይልቅ ማዳመጡ ያዳግተናል፡፡ አብዛኞቹ

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የንግግር ተለጥአ አላቸው:: የራሳቸውን አሳብ ለመግለጽ ይፈልጋሉ:: ነገር ግን እንዱ ሌላውን ለማዳመጥ አይፈልግም:: ያለፈውን ጊዜ የቦርድ ስብሰባ አስታውስ:: ወይም ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ምክር ለመስጠት ወደ አንድ ሰው ቤት የሄድክበትን ጊዜ አስታውስ:: ምን ያህሉን ጊዜ ነበር በመናገር ያሳለፍከው? ምን ያህሉንስ በማዳመጥ አሳለፍክ? ሊሆን የሚችለው አብዛኛውን ጊዜህን የጨረስከው በመናገር ወይም ሰውዬው ለሚያነሣው አሳብ እንዴት ምላሽ እንደምትሰጥ በማሰብ ነው:: ሌሎች የሚናገሩትን በማዳመጥ የምናጠፋው ጊዜ ብዙ አይደለም::

ከሌሎች ጋር ግንኙነት በምናደርግበት ጊዜ ልንጠቀም የምንችላቸው አምስት የማዳመጥ ዓይነቶች አሉ:-

1. አንዳንድ ጊዜ ግለሰቡ የሚናገረውን አሳብ ቸል እንላለን:: ይህ ብዙውን ጊዜ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ ያጋጥማል:: እየተናገርን ሳለ ሌሎች ሰዎች የጎንዮሽ ወሬ ገጥመው እናገኛለን:: በመጽሐፎቻቸው ላይ የሚጽፉና እያዳመጡን አለመሆናቸውን የሚያሳዩ ሌሎች ተግባራት የሚፈጽሙም አሉ:: ይህ ስሜታችንን ይጎዳዋል:: ምክንያቱም አለማዳመጣቸው ለአሳባችን ክብደት አለመስጠታቸውንና ለእኛ እምብዛም ክብር እንደሌላቸው ስለሚያሳይ ነው:: እየተናገረ ያለውን ሰው ቸል ማለታችን ፍቅርን አለማሳየት ነው:: ፍቅር የማናሳይ ከሆነ ደግሞ፣ እኛ በምንናገርበት ጊዜ እነርሱም አይሰሙንም:: አገልጋይ መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ሲናገሩ በጥንቃቄ በማዳመጥ ለእነርሱ ያለንን ፍቅርና እንደምንቀበላቸው ማሳየት አለብን:: ምንም እንኳን አሳባቸውን ለመቀበል ባንፈልግም ወይም ንግግራቸው አሰልቺ ቢሆንም፣ ይህን የማድረግ ኃላፊነት አለብን::

2. የምናዳምጥ ብናስመስልም፣ አናዳምጥም:: ሁላችንም ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ አሳባችን ሊባዝንብን ይችላል:: ወደ እኛ ሲመለከቱ የምናዳምጥ ቢመስልም፣ እውነቱ ግን አለማዳመጣችን ነው:: አሳባችን ወደ ቤታችን ወይም ወደ ሌላ አጀንዳ ይሄድብናል:: እየተነገረ ስላለው አሳብ ጥያቄ ስንጠይቅና አሳባችን ሌላ ቦታ



በመሄዱ ምክንያት ጥሩ ምላሽ ባለመስጠታችን ያፈርንባቸው ጊዜ ያት ይኖራሉ:: እያዳመጥን ብናስመስል እንኳን እየተነገረ ያለውን አሳብ የማንከታተል ከሆነ፣ አገልጋይ ባሪያዎች አይደለንም:: የኋላ ኋላ ሰዎች አለማዳመጣችንን ስለሚያውቁ፣ እነርሱም እኛ በምንናገርበት ጊዜ ላለማዳመጥ ይመርጣሉ::

3. ሰዎች ከሚናገሩት አሳብ የተወሰነውን ብቻ እንሰማለን:: ከአሳባቸው ጋር ስንስማማ ወይም ደግሞ የሚነገረውን አሳብ ለመቃወም በምንፈልግበት ጊዜ እናዳምጣለን:: ከዚህ ውጭ አሳባችንን ሌላ ቦታ እንስድዳለን::

4. እናዳምጣለን፣ ግን የምናዳምጠው መልስ ለመመለስ እንድንችል ብቻ ነው:: የግለሰቡን ንግግር እየመዘንን ተራችን ሲደርስ ምን ዓይነት ምላሽ እንደምንሰጥ እናውጠነጥናለን:: ግለሰቡን ለመረዳት ብንሞክርም፣ ይህንን የምናደርገው መልስ ለመስጠት በመፈለግ ነው:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ፣ በአብዛኛው ከሁለት ነገሮች አንዱን እያደረግን ነው ማለት ነው:: በመጀመሪያ፣ መስማማት አለመስማማታችንን ለማወቅ የግለቡን ንግግር እንመዝናለን:: ሁለተኛ፣ እያዳመጥን የግለሰቡን ልባዊ ፍላጎት ለመመዘን እንሞክራለን:: መልስ ለመስጠት ብለን በምናዳምጥበት ጊዜ፣ ለግለሰቡ ፍቅርና አክብሮት የለንም ማለት ነው:: የሰዎች ስሜት የሚጎዳው ብዙውን ጊዜ የአሳብ ልዩነታቸው በጣም የተራራቀ በመሆኑ ምክንያት ሳይሆን፣ ግለሰቦች ከመደመጥ ይልቅ ክርክር የገጠሟቸው መስሎ ስለሚሰማቸው ነው::

5. ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ግለሰቡን እናዳምጠዋለን:: ንግግራቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ስሜታቸውን ጭምር ለመረዳት እንሞክራለን:: ሁኔታውን በተናጋሪው ዓይን ለማየት እንጥራለን:: ስለ ጉዳዩ በስሜት የሚናገሩት ለምንድን ነው? ከግለሰቡ አሳብ ጋር ላንስማማ ብንችልም፣ የሚሰማቸው ሕመም ወይም የደረሰባቸው ችግር ይሰማናል:: የሚናገሩትን ከማዳመጥ ባሻገር የፊታቸውን ገጽታ በመመልከት በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር ለመረዳት እንጥራለን:: ለሰዎች ፍቅር እንዳለን የሚያሳይ

ዓይነት ማዳመጥ ይህ ነው:: ሰዎች እንዲያዳምጡን የሚያነሣሣቸው እንዲህ ዓይነት ማዳመጥ ብቻ ነው::

| |
|---|
| 31ኛ ጥያቄ:- ሀ) በዚህ በመጨረሻው መንገድ ያዳመጥከበትን ሁኔታ ከሕይወትህ አላይ:: ለ) ከተናጋሪው ጋር የነበረህ ግንኙነት እንዴት ነበር? ሐ) የተናጋሪውን ሁኔታ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማዳመጥ ለቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? መ) የዚህ ዓይነቱ ማዳመጥ ከሌሎች አራት የማዳመጥ ዓይነቶች በተለየ መንገድ ጠቃሚ የሚሆንባቸውን መንገዶች ዘርዝር:: |

## እምስተኛ ቀን:- ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ::

## ሳምንታዊ ስብሰባ

***የመወያያ ጥያቄዎች:-***

1. ሀ) እንደ ኮሚቴ ወይም ቦርድ ጥሩ ውሳኔዎችን ስለ መስጠት የተሰጠውን ትምህርት ከልሱ:: እያንዳንዱ ነጥብ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ግለጽ:: ለ) ከእነዚህ ነጥቦች መካከል ብዙ ኮ ሚቴዎች ወይም ቦርዶች በጥሩ ሁኔታ የማያከናውኗቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን? ጥሩ ያልሆኑ የቦርድ ውሳኔዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፈጠሯቸው አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ቦርዱ ጥሩ ውሳኔዎችን ለመስጠት ቢችል ኖሮ ምን ዓይነት ጥሩ ነገሮች ይከናወኑ ነበር?

2. ሀ) ለሁኔታዎች ምላሽ በሚገዛና ሁኔታዎችን በሚቆጣጠር መሪ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥ እንዳይመጣ በቀጥታ ቁጥጥር ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) ለገጠማቸው ሁኔታ የተቆጣጣሪነትን አመለካከት ቢይዙ ሁኔታው እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ግለጽ::

3. በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችሁ የተጋፈጠችውንና መለወጥ ያለበትን አንድ ሁኔታ ምረጥ:: ሀ) መሪዎች ለውጥ ለማምጣት <u>በቀጥታ</u> ሊቆጣጠሩ የሚችሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ለ) መሪ ዎች **<u>በተዘዋዋሪ መንገድ</u>** ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሏቸው ነገሮችስ?



ሐ) መሪዎች ለመቆጣጠር የማይችሏቸውና መጨነቅ የሌለባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥ ለማምጣት ሊከተሉ የሚገባቸውን ደረጃዎች ዘርዝር::

4. ባለፉት አምስት ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የታዩትን ለውጦች ገምግሙ:: ሀ) የታዩት ውጫዊ ለውጦች ምን ምንድን ናቸው? ለ) የታዩት ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በሰዎች ሕይወት ውስጥ የተመለከታችኋቸው ለውጦች ምን ምንድን ናቸው? መ) የእምነት ለውጦችስ? ሠ) ከእነዚህ ለውጦች መካከል በእምነት መብሰልን የሚያሳዩት የትኞቹ ናቸው? ረ) የምእመናንን የተግባርና የእምነት ለውጥ ለማምጣት ልታደርጉ የምትችሏቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

5. ሀ) የእውነተኛ መግባባትን ክፍሎች ዘርዝር:: ለ) ሁላችሁም የምታውቁትን አንድ ጥሩ የተግባቦት ችሎታ ያለው ሰው ምረጡ:: የዚህን ሰው ተግባቦት ውጤታማ ያደረገው ምንድን ነው? ሐ) ተ ግባቦቱ ውጤታማ ያልሆነበትን ሁኔታ ግለጹ:: ውጤታማ ያልሆነው ለምንድን ነው? መ) መሪዎች ሰዎቹ በዕለተ ሰንበት የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያዳምጡ የሚገድቧቸውን ነገሮች ለመቀነስ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

6. ሀ) ጥሩ ተግባቦት የሚጠይቁትን አገልግሎቶች ዘርዝር:: ለ) በአገልግሎቱ ውስጥ ማዳመጥ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? ሐ) መሪዎች ከማዳመጥ ይልቅ በመናገር ላይ ትኩረት በሚያደርጉበት ጊዜ የሚፈጠሩ ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?

# ትምህርት አሥራ አራት

## አንደኛ ቀን

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ቀዳሚ ኃላፊነት ውሳኔ መስጠትና እነዚህን ውሳኔዎች ለሰዎች ማሳወቅ ይመስለናል:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪን አገልግሎት በምንመርምርበት ጊዜ፣ ብዙ ጊዜው ሰዎችን በማዳመጥ እንደሚባክን እንረዳለን:: ሰዎችን በደንብ የማዳመጥ «ክህሎት» ካላዳበረ፣ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው ራእይ የመምራቱና ለችግሮቻቸው መፍትሔ የመስጠቱ አቅም በእጅጉ ይገደባል:: ትእዛዝ በመስጠት ላይ ከሚያተኩሩ የዓለም መሪዎች በተቃራኒ፣ አገልጋይ መሪዎች የተግባቦትን ክህሎት የምንጠቀመው ለየት ባለ መንገድ ነው:: ዛሬ ሰዎችን በርኅራኄና ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማዳመጥ ለአንድ መሪ ለምን እንደሚያስፈልግ የጀመርነውን እሳብ መግለጻችንን እንቀጥላለን::

**ከመናገር በፊት ተናጋሪው ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማዳመጥ ለአንድ መሪ ለምን እንደሚያስፈልግ::**

1. አንድ ሰው በሕይወቱ እንዲያድግ ወይም ችግሩን እንዲያሸንፍ ልንረዳው የምንችለው እውነተኛውን ችግር ያወቅን እንደ ሆነ ብቻ ነው:: እውነተኛውን ችግር ልናውቅ የምንችለው ደግሞ በጥልቀት ስናዳምጥ ነው:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚናገሩት ከእውነተኛው ችግር የራቀ ነገር ሊሆን ይችላል:: (ለምሳሌ፣ አንድ ጊዜ ከመሪዎች ጋር ስንነጋገር፣ ብዙ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶችን በአንድ ጊዜ በብዛት መክፈት አስፈላጊ አይደለም የምልባቸውን ምክንያቶች እገልጽ ነበር:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ ግን ትምህርት ቤቶቹ አስፈላጊዎች ናቸው በሚለው አሳባቸው መጽናታቸው አስገረመኝ:: ሁሉም ትምህርት ቤቶች መከፈት እሳባቸው የሚለውን አሳብ መሪዎች ካቀረቧቸው አሳቦች የትኛውም በበቂ ምክንያትነት ሲገልጽ አይችልም ነበር:: በኋላ ግን ይህ ቤተ ክርስቲያኖች በሙሉ ትምህርት ቤቶች ተክፍቶላቸው በሰላም እንዲኖሩ ለማስቻል የታሰበ መሆኑን ለመገንዘበ ችያለሁ::)



ድብቆቹን ምክንያቶች ለመረዳት የምንችለው ሰዎች የሚናገሩትን አሳብ በጥንቃቄ ስናዳምጥ ነው:: ሰዎች እውነተኞቹን ችግሮች ልባቸውን ከፍተው የሚያጋሩን ቀስ በቀስ ነው:: ለሰዎች በቂ ጊዜ ካልሰጠናቸው፣ ወደ ዋናው ችግራቸው ዘልቀን መፍትሔ ልንፈልግላቸው አንችልም:: በመናገራችን ከቀጠልን ደግሞ፣ ልናዳምጥ አንችልም:: ስለሆነም፣ አንድ ችግር ሲገጥመን ወይም በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ለሰው ምክር ለመስጠት በምንሞክርበት ጊዜ፣ በሚገባ አዳምጠን ችግሩን ካልተረዳን፣ ጠቃሚ የሆነ ምክር ልንሰጣቸው አንችልም::

> 1ኛ ጥያቄ፦ ሀ) አንድ የምታውቀው መሪ አንድ ችግር በሚገባ ባለማዳመጡ የተሳሳተ መፍትሔ ያቀረበበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለችግሩ ተገቢውን መፍትሔ እንዲሰጥ በሚገባ ማዳመጥ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው?

2. የሰዎችን እሳብ በከፊል ሰምተን ትክክል እሰመሆኑን ለማስረዳት በምንሞክርበት ጊዜ፣ ሌላውም ሰው የሚሰማን አሳባችን ትክክል አሰመሆኑን ለማስረዳት በመፈለግ ይሆናል:: ይህ ደግሞ የስሜት መጎዳትንና ክፍፍልን ያመጣል:: አሳባቸውን በምንፈታተንበት ጊዜ፣ እነርሱም አሳባችንን ለመፈታተን ይሽቀዳደማሉ:: ለሚናገሩት አሳብ እንዴት ምላሽ እንደምንሰጥ የምናስብ ከሆነ፣ በሚገባ ልናዳምጣቸው አንችልም:: ሰዎች በእውነተኛ ልብ እንዳዳመጥናቸው የሚያውቁትና የእኛን እሳብ ለማዳመጥ የሚፈቅዱት በትክክል የሰማናቸው እንደ ሆነ ብቻ ነው::

በተለይ በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ ብዙውን ጊዜ አንዱ ሲናገር ሌላው የሚያዳምጠው የድጋፍ ወይም የተቃውሞ አሳብ ለመሰንዘር በማሰብ ነው:: አብዛኛው ትኩረታችን የሚውለው የተናጋሪውን እሳብ በመረዳቱ ላይ ሳይሆን፣ እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚቻል በማሰብ ላይ ነው::

*ለምሳሌ፣ እንበልና አንተና ሌላ መሪ በቤተ ክርስቲያናችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መጀመር አስፈላጊ ነው አይደለም በሚለው አሳብ ላይ ትከራከራላችሁ:: እርሱ የማታ የመጽሐፍ*

*ቅዱስ ት/ቤት ያስፈልጋል ሲል፣ አንተ አያስፈልግም ትላለህ:: በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ እርሱ ጉዳዩን ያነሣና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መከፈት አስፈላጊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በሙሉ ይዘረዝራል:: አንተም የእርሱን ምላሽ በምትሰማበት ጊዜ፣ ለእያንዳንዱ ምክንያት ተቃራኒውን ታዘጋጃለህ:: በዚህ ጊዜ የምታዳምጠው እርሱን ለማዳመጥ አልነበረም:: ለዎች የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አለባቸው የሚል ሸክሙን ለመረዳት አልፈለግክም:: የምትሰማው አሳቦቹን ለመፈታተን ስትል ብቻ ነው:: የአንተ ተራ በሚደርስበት ጊዜ፣ የማታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መከፈት አስፈላጊ የማይሆንባቸውን ምክንያቶች መዘርዘርህን ትጀምራለህ:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ በአመዛኙ አንተና እርሱ አሸናፊ ለመሆን ትሽቀዳደማላችሁ:: ነገር ግን አሳቡን ብትረዳለት፣ ለቃሉ ያለውን ፍቅር ብታደንቅለትና ብትደግፈው፣ ከመፎካከር ይልቅ የተሻለ መፍትሔ ለማምጣት አብራችሁ ልትሠሩ ትችላላችሁ::*

ለዎች እቋማቸውን በፍቅር እንደምንረዳላቸው በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ ከችግሩ ሥር ዘልቀን እንድንረዳቸው ይፈቅዳሉ:: ቃላቸውን እንደምንረዳና ዳሩ ግን ሁኔታቸው እንደማይገባን በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ ሊሰሙን አይፈልጉም:: አንድን ሰው በጥልቀት ልናዳምጥ የምንችለው ከቃላቱ አልፈን ስሜታቸውን ወይም ሁኔታውን ለመረዳት ስንሞክር ብቻ ነው:: አብዛኞቹ ሰዎች ስሜታዊ እንዲሆኑ በሚያደርጓቸው ነገሮች ሳቢያ ጠንከር ያለ አሳብ ይይዛሉ:: በዚህ ጊዜ ስሜታቸውንና ምክንያቱን ካልተረዳን፣ ተቀባይነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት መቸገራችን የማይቀር ነው::

ብዙውን ጊዜ አመለካከታቸውን ለመረዳት ሳንጥር፣ አንድን ሰው በምናዳምጥበት ጊዜ፣ የምንረዳቸው በራሳችን ተሞክሮ ላይ ተመሥርተን ነው:: (ለምሳሌ፣ «አስታውሳለሁ በታመምኩ ጊዜ . . . » ወይም «በቤተ ክርስቲያኔ . . . » ልንል እንችላለን::) ስለሆነም፣ ስሜታችንን እና ተሞክሮአችንን በሌሎች ላይ እንጭናለን:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን ሌሎች የተደመጡ መስሎ አይሰማቸውም:: ሁላችንም የእኛ ሁኔታዎች ልዩ ናቸው ብለን እናስባለን:: በመሆኑም፣ መሪዎች ሊረዱን እንዳልሞከሩ ስለምናስብ



የተናገሩትን አሳብ እንቃወማለን:: እውቀታቸውን ለማሳየትና መልስ እንዳላቸው ለማመልከት እየሞከሩ ናቸው ብለን እናስባለን::

ሁላችንም በችግራችን ጊዜ ሊረዱን የሞከሩ ጥሩ የሚባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አጋጥመውናል:: ተሞክሮአችንን መናገር ስንጀምር እነርሱ ይቀድሙናል:: «ይህ ችግር በገጠመኝ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ አስታውሳለሁ:: እናም የምታልፍበት ሁኔታ ይገባኛል::» ከዚያም የገጠማቸውን ነገር በረዥሙ ይተርኩልናል:: በዚህ ጊዜ ስሜትህን እንዳትገልጽ መሪው ስላታለለህ ትናደዳለህ:: የሰዎችን ታሪክ በከፊል ሰምተን የራሳችንን ታሪክ በምንናገርበት ጊዜ የሚሆነው ይኸው ነው::

ተመሳሳይ ገጠመኝ እንዳሳለፍን በመግለጽ የሚያልፉበትን ሁኔታ እንደምንረዳ መግለጻችን አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን እነርሱ የሚፈልጉት በልባቸው ውስጥ ያለውን አሳብ ማካፈል ነው:: እኛ መናገርና ታሪካችንን ማውራት ስንጀምር ግን፣ እነርሱ መናገራቸውን ያቆማሉ:: ይህ ደግሞ ችግራቸውን እንዳንሰማ ወይም እንዴት እንደምንረዳቸው እንዳናውቅ ያደርገናል:: ሰዎች በልባቸው ውስጥ ያለውን አሳብ እስካልተናገሩ ድረስ፣ ከእስቸጋሪ ሁኔታቸው ሊፈወሱ አይችሉም:: ይህ ብቻ አይደለም:: አሳባቸውን ለማካፈል እስካልቻሉ ድረስ፣ የምንነግራቸውን ቃልና ችግራቸውን ለመፍታት ያስችላቸው ዘንድ የምንሰጣቸውን መንፈሳዊ ምክር ለመቀበል የሚያስችል አእምሯዊ ይዘት አይኖራቸውም:: ስለሆነም፣ መንፈሳዊ ምክሮችን ከመስጠታችን በፊት ሰዎች ለችግራቸው ጆሮ እንዳዋስናቸው ማረጋገጣቸው ወሳኝ ነው::

ይህ ክርስቲያኖችን በማማከሩ ረገድ እውነት ነው:: ላልዳነ ሰው በምንመሰክርበት ጊዜም ይህ እውነት ነው:: ግለሰቦቹን መዳን እንዳለባቸው ዒላማዎች ሳይሆን፣ እንደ ሰዎች ተመልክተን ችግራቸውን በምንረዳበት ጊዜ፣ ስለ ክርስቶስ ለመመስከርና ክርስቶስ ለእነርሱና ለቤተሰባቸው ችግር የሚሰጠውን መፍትሔ ለማቅረብ እንችላለን:: ነገር ግን ወንጌሉን ብቻ የምናካፍላቸው ከሆነ፣ እምብዛም በጊዜው ከሚጋፈጡት ችግር ጋር ሳይጣጣምላቸው ይችላል:: ክርስቶስ ውኃ ልትቀዳ ለወጣችው ሴት መናገር የጀመረው ካለችበት ሁኔታ በመጀመር ነበር:: እኛም ለን

ረቤቶቻችንና ለማናውቃቸው ለዎች በምንመለከርበት ጊዜ፣ መጀመሪያ ታሪካቸውን መስማት አለብን (ያዕ. 4:7-26)::

> 2ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪው ችግር ያለበትን ሰው ላያዳምጥ መፍትሔውን ብቻ ለመስጠት በመሞከሩ የለዎች ስሜት የተጎዳበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ብዙ ሳንናገር ከአጠገባቸው ቁጭ ብለን በምናዳምጣቸው ጊዜ እንዴት የምንወዳቸው መሆኑን እንደምናሳይ ግለጽ:: ሐ) ውይይቱን ተቆጣጥረን ስለ ራሳችንና ስለ አሳባችን ብቻ በምንናገርበት ጊዜ እንደማንወዳቸው የምናሳየው እንዴት ነው? መ) ለዎችን በሚገባ በማዳመጥ ችግራቸውን ለመረዳት በምትሞከርበት ጊዜ ወንጌሉን ለመቀበል ፈቃደኛ የሚሆኑት እንዴት ነው?

4. ሰዎች ምክራችንን የሚቀበሉት የተናገሩትን ማዳመጣችንን ሲያረጋግጡ ብቻ ነው:: ለእነርሱ እንደምናስብ ከተገነዘቡና ለእነርሱ የሚበጀውን ብቻ የምናስብ መሆናችንን በማወቅ ባሕርያችንን ካከበሩ፣ በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር ለማካፈል ነፃ ይሆናሉ:: ነገር ግን ወንጌላዊ እንደ መሆናችን መጠን፣ ሥራችንን ለማከናወን ብለን እንደምናነጋግራቸው ከተገነዘቡ፣ ወይም አንድ ጥሩ ያልሆነ ነገር ከባሕርያችን ውስጥ ከተመለከቱ፣ በልባቸው ውስጥ ያለውን ነገር መደበቃቸው የማይቀር ነው:: ስለ አጠቃላይ ነገሮች ሊነግሩን ቢችሉም፣ የግል ሕይወታቸውን ትግሎች አይገልጡልንም:: እንደ ሽማግሌዎች፣ መጋቢያን ወይም ወንጌላውያን ችግሩን ካላወቅን ደግሞ፣ ግለሰቡን ልንረዳው አንችልም:: ነገር ግን አንድ ሰው ችግሩን በሚያካፍለን ጊዜ፣ በፍቅር ካዳመጥን ችግሩ ችግራችን ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ችግሩ የደረሰበትና ለመርዳት የሚሞከረው ግለሰብ ወደ አንድ ጉዳይ በመመልከት ችግሩ የሚወገድባቸውን መንገዶች ይፈልጋሉ::

5. ሰዎች ከልባቸው በሚናገሩበት ጊዜ ለሜታቸውን ተ ቋቁመው ከእውነታ ባልተፋታ መንገድ ችግራቸውን ሊመለከቱ ይችላሉ:: ለአንድ ችግር መፍትሔ በሚፈለግበት ጊዜ ከሚከለቱት ችግሮች አንዱ ችግሩን በተጨባጭ በመመልከት ከሁሉም የተሻለ መፍትሔ እንዳንፈልግ ስሜታችን የሚከለክለን መሆኑ ነው:: ቁጣ፣ መጎዳት ወይም የልብ ሥቃይ ነገሮችን በተጨባጭ በመመልከት ስለ ጉዳዩ ለማሰብ ፈቃደኞች እንዳንሆን ሊያደርጉን ይችላሉ::



መጎዳታችን ሰዎች የሚሰጡንን ጠቃሚ ምክሮች እንዳንሰማ ይከለክለናል:: ነገር ግን ለምናምነውና ለምናከብረው ሰው የልባችንን አሳብ ለማካፈል ከቻልን፣ አእምሯችን ነገሮችን ከእውነታ ባልተፋታ መንገድ የመመልከት ብቃት ይኖረዋል:: በዚህ ጊዜ እንዴት ነገሮችን በተሻለ ሁኔታ ልናከናውን እንደምንችል ወይም በሕይወታችን እንዴት እንደምናድግ የሚሰጡንን ምክሮች ለመስማት እንችላለን:: ሁኔታውንም ከሌላ የእይታ አንጻር ልንመለከት እንችላለን::

> 3ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው ችግርህን በጥሞና በመስማቱ ምክንያት የቀረበልህን የመፍትሔ አሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆንክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) አንድ ለው ችግርህን በጥሞና ማዳመጡ ስለ ችግሩ በግልጽ እንድታስብ እንዴት እንዳገዘህ ግለጽ::

6. ሰዎች በግልጽ አሳባቸውን እንዲናገሩ በሚፈቀድላቸው ጊዜ፣ በአብዛኛው ለችግሮቻቸው መፍትሔ የመፍለግ ብቃት ይኖራቸዋል:: ስለ ችግሮቻቸው በሚናገሩበት ጊዜ፣ ነገሮች ግልጽ ይሆኑላቸዋል:: ይህ ሰዎች ስለ ችግራቸው እንዲናገሩና መፍትሔ እንዲያመጡ የማድረግ ሂደት ለዎችን እንዲያድጉ ለማገዝ እጅግ ጠቃሚው መንገድ ነው:: ብዙውን ጊዜ አንድ መሪ ሰዎች መፍትሔ በማግኘት ብቃታቸው እንዲያድጉ የሚያግዘው ጥያቄ ዎችን በመጠየቅና ሰዎቹ የራሳቸውን መፍትሔዎች እንዲያመጡ በማድረግ ነው:: ነገር ግን ለችግሩ የራሳችንን መፍትሔ በምንሰጥበት ጊዜ፣ ግለሰቡ የማሰብና ለችግሮቹ መፍትሔ የማግኘ ት ጥረት የማድረግ ዕድል አይኖረውም:: ብዙውን ጊዜ ምክር መስጠት ወይም ለችግሩ መፍትሔ መስጠት ያለብን ግለሰቡ የራሱን ችግር ለመፍታት ጥረት ካደረገ በኋላ ሊሆን ይገባል:: መሪ ዎች እንደ መሆናችን፣ ጥያቄዎችን በማቅረብ ወይም የሚያጠኗቸውን ነገሮች በመስጠት የአባሎቻችንን አስተሳሰብ መምራት አለብን:: ስለ መፍትሔው ካሰቡበት በኋላ ችግሩን መፍታት የሚቻልበትን መንገድ ይዘው እንዲመጡ እንጠይቃቸዋለን::

4ኛ ጥያቄ፡- እንበልና፣ አንድ ሰው ገንዘቡን አላግባብ በማባከኑ ምክንያት ችግር እየደረሰበት ነው። ወጭውን ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት ስላልቻለ በዚህ በኩል ልትረዳው ፈለግክ እንበል። ሀ) ይህንን ወንድም ለመርዳት 1) ለችግሩ መፍትሔ በመስጠት ወይም 2) ስለ ችግሩ በማሰብ የራሱን መፍትሔ እንዲሰጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ። ለ) ግለሰቡ ችግሩን እንዲረዳና የተሻሉ መፍትሔዎችን እንዲያዘጋጅ የትኛው አማራጭ የሚሻል ይመስልሃል?

7. ሰዎች እንደምናዳምጣቸውና አመለካከታቸውን ለመረዳት እየጣርን መሆናችንን በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት ይጠናከርና ይተማመኑብናል። በዚህም ጊዜ ስለ ችግሩ የምንሰጣቸውን አሳብ ለመቀበል ፈቃደኞች ይሆናሉ። አንተ እርሱን ለመረዳት ከሞከርክ፣ እርሱም አሳብህን በምትገልጽበት ጊዜ ለመረዳት ይሞክራል። በዚህ ጊዜ የቃላት ጥቃት ለማድረስ የሚፈልጉት ጠላት መሆንህ ይቀራል። አሁን ወዳጃቸው ስለምትሆን፣ በችግሩ ላይ አብራችሁ ልትሠሩ ትችላላችሁ።

8. እንደ መሪ፣ ከሥልጣንህ ሥር ያሉትን ወገኖች (ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች፣ ወጣቶች) ለመስማት ከሞከርክ በኋላ፣ እነርሱም አንተን ለመስማት የበለጠ ፈቃደኞች ይሆናሉ። የሌሎች ሰዎችን አመለካከት መጀመሪያ ለመረዳት በምትሞክርበት ጊዜ እያሌ ነገሮች ይከናወናሉ።

<u>በመጀመሪያ</u>፣ አሳባቸውን በተሳሳተ መንገድ ስትረዳ ወይም እነርሱ የማይፈልጉትን ውሳኔ ስትሰጥ፣ ይቅር ሊሉህ ፈቃደኞች ይሆናሉ። የማይፈልጉትን ውሳኔ ብትሰጥ (ለምሳሌ፣ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄያቸውን ውድቅ ብታደርግ)፣ በቂ ምክንያት ቢኖረው ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን እነርሱን ለመረዳት ባለመሞከርህ ምክንያት እንደ ተሳሳትክ ካወቁ፣ ስሜታቸው ይጎዳል። ይህም ከእነርሱ ጋር ያለህን ግንኙነት ያሻክረዋል።

<u>ሁለተኛ</u>፣ አሳብህ ከእነርሱ በሚለይበት ጊዜ ሳይቀር ለማለት የምትፈልገውን ይሰማሉ። ሰዎች መሪዎች በትክክል እንዳዳመጧቸው እርግጠኞች እስከ ሆኑ ድረስ፣ ለእነርሱ የማይመቹትን ውሳኔዎች ለመቀበል ዝግጁዎች ይሆናሉ። ነገር ግን



መሪው እንዳዳመጣቸው እርግጠኞች ካልሆኑ፣ ስለሚናደዱ ያን ያህልም ውሳኔውን አይደግፉም። ወይም የመሪውን ዕቅድ ለማሳካት ተግተው አይሠሩም።

<u>ሦስተኛ</u>፣ ሥራውን እንዴት በተሻለ መንገድ ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ወይም አንድ ያልገባቸው ነገር ካለ፣ ምክር ለመጠየቅ ወደ አንተ ይመጣሉ። ነገር ግን ለእነርሱ እንደማትጨነቅ ወይም የሚያቀርቧቸውን አሳቦች ለመስማት ፈቃደኛ አለመሆንህን ካወቁ፣ ምክር ፍለጋ ወደ አንተ ለመምጣት ፈቃደኞች አይሆኑም። ከዚህም የተነሣ የሚያከናውኑት ሥራ ጥራት የሌለው ወይም የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። አንተም እነዚህን ሰዎች ለማሳደግ የምታበረክተው አስተዋጽኦ ውስን ይሆናል።

5ኛ ጥያቄ፡- የሥራ አለቃህ ወይም የአገልግሎት መሪህ፣ ሀ) አሳቦችን በምታቀርብበት ጊዜ የማያዳምጥህ ከሆነ፣ እና 2) አሳብህን ባቀረብክ ጊዜ የሚሰማ ከሆነ (አሳቦችህ ተግባራዊ ባይደረጉም)፣ በአመራሩ ላይ ምን ዓይነት አመለካከት እንደሚኖርህ ግለጽ። ይህ መሪዎች የሠራተኞቻቸውን አሳብ ስለ መስማታቸው አስፈላጊነት ምን ያሳያል?

## ሌሎችን በምናዳምጥበት ጊዜ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት መሞከር

ጥሩ አመራር የምንፈልግ ከሆነ፣ መሪዎች ሰዎችን በምናዳምጥበት ጊዜ ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ክህሎታችን ማደግ አለብን። በጥሩ ሁኔታ በምናዳምጣቸው ጊዜ፣ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት እየጠለቀ ይሄዳል። ሁሉም የሌላውን ሁኔታ በማገናዘብ በጽሞና ማዳመጥ ከቻለ ደግሞ፣ በስብሰባዎች ላይ የተሻሉ ውሳኔዎችን መስጠት ይቻላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን በሚያዳምጡበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አለባቸው፡-

1. በአቀማመጣችን፣ በዓይኖቻችንና በእጆቻችን ለምናሳያቸው ምልክቶች ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ምሁራን እንደሚሉት፣ ከመግባቢያችን አብዛኛው የቃላት ልውውጥ የሌለበት ነው። ለምሳሌ ያህል፣ አቀማመጣችን ግለሰቡ የሚናገረውን ለመስማት ፈቃደኛ መሆን አለመሆናችንን ያሳያል። ግለሰቡን ፊት ለፊት

ማየት አለማየታችን፣ የፊታችን ሁኔታና ጣቶቻችንን ማፍተልተላችን፣ ሰዓታችንን ማየታችን ሰውየው የሚናገረውን ለመስማት መፈለግ አለመፈለጋችንን ያሳያሉ። ሰዎች ልባቸውን ክፍተው አሳባቸውን እንዲያጋሩን ከፈለግን፣ የመግባባት ምልክት ከፊታችን ላይ በማሳየት በጽሞና ልናዳምጣቸው ይገባል። በዚህ ጊዜም እያዳመጥናቸው መሆናችንን ያውቃሉ።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች ሲያናግሩን እያዳመጥናቸው አለመሆናችንን የሚያሳዩትን ነገሮች ዘርዝር። ለ) የአንድን ሰው ንግግር በፍላጎት እያዳመጥንና ያለበትን ሁኔታ እየተረዳን መሆናችንን ለማሳየት ልንጠቀም የምንችላቸውን የመግባቢያ ዘዴዎች ዘርዝር።

2. አንድን ሰው በምታዳምጥበት ጊዜ፣ የሚረብሹትን ነገሮች ሁሉ አርቅ። ስልክን መንቀል፣ ሞባይል ከሆነም ማጥፋት፣ ጸሐፊ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ ውይይት መሐል እንዳይጠራህ ማድረግ ያሻል። አንድ ሰው አሳቡን እያካፈለ እያለ አቋርጠን ሌላ ነገር የምናደርግ ከሆነ፣ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶኛል ብሎ ሊያስብ አይችልም። እየተናገረ ሳለ አታቋርጠው። መናገር የሚፈልገውን ተናግሮ እስኪጨርስ ድረስ አንተ የምትናገረውን ለመስማት ዝግጁ አይሆንም።

3. እየሰማኸው መሆኑን የሚያሳዩትን ዘዴዎች ተጠቀም። (ማስታወሻ:- ይህ በተለይ በአሳብ ለመረዳዳት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ጠቃሚ ዘዴ ነው።)

ሀ. የተናገረውን መልስህ ተናገር። እያዳመጥን መሆናችንን ከምናሳይባቸው መንገዶች መካከል ራሳችንን በአዎንታ መነቅነቅ፣ «አዎ»፣ «እህ» ወይም ሌላ ቃል ማሰማት፣ ወይም የተናገሩትን መልሶ መድገም ይገኙባቸዋል። (ለምሳሌ፣ «ምንም የሠለጠነ ሰው የለንም» ቢሉ፣ አንተም መልስህ፣ «እሂ፣ ምንም የሠለጠነ ሰው የላችሁም ማለት ነው?» ትላለህ።) ይህ አሳባችን ወደ ሌላ ቦታ ሳይባዝን እንድናዳምጥና ግለሰቡም እያዳመጥን መሆናችንን እንዲገነዘብ ያስችለዋል። ይህ ግን ግለሰቡ ያለበትን ሁኔታ በመረዳትና በርኅራኄ እየሰማን መሆናችንን የምናሳይበት ከሁሉም የተሻለ ውጤታማ መንገድ አይደለም።



ለ. የተናገሩትን በራስህ ቃላት ድገም። ይህ እያዳመጥክ ብቻ ሳይሆን፣ አሳባቸውን እየተረዳህ መሆንህን ጭምር የሚያሳይ ነው። (ለምሳሌ፣ ቀደም ሲል የተናገሩትን አሳብ በራስህ አገላለጽ በማስቀመጥ፣ «እንግዲህ በእናንተ አካባቢ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ብዙ የሠለጠነ የሰው ኃይል የለም ማለት ነው» ልትል ትችላለህ።) መሪው ግለሰቡ የተናገረውን አሳብ በራሱ ቃላት ጠቅለል አድርጎ ለማስቀመጥ በሚሞክርበት ጊዜ « . . . ማለትህን በትክክል ተረድቻለሁ?» ብሎ መጠየቁ ጠቃሚ ነው። ይህ እየተነገረ ያለውን ነገር ለመረዳት መሞከራችንን ያሳያል። ግለሰቡም የተናገረውን አሳብ በትክክል እንድንረዳለት ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ እንዲጨምር ያስችለዋል። እንዲሁም በተለየ መንገድ ተቀምጦ በሌላ መስኮት እንዲያይ በሚደረግበት ጊዜ አሳቡ ምን ያህል ከንቱ እንደ ሆነም እንዲረዳ ሊያግዘው ይችላል።

ሐ. የተናገረውን አሳብ በራስህ ቃላት በመግለጽ ከግለሰቡ ላይ ያየኸውን ስሜት ለማንጸባረቅ ሞክር። (ለምሳሌ፣ «እንግዲህ በአካባቢያችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የሚያስችል ሥልጠና የወሰዱ ብዙ ሰዎች አለመኖራቸው ከሐሰተኛ አስተማሪዎች መብዛት የተነሣ አሳስቧችኋል ማለት ነው።») ይህ እጅግ የጠለቀ የማዳመጥ ዓይነት ነው። በዚህ ደረጃ የምናዳምጠው ቃላትን ብቻ ሳይሆን፣ ከቃላት በስተጀርባ ያሉትን ስሜቶች ጭምር ይሆናል። ነገሮችን በዚህ መንገድ በምንገልጽበት ጊዜ፣ ግለሰቡ «ይህ ሰው ለችግራችን ያስባል ማለት ነው» ወደሚል ግንዛቤ ይገባል። ችግሩ እንደሚያሳስብህ በሚረዳበት ጊዜ ደግሞ በበለጠ ግልጽ ሆኖ መናገር ይችላል። («አዎን፣ እንዲያውም ባለፈው ሳምንት አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ . . . አስተምሮን ነበር» በማለት አሳቡን ሊቀጥል ይችላል።) አሁን ጫና እንዳደረበት ሳይሆን፣ ወዳጅ እንዳገኝ ስለሚያስብ፣ «እኔም ራሴ በቂ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ስለሌለኝ ለዚህ ችግር እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብኝ አላውቅም» ሲል ይቀጥላል። ይህ ግለሰቡ የሚፈልገውን ነገር እንዲናገር ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ውሳኔ የተጨነቀበትን ድብቅ ምክንያቶች እንዲያወጣ የሚያስችል ጥልቅ ማዳመጥ ነው።

7ኛ ጥያቄ፡- በዚህ ሳምንት እነዚህን ሁሉ ምላሾች ከጓደኛህ ወይም ከሆነ ሰው ጋር ተለማመድ። ሀ) እነዚህ ምላሾች አሳብህ ሌላ ቦታ እንዳይሄድ ወይም ንግግሩን ለማቋረጥ ከመሞከር ይልቅ፣ በንግግሩ ላይ እንድታተኩር ረድተውህ እንደ ሆነ አብራራ። ለ) ከሦስቱ መካከል የበለጠ ውጤታማ ሆኖ ያገኘኸው የትኛውን ነው? ለምን?

እሁን ግለሰቡ ታሪኩን ለማዳመጥ ፈቃደኛ መሆንህንና የምታስብለት መሆኑን ስላረጋገጠ፣ ችግሩን ለመፍታት አብራችሁ ልትሠሩ ትችላላችሁ። በዚህ ጊዜ የተለያዩ የችግር መፍቻ ዘዴዎችን በማቅረብ በየፊናችሁ መፎካከር አያስፈልጋችሁም። ነገር ግን በአጋርነት ችግሩን አብራችሁ ለመፍታት ትጥራላችሁ። (ለምሳሌ፣ «ችግርህን ተረድቻለሁ። እዎን፣ ችግሩን ለመፍታት የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መከፈት ያስፈልጋል። ነገር ግን ይህ ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። ሌላ ችግሩ የሚፈታበት መንገድ እስበህ ታውቃለህ? መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን እንዲያካሂዱና ይህ ደግሞ ለመሪነት መመዘኛ እንዲሆን ማድረግስ ያስኬድ ይሆን?» ልትል ትችላለህ።) የተለያዩ አሳቦችን በምታቀርብለት ጊዜ፣ ለመከላከል ሳይሞክር ለመስማትና ለማሰብ ፈቃደኛ ይሆናል። መጀመሪያ አንተ ግድ ብሎህ በጽሞና ስላዳመጥከው፣ እርሱም አሳብህን ባይደግፍም እንኳን ያዳምጥሃል። ችግሩ እንዳሳሰበህ ስለሚገነዘብ፣ በሚገባ ሊረዳህ ይፈልጋል።

8ኛ ጥያቄ፡- አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ጫና በማያሳድር መንገድ አሳቡን ለመግለጽ እንዲችል እንዴት በጽሞናና በመረዳት ሊያዳምጥ እንደሚችል የሚያሳዩትን ሌሎች መንገዶች ዘርዝር።

ስዎች ያሉበትን ሁኔታ እየተረዳን ስናዳምጣቸው፣ እግዚአብሔር በሚያስደንቅ መንገድ ከግንኙነቶች መካከል መራርነትን በማስወገድ ሰዎች አብረው እንዲሠሩ ያስችላቸዋል። በርኅራኄ ማዳመጥ እንዴት ሁኔታዎችን እንደሚለውጥ ለመመልከት ቀጥለን ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት።

ምሳሌ ቁጥር 1፡- ከተለያዩ ቤተ እምነቶች የመጡ ሁለት መሪዎች ሲገናኙ አንደኛው፣ «ከእናንተ ጋር በሰላም ለመኖር የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እደርጋለሁ። እናንተ በክርስቶስ



ወንድሞቼና እኅቶቼ ናችሁ። ቤተ ክርስቲያናችሁን ለመርዳት እኔም ሆንኩ ቤተ ክርስቲያናችን ምን ልናደርግ እንችላለን?» ይላል። የሌ ሆንኩ ቤተ ክርስቲያናችን ... ላው ቤተ እምነት መሪ 1) ወደዚያው ቤተ እምነት ሄደው አባላትና ላው ቤተ እምነት መሪ መሪዎች ከሆኑ በኋላ በሽማግሌዎች ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሰዎችና 2) ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን ለቅቀው ወደ እነርሱ እንዲመጡ የሚገፋፉ ወንጌላውያን እንዳስዘኗቸው ሲገልጽ፣ መሪ ው በአዎንታ ራሱን ይነቀንቃል። በዚህ ዓይነት ተጨማሪ አሳቦች ንግግሩን እንዲናገር ካበረታታው በኋላ፣ «እንግዲህ ከእናንተ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን በአባልነት በመቀበላችን በጣም ጎድተናችኋል ማለት ነው። ወንጌላውያኖቻችን የእናንተ አባላት ወደ እኛ እንዲመጡ መገፋፋታቸውም ትክክል እንዳልሆነ ታስባላችሁ። በዚህ ዓይነት ጥልቅ ጉዳት እንዳደረስንባችሁ እረዳለሁ። በበኩሌ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እጠይቃለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ መጀመሪያ ከእናንተ ጋር ስለ ጉዳዩ ሳንነጋገር ማንኛውም ሰው ከእናንተ ዘንድ ቢመጣ በአባልነት አንቀበልም። ለወንጌላውያኖቻችንም የእናንተ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ሰው በሚመጣበት ጊዜ ባለበት ቤተ ክርስቲያን ጌታን እንዲያገለግል እንዲያበረታቱት እንነግራቸዋለን። እባካችሁ ማንኛውም ወንጌላዊ የእናንተን አባል ካስኮበለለ እስታውቁኝና እንነጋገርበት» ይላል። በዚህ ጊዜ የተጎዳው ወገን ንዴት ይበርዳል። ከልቡ ውስጥ ንዴቱ ስለሚወጣ፣ መሪው ችግሩን በተለየ ሁኔታ በመመልከት የበለጠ በግልጽነት ይናገራል። «እንደዚያ ማለቴ አይደለም። ሆን ብላችሁ አባሎቻችንን እንዳልወሰዳችሁ ይገባኛል። በመሪዎችና በሕዝቡ መካከል ጥሩ ሰላም አልነበረምና ምእመኖቻችን ወደ እናንተ ቤተ ክርስቲያን የሄዱት በእናንተ ጥፋት አይደለም። የሚሄዱት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያለው ሰላም፣ አንድነትና አምልኮ ስላስደሰታቸው ነበር። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አንድነት እንዲፈጠር ልትረዱን ትችላላችሁ? ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዴት ልናመልክ እንደምንችል ሊታሳዩን ትችላላችሁ?» ሲል እንገዛ መፈለጉን ያስረዳል። አንደኛው መሪ ራሱን ዝቅ በማድረግ ሁኔታውን በሚረዳ መንገድ ለማዳመጥ በሚፈልግበት ጊዜ፣ ሌላው

መሪ የራሱን ጥፋት ለመቀበል ይገደዳል። አሁን ከጠላትነት ይልቅ በክርስቶስ ወንድሞች ሆነው ሊሠሩ ይችላሉ።

ምሳሌ ቁጥር 2፦ ወንጌላዊውና ሽማግሌዎች ስምምነት ስለሌላቸው፣ ወንጌላዊው ስለ ሽማግሌዎቹ የሐሰት ወሬ እያዛመተ ነው እንበል። ይህንን ችግር የሽማግሌዎቹ ስብሳቢ በሁለት መንገዶች ለመቆጣጠር ሊሞክር ይችላል።

ሰብሳቢው ወንጌላዊው የሚያደርገውን ነገር ከተገነዘበ በኋላ ይጠራውና፣ «እንደምሰማው መንፈሳዊ አለመሆናችንንና እንዳትሠራ እንዳደረግንህ በማውራት ላይ ነህ። እኔ ግን እነዚህ የምታወራቸው ነገሮች ውሸት መሆናቸውን ልነግርህ እፈልጋለሁ። በየሁለት ሳምንቱ እርብ እርብ እንጸልያለን፣ እንጾማለን። ምን ለማድረግ እንደምትፈልግ ንገረንና እናጸድቅልሃለን ብለን ነበር። አንተ ግን ምንም ነገር አላልከንም፣» በማለት ሽማግሌዎች ወንጌላዊው ፈጽሟል የሚሏቸውን ጥፋቶች በሙሉ ይዘረዝርለታል። «እንግዲህ፣ ከተናገርኩት ነገር የትኛው ውሸት እንደ ሆነ ንገረኝ፣» ሲል ያፋጥጠዋል። ወንጌላዊውም በእርሱ ግምት የሽማግሌዎች ስሕተት ናቸው የሚላቸውን 10 ነገሮች ይዘረዝራል። ሰብሳቢውም እነዚህ አሥር ነገሮች እንዴት የሽማግሌዎች ጥፋቶች ሊሆኑ እንደማይችሉ ያብራራለታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሊከራከሩ ይቆዩና ወንጌላዊው ከምንጊዜውም በላይ ሰብሳቢውም ሆነ ከእርሱ ጋር ያሉት ሽማግሌዎች ለእግዚአብሔር ሥራ ደንታ-ቢስ ናቸው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ ይወጣል።

ሰብሳቢው ወንጌላዊው የሚያደርገውን ነገር ከተገነዘበ በኋላ ይጠራዋል። ወንጌላዊው ሲመጣ፣ «ለቤተ ክርስቲያን ያከናወንከውን ሥራና ለጌታ ያለህን ፍቅር በጣም ነው የማደንቀው። ነገር ግን እኛ ሽማግሌዎች እንደ ጎዳንህ ስሰማ ደንግጫለሁ። እባክህ ችግሮቹ ምን እንደ ሆኑ በግልጽ ንገረኝና ላስተካክለው፣» ይለዋል። በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው በልቡ ውስጥ ያሉትን መጎዳቶች በሙሉ ይዘረዝራል። «ባለፈው ዓመት የሥራ ዕቅዶቼን አቅርቤላችሁ ምንም ምላሽ አልሰጣችሁኝም። ይለፍ ይውደቅ የማውቀው ነገር የለኝም። ሥራዬን እንዳከናውን ምንም በጀት አትሰጡኝም። ይህ ማለት እኔ



ለምሠራው ነገር ምንም ደንታ የላችሁም ማለት ይመስለኛል። እነዚህን ሁለት ጸበኛ ክርስቲያኖች እንድታነጋግሩ ብጠይቃችሁም፣ እስካሁን ምንም ነገር አላደረጋችሁም። ደመወዜ አጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የቤት ኪራይ ከከፈልኩ በኋላ የሚተርፈኝ ነገር የለም። የሆነች ነገር ቀምሼ ለማደር ስል ከዘመድ አዝማድ ብድር ለመጠየቅ እገደዳለሁ።» ወንጌላዊው ችግሮቹን ከዘረዘረ በኋላ መሪው፣ «በትክክል እንደ ተረዳሁህ ላረጋግጥ። በርግጥ ጎድተንሃል። ለቤተ ክርስቲያን እድገት የወጠንከውን ዕቅድ ምን ያህል እንደ ወደድን ስላልነገርንህ ተስፋ ቆርጠሃል። ልክ ነህ፣ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መንገድ ስታድግ ማየት ምን ያህል እንዳስደሰተን ልንነግርህ ይገባን ነበር። እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥፋት ስለፈጸምኩ፣ እባክህን ይቅርታ አድርግልኝ። ለሥራህ ዋጋ የሰጠን መስሎ እልተሰማህም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የማስተማር አገልግሎትህ ቤተ ክርስቲያናችንን በሚገባ እንደ ጠቀማት ሳልገልጽልህ ቀርቻለሁ። አገልግሎትህ በቤቴ አካባቢ ሦስት ሰዎችን ደቀ መዛሙርት እንዳደርግ ረድቶኛል። በጣም አስፈላጊ የቡድናችን አካል መሆንህን ለማሳየት ምን ላደርግ እችላለሁ?» የቤተ ክርስቲያን መሪው ጥፋቱን በትክክል በሚቀበልበት ጊዜ በወንጌላዊው ልብ ውስጥ ያለው ሕመም መወገድ ይጀምራል። «አየህ፣ እኔም ይቅርታ መጠየቅ እፈልጋለሁ። ለአገልግሎት ገንዘብ እልመደባችሁም ብዬ ስወቅሳችሁ ነበር። ነገር ግን ሕዝቡም ያን ያህል እንደማይሰጥ አውቃለሁ። ስለ እናንተ ለሌሎች መናገርም አይገባኝም ነበር። ኃጢአት ፈጽሜአለሁና እባክህን ይቅር በለኝ፣» ሲል ይቅርታ ይጠይቃል። «የሥራ ዕቅድህን እውን ለማድረግ አብረን ምን ልናደርግ እንችላለን? ለአገልግሎትህና ለደመወዝህ በቂ ገንዘብ እንድታገኝ ይቻል ዘንድ ምእመኖቻችን ገንዘብ እንዲሰጡ እንዴት ልናበረታታቸው እንችላለን?» ሲል ይጠይቃል የቤተ ክርስቲያን መሪው። ይህም ችግሩን ለመቅረፍ አብረው የሚሠሩ አጋሮች እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሮችን ለመፍታት የሚሞክሩት በአንደኛው መንገድ ነው። የማይስማሙባቸውን ነገሮች ይዘረዝራሉ። አንደኛው በሚናገርበት ጊዜ ሌላኛው

አለመስማማቱን የሚያሳዩትን ምክንያቶች በአእምሮው ሲዘረዝር ይቆያል፡፡ ተናጋሪው እየተደመጠ አለመሆኑን ያውቃል፡፡ የፍርድ ብያኔ ከማግኘቱ በፊት በፍርድ ችሎት ፊት ምርመራ እየተደረገለት መስሎ ይሰማዋል፡፡ ለዚህም ነው እውነተኛውን ችግርና በልቡ ውስጥ ያለውን አሳብ የማይናገረው፡፡ ከዚህ ይልቅ ዝም ብሎ ቁጣው እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ምንም እንኳን መሪው በክርክሩ ቢያሸንፍም፣ ወንጌላዊው የበለጠ ተጎድቶና የሽማግሌዎ ቹን ሥራ ለማደናቀፍ ቁርጥ ውሳኔ አድርጎ ይወጣል፡፡

በሁለተኛው ማብራሪያ ውስጥ ግን ሽማግሌው በጽሞና ስላዳመጠና ስሕተቶቹን ስለ ተቀበለ፣ ወንጌላዊው ጥፋቱን ተ ቀብሏል፡፡ ብዙም ሳይቆይ አብረው ለመሥራት ወስነዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ራሳቸውን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በግልጽ ሊነጋገሩ ይችላሉ፡፡

9ኛ ጥያቄ፡- የመዘምራን ቡድን በእምልኮ ላይ ምን ያህል ጊዜ መጠቀም እንዳለበት መዘምራኑና ሽማግሌው ሊስማሙ አልቻሉም፡፡ ሀ) ሽማግሌው መጀመሪያ በሚገባ ሳያዳምጥ የሽማግሌዎቹን አሳብ ብቻ ይዞ ውይይቱን ከጀመረ፣ ችግሩን እንዴት ሊፈታ ይችላል? ለ) ሽማግሌው መጀመሪያ ችግሩን በሚገባ ካዳመጠ፣ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው እንዴት ነው? ሐ) ሽማግሌው እነዚህን ሁለት የተለያዩ ዘዴዎች ቢጠቀም የሚመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

4. ከአንድ ሰው ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ፣ በግለሰቡና በአመለካከቶቹ ላይ ያለንን የጥላቻ ስሜት ማስወገድ አለብን፡፡ «አገሌና እገሌ የዚያ ጎሳ አባላት ስለሆኑ፣ ሁልጊዜም ነገሮችን የሚያከናውኑት በዚህ መንገድ ነው፡፡» ወይም «ይህ ሰውዬ ሁልጊዜ ም ነገሮችን ያለ ምንም ክፍያ በነፃ ለማግኘት ይፈልጋል፣» ከሚሉ ዓይነት አሳቦች ነፃ መሆን አለብን፡፡ በአንድ ሰው ጎሳ፣ ጾታ፣ የኢኮኖሚ ደረጃ ወይም የቤተ እምነት ስም ላይ የጥላቻ ስሜት ካለን፣ የሚናገረውን በሚገባ ለማዳመጥ አንችልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስሜት እንድንጠራጠራቸውና ከንግግራቸው ውስጥ ድብቅ መልእክቶችን እንድንፈልግ ያደርገናል፡፡ በመሆኑም፣ በክፍት አእምሮ ማዳመጥ አለብን፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ አስቀድመን ከውሳኔ



ላይ ከደረስን፣ በሚገባ ለማዳመጥ፣ ለመገምገምና የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት አንችልም፡፡ እንዲሁም ደግሞ አንድ ሰው ይናገራል የምትለውን አሳብ ቀድመህ ለመገመት መሞከር የለብህም፡፡ ግለሰቡ የሚናገረውን ነገር አስቀድመን የምንገምት ከሆነ፣ የምንሰማውም ለመስማት የምንፈልገውን ወይም ግለሰቡ ይናገራል ብለን የምናስበውን ነገር ብቻ ይሆናል፡፡

5. በድርጅታችን ውስጥ አለመግባባቶች እንዳይነሱብቱ ከፈለግን፣ ሰዎች ከእኛ ጋርም ሆነ እርስ በርሳቸው በነጻነት በአሳብ ሊለዩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን፡፡ በዚህ ሁሉ ግን ስእነርሱ ያለን ፍቅርና ተቀባይነት ሊቀንስ አይገባም፡፡ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ ሰዎች በአሳብ ለመለያየት የማይፈቀድላቸው ከሆነ፣ አሳባቸውን ለመግለጽ አይፈልጉም፡፡ ይህም ከሁሉም የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት አያስችለንም፡፡ በአመዛኙ ሰዎች ንዴታቸውን ለማብረድ ሲሉ መሪውን ለማማት ወይም ውሳኔዎቹን ላለመደገፍ ይመርጣሉ፡፡ ውሳኔዎቹ ጥሩ ቢሆኑም እንኳን ለመቀበል አይፈልጉም፡፡ ከአንድ ሰው ጋር በአሳብ በማንስማማበት ጊዜ፣ «እኔ ባልስማማም እነዚህን አሳቦች የማራመድ መብት እንዳለህ አምናለሁ፣» ልንል ይገባል፡፡ ይህ ነጻነት ከሌለ፣ አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ያለውን አሳብ በግልጽ ላይናገር ይችላል፡፡

10ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 4:15 እንብብ፡፡ ሀ) በጤናማ ግንኙነት ውስጥ እውነትና ፍቅር አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው? ለ) ፍቅር የሌለበት እውነት ግንኙነቶችን ሊጎዳ የተመለከትከው እንዴት ነው? ሐ) እውነት የሌለበት ፍቅር ግንኙነቶችንና የእግዚአብሔርን ሥራ ሲጎዳ የተ መለከትከው እንዴት ነው?

የቤተ ክርስቲያን መሪው ተናጋሪው ያለበትን ሁኔታ በሚረዳ መንገድ ካዳመጠ በኋላ የራሱን አመለካከት በውጤታማ መንገድ እንዴት እንደሚያካፍል ማወቅ አለበት፡፡

በምዕራፍ 15 ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ጤናማ ግንኙነት በ«አሸናፊ/አሸናፊ» የግንኙነቶች ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ማለት ሁለቱም ወገኖች አንድን ጉዳይ የሚያጠናቅቁት በአሸናፊነት ወይም ለሁሉም ምርጥ የሆነ መላ እንዳገኙ በመተማመን ነው

ማለት ነው:: ያሉበትን ሁኔታ በሚረዳ መንገድ ለዎችን በምናዳምጥበት ጊዜ፣ እነርሱም እኛን ለማዳመጥ ፈቃደኞች ይሆናሉ:: ማዳመጣችን ራሳችን አሸንፈን እነርሱ እንዲሸነፉ ሳይሆን፣ እነርሱ እንዲያሸንፉ የምንፈልግ መሆናችንን ያረጋግጥሳቸዋል:: ይሁንና፣ ለሌሎች ፍቅርን በማሳየት ከሚናገሩት እሳብ ሁሉ ጋር መስማማቱ ብቻ በቂ እይደለም:: የራሳችንንም አመለካከት በትሕትና ልንነግራቸው ይገባል:: የስሜት መጎዳት የሚጠገነውና ሥራው ለእግዚአብሔር ክብር የሚከናወነው ሁለቱም ወገኖች እንደ ተደማመጡ፣ የራሳቸውን እሳቦች በግልጽ ለማካፈል እንደ ቻሉና ምርጥ የሆነውን መፍትሔ በጋራ እንደ ፈለጉ እርግጠኞች ሲሆኑ ብቻ ነው:: ነገር ግን አንድ ሰው ለዎች እንዳዳመጡት እርግጠኛ ካልሆነ ወይም በሁኔታው ተጎጂ እንደ ሆነ የሚሰማው ከሆነ፣ ችግሩ አልተፈታም ማለት ነው:: ይህ በቅርብ ጊዜ ደርሶብኛል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጥተው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ እንደ ጎዳቸውና የሚጠብቋቸውን ነገሮች እንዳላደረገላቸው ገለጹለት:: እኔም ለፈጸምኩት ጥፋት ይቅርታ ጠይቄ ስብሰባው ተጠናቀቀ:: ሽማግሌዎቹ ግን የራሳቸውን ጥፋቶች ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም:: እኔ «ተሸናፊ»፣ ሽማግሌዎቹ ደግሞ «አሸናፊዎች» ሆነን ሰብሰባው ስለ ተጠናቀቀ፣ በልቤ ውስጥ የመጎዳት ስሜት ይዤ ተመለስኩ:: እነዚህን ለዎች ይቅር ለማለትም በልቤ ጥረት ማድረግ ነበረብኝ::

በውይይቶች ውስጥ «ተሸናፊ» በምንሆንበት ጊዜ፣ በአብዛኛው ተጎድተንና ተቆጥተን እንሄዳለን:: ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ከተፈለገ፣ የራሳችንንም አመለካከት ለማካፈል መጠንከር አለብን:: አንዱ ተወቅሶ ሌላው በሚሞገስበት ጊዜ ስብሰባው ስኬታማ አይሆንም:: በሁሉም አለመስማማቶች ውስጥ ማለት ይቻላል ሁለቱም ወገኖች የተወሰነ ጥፋት ይኖራቸዋል:: ስለዚህ ሁለቱም ወገኖች ይቅርታ የሚጠይቁት ነገር ይኖራል ማለት ነው:: በመሆኑም፣ ሌላውን ሰው መስማቱ ብቻ በቂ እይሆንም:: በእውነተኛ ፍቅር የራሳችንን አመለካከት የምናካፍልበት ጊዜ መኖር አለበት:: ይህንን ልናደርግ የምንችለው ግን በሌላው ሰው ውስጥ ያለውን መጎዳት እርሱን በማዳመጥ ስናስወግድለት ነው::



1. ሰዎች እንዲረዱንና እንደ ተጫንናቸው እንዳይሰማቸው ለማስቻል የሚያግዙ ሦስት ነገሮች አሉ:-

ሀ. ሌላው ወገን እንዲለማን የሚያደርግ የመተማመን መንፈስ ወይም ግለሰባዊ ክብር ማሳደግ እለብን:: አለመተማመን እስካለ ድረስ፣ ትክክለኞች ብንሆን እንኳን የምናደርገው ነገር ብዙም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም:: የሚናገሩትን አሳብ በማዳመጥና ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት፣ እንዲሁም የራስህን ስሕተቶች በመቀበል ለመተማመን መሠረት ልትጥል ትችላለህ:: ይህም ሌሎች እንዲያዳምጡህ የሚያግዝ ነው::

ለ. በግንኙነቱ ውስጥ ካለው ስሜታዊ ሥቃይ ራሳችንን ለማራቅ መሞከር አስብን:: እኛም ሆንን ሌላው አካል የግልጽነት መንፈስ ሊኖረን ይገባል:: ከተናደድክ፣ ሁኔታውን በትክክል ልትገመግም አትችልም፤ ራስህንም በእግባቡ ለመግለጽ ትቸገራለህ:: ሌላው ሰው መቆጣትህን ሲያውቅ የምትናገረውን እይሰማም:: ሌላውም ሰው ከተቆጣ፣ አንተ የምትናገረውን ነገር ሊሰማ አይችልም:: ከተቆጡ፣ ከተጎዱ፣ ግድ ከሌላቸው ወይም የራሳቸውን እሳብ ብቻ የሚከላከሉ ከሆነ፣ በግልጽነት ልትግባባ አትችልም:: ሰዎች የበለጠ እንዳይናደዱ ለማድረግ አንዳንድ እውነታዎችን መደበቅና በጥንቃቄ ቃላትን መምረጥ ይኖርብናል:: ብዙውን ጊዜ አሳባቸውን ለመስማትና ለመረዳት እንደምትፈልግ በምታሳይበት ጊዜ፣ ሰዎች ያንተን እሳብ ለመስማትና ስመረዳት ይጥራሉ::

ሐ. አሳቦቻችንን በግልጽ ማቅረብ እለብን:: በልባችንና እእምሯችን ውስጥ ያሉትን ነገሮች ማድበስበስ የለብንም:: አሳባችንን በሚገባ እደራጅተን ራሳችንን በጥሩ ሁኔታ መግለጽ አለብን:: በዚህ ጊዜ እድማጫችን እሳባችንን ሊረዳ ይችላል:: ውይይታችንም በእውቀት ላይ የተመሠረተ ይሆናል:: ማብራሪያችን ከተድበሰበሰ ግን፣ በተሳሳተ መንገድ የመረዳት ሁኔታ ይጨምራል:: ይህም በበኩሉ ለተጨማሪ ጉዳት በር ስለሚከፍት፣ ከጋራ ውሳኔ የመድረሱ ዕድል ይጠብባል::

11ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉት ወጣቶች በአምልኮ ጉዳይ ላይ ከሽማግሌዎች ጋር ተጋጭተዋል እንበል:: ሀ) መሪው ወጣቶቹ እርሱ እንደሚፈልገው ማምለክ እንዳለባቸው ነበር የነገራቸው - ይህ ማለት እርሱ አሸናፊ እነርሱ ተሸናፊዎች ይሆናሉ ማለት ነው:: ይህ ወጣቶቹ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል? ለ) መሪው ወጣቶቹን ለመረዳትና እነርሱ የሚፈልጉትን ነገር ለማድረግ ብቻ ነበር የፈለገው? ማለትም እርሱ ተሸናፊ እነርሱ አሸናፊዎች ይሆናሉ ማለት ነው:: ይህ በወጣቶችና በሽማግሌዎች የረዥም ጊዜ ግንኙነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? ሐ) ሽማግሌዎቹ መጀመሪያ ወጣቶቹን ለመረዳትና ከዚያም ወጣቶቹ የእነርሱን እሳብ እንዲረዱ ለማድረግ ቢሞክሩ ምን ዓይነት ውጤት ይገኛል? ሁኔታውን በዚህ መንገድ ቢያስተካከሉ፣ የወጣቶችና የሽማግሌዎች የረዥም ጊዜ ግንኙነት ምን ዓይነት ይሆናል?

## ሁለተኛ ቀን

## በሕዝብ ፊት የመናገር (የሕዝባዊ ተግባቦት) ክህሎት

እስካሁን ከሰዎች ጋር አብረን ለመሥራት እንድንችል የተግባቦት ክህሎት እንዴት አንድነትንና ፈውስን ሊያመጣ እንደሚችል ስንነጋገር ቆይተናል:: አገልጋይ መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ሰዎችን መጀመሪያ በማዳመጥ ለእነርሱ ያለንን አክብሮት እናሳያለን:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ እኛን ለማክበርና የምንናገረውን እሳብ ለመስማት ፈቃደኞች ይሆናሉ:: ውጤታማ የመግባባት ብቃት ከሌለን፣ ውጤታማ አመራር ልንሰጥ አንችልም:: ምክንያቱም ሰዎች ሊሰሙን ወይም ሊታዘዙን አይፈልጉምና:: መሪዎች ለምእመናን በቂ መረጃ ካልሰጡ፣ ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን ራእይ ለመፈጸም ተግተው ሊሠሩ አይችሉም:: በዚህ ፈንታ ከስንበት እምልኮ ያለፈ ነገር አስፈላጊ አይደለም ብለው ያስባሉ:: እንደ አንድ አካል ለአንድ ዓላማ ስለማይሠሩ ብዙም ሳይቆይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል ይፈጠራል:: የሕዝባዊ ተግባቦትን ክህሎት በመጠቀም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን በሙሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሠሩ ሊያደርጉ ይችላሉ::



12ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሕዝባዊ ተግባቦት የቤተ ክርስቲያን አመራር ዐቢይ ክፍል የሚሆንባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ:: ለ) መግባባትን የማይችል ሰው እንዴት ምእመናንን ወደተፈለገው ግብ ሊያደርስ እንዳልቻለ የሚያሳዩትን ምሳሌዎች ስጥ:: ሐ) ጥሩ የመግባባት ችሎታ ያለው ሰው ምእመናን ለአንድ ዓላማ እንዲሠሩ ያነሣሣበትን ሁኔታ ግለጽ:: መ) በሁለቱ መሪዎች መካከል የነበረው ልዩነት ምን ነበር? የመግባባቶቹ ውጤቶች ምን ምን ነበሩ?

እግዚአብሔር ምእመናን ሁሉ ተባብረው በመሥራት ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን ዓላማ የሚያሳኩበትን መሣሪያ ሰጥቷል:: ይህም የሕዝባዊ ተግባቦት ክህሎት ነው:: ነገር ግን እንደ ማንኛውም መሣሪያ የተለያዩ አጠቃቀሞችን መከተል ይቻላል::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ሕዝባዊ ተግባቦትን በአግባቡ ሳንጠቀም እንችላለን:: ማረሻ የሌለው ሰው ስለ ማረሻ አጠቃቀም ሊያስብ አይችልም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመግባቢያ መሣሪያን እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደሚጠቀሙ አያስቡም:: እምብዛም የአመራር መሣሪያ አድርገው አይጠቀሙም:: የሚወስኗቸውን ውሳኔዎችና ውሳኔዎቹን የሰጡባቸውን ምክንያቶች ለምእመናን አይናገሩም:: ምእመናን ለአንድ ዓላማ እንዲሠሩ አያደርጉም:: በመሆኑም፣ ብዙ ሥራ አይሠራም::

<u>ሁለተኛ</u>፣ የሕዝባዊ ተግባቦትን መሣሪያ ልንጠቀም እንችላለን:: ነገር ግን መሣሪያው የተሳለ ባለመሆኑ፣ በብቃት ሳንጠቀምበት እንችላለን:: እንጨትን በቀላሉ ለመቁረጥ ከፈለግን፣ ስለታም ምሳር ያስፈልገናል:: እንዳለመታል ሆኖ፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕዝባዊ ተግባቦትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመጠቀም ይሞክራሉ:: ነገር ግን ብዙም ክህሎት የላቸውም:: ይህ'ደግሞ በብቃት ሕዝቡን እንዳይመሩ አድርጓቸዋል::

<u>ሦስተኛ</u>፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎታችንን ለማካሄድ የሕዝባዊ ተግባቦትን መሣሪያ በጥበብ ልንጠቀም እንችላለን:: ጥበብ ባለው እጅ ውስጥ ያለ ስለታም መጋዝ በፍጥነት ግሩም አድርጎ ይቆርጣል:: በተመሳሳይ መንገድ፣ የሕዝባዊ ተግባቦት መሣሪያ

ክህሎት ባለው መሪ እጅ አመራሩን የበለጠ ውጤታማ ያደርግለታል።

አንድ መሪ ውጤታማ የሕዝባዊ ተግባቦት ክህሎት እንዲኖረው ከፈለገ፣ ሕዝባዊ ተግባቦትን ጠቃሚ የአመራር መሣሪያ የሚያደርጉትን ክህሎቶች መማር አለበት።

## የጥሩ ተግባቦት አስፈላጊነት

ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ተግባቦት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ አይገነዘቡም። ብዙ ሰዎች በዕለተ እሑድ አንድ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስታወቂያ በሚናገርበት ጊዜ ይህ ግልጽ መረጃ ለመስጠት ጠቃሚ ጊዜ መሆኑን ይዘነጋሉ። ይህ ማስታወቂያውን ለሚናገር ወይም የሽማግሌዎችን ውሳኔ ለሚያስተላልፍ ሰው ወሳኝ ጉዳይ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም እርሱ ተናገር የተባለውን ከተናገረ ወዲያ አፈጻጸሙ የፈለገውን ዓይነት ቢሆን እርሱን አያስጨንቀውም ይሆናል። ነገር ግን መልእክቱን የምናስተላልፍበት መንገድ ሰዎች እንዳይሰሙን ወይም ትኩረት እንዳይሰጡን የሚከለክል ቢሆንስ? በዚህ ጊዜ ሰዎች በአመራራችን ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ይኖራቸዋል? መቼም ጥሩ ሊሆን አይችልም። ወይም ደግሞ በሰብከት ክህሎት ላይ እምብዛም ትኩረት ሳያደርግ ብድግ ብሎ ቢሰብክስ? ግለሰቡ ጥሩ መረጃ ሊያስተላልፍ ቢችልም፣ በሚሰብክበት ጊዜ አድማጮቹ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ቢወስዳቸው፣ ስብከቱ የሁሉንም ሰው ጊዜ አባክኗል ማለት ነው።

ሁሉም መሪዎች ጥሩ የተግባቦት ብቃት ለአመራራቸው ወሳኝ መሆኑን መረዳት አለባቸው። ክህሎት ያለው አገልግሎት አስፈላጊ የሚሆንባቸው አምስት ምክንያቶች-

1. ክህሎት ያለው ተግባቦት የአመራር መሠረት ነው። ተግባቦት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት እምብርት ነው። ሰባኪዎች፣ መጋቢያን፣ ወንጌላውያንና ሽማግሌዎች የሚያገለግሉት በሕዝብ ፊት መልእክቶችን በማስተላለፍ ነው። እንዲያውም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሞላ ጎደል ሁሉም አገልግሎት



የሚካሄደው በሕዝብ ፊት በሚተላለፉ መልእክቶች አማካኝነት ነው ማለት ይቻላል። አንድ መሪ ሰዎች ሕዝቡ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ ወዳዘጋጀው ግብ ለመሥራት ተግተው እንዲሠሩ ሊያነሣሣ የሚችለው በተግባቦት አማካኝነት ነው። ሰዎች መሪው የሚናገረውን ካልሰሙ፣ አይታዘዙትም ማለት ነው፣ ካልታዘዙት ደግሞ፣ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ የመምራት ብቃት አይኖረውም። የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ሰዎች የምናደርሰውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የምናግዛቸው በሕዝብ ፊት (በአደባባይ) ቃሉን በመናገር ነው። ስለሆነም፣ ይፋዊ ተግባቦት ለሁሉም አመራር ውጤታማነት ወሳኝ ነው ማለት ነው።

2. ብዙውን ጊዜ ሰዎች የአንድን ሰው የመምራት ብቃት የሚለኩት በንግግር ችሎታው ነው። አንድ መሪ አሳቡን ጥሩ አድርጎ የማያስባስብ፣ የሚንተባተብና አሰልቺ ንግግር የሚያደርግ ከሆነ፣ ሰዎች ክህሎት ያለው መሪ አይደለም ብለው ይደመድማሉ።

3. መሪ በጥሩ የተግባቦት ችሎታው ተጠቅሞ ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን ግቦች አብረው እንዲሠሩ ሊያስተባብራቸው ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ የሚሰጡት በቀዳሚነት የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ በማካፈልና ሰዎች ራእዩን ለመደገፍ እንዲነሣሡና እውን እንዲያደርጉት በማስቻል ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራእዩን በግልጽ ለሕዝቡ ካላብራሩ፣ ሕዝቡ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር እንድናደርግ ይፈልጋል ስለሚሉት ራእይ ደስተኞች ካልሆኑ፣ ለቤተ ክርስቲያን ራእይና ዕቅድ ለማውጣት የተደከመው ድካም ሁሉ ከንቱ ሆኗል ማለት ነው። ብዙ ራእዮችና ዕቅዶች የማይሳኩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ራእዮችና ዕቅዶች በአግባቡ ለሕዝቡ በማብራራት ለተግባራዊነቱ እንዲነሣሡ ስለማያደርጓቸው ነው።

4. አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እውነታዎችን በትክክልና በግልጽ ካላብራራ፣ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ይገባቸዋል። ጳውሎስ ሁነኛ መልእክት የማይሰጥ የመለከት ድምጽ ግራ እንደሚያጋባ ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 14:7-10)። በተመሳሳይ

ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ የቤተ ክርስቲያን ሥራ እንዲከናወን ከፈለገ፣ ግልጽና ትክክለኛ ምሪቶችን መስጠት አለባቸው። ሁላችንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግልጽ ያልሆኑ መልእክቶችን ሲናገሩ ሰምተን እናውቃለን። ነገሮች ግልጽ ያልሆኑና ግራ የሚያጋቡ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ሰዎች ሰምተው አይታዘዙም።

5. አሰልቺውን የአምልኮ ፕሮግራም ትርጉም ወዳለው አምልኮ የሚለውጠው የይፋዊ ተግባቦት ክህሎት ነው። ለአምልኮ የመጡት ሰዎች ደስ የሚሰኙት ብቁ የአምልኮ መሪዎች፣ በአገልግሎቱ የተካኑ ሰባኪዎችና ክህሎት ያላቸው ማስታወቂያ ተናጋሪዎች ሲያገለግሉ ነው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንዲያድጉና አንዳንዶች ደግሞ እንዳያድጉ ከሚያደርጉ ዐበይት ምክንያቶች አንዱ የይፋዊ ተግባቦት ክህሎት ነው ልንል እንችላለን። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እሳት የላሱ ተናጋሪዎች ሲኖሯቸው፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አሰልቺ ተናጋሪዎችን መድረክ ላይ ያቆማሉ።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፡- ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ተግባቦት ያስፈልጋል የምትልባቸውን ሌሎች ምክንያቶች ዘርዝር። |

**የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተግባቦቶች ከሁሉት አቅጣጫዎች እንዲካሄዱ ማድረግ ይኖርባቸዋል።**

ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን አካል ወይም ቤተሰብ መሆኗን ተናግሯል። ጤናማ አካል ሁሉም የሰውነት ክፍሎች አብ ረው የሚሠሩበት ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ፣ ተግባቦት ከራስ ወይም ከአእምሮ ወደ እግር (ለምሳሌ፣ ኳሱን ሲጋው) መተላለፍ አለበት። እግርም መረጃውን ወደ አእምሮ መመለስ አለበት። ጤናማ ቤተሰብ ደግሞ እያንዳንዱ አባል የሚነጋገርበትና እርስ በርስ የሚረዳዱበት ነው። ባል ሁልጊዜም እየተናገረ ሚስቱ ወይም ልጆቹ ምንም ነገር እንዳይናገሩ ዕድል ሊነሳቸው አይገባም። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን የምትኖረን መሪዎች ለሕዝቡ፣ ሕዝቡ ደግሞ ለመሪዎች መልካም ተግባቦት የሚያደርጉባት ነች። መሪዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እየተከናወነ ስላለው ነገር፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን እንዴት መሪዎችና ምእመናን ወደ ወጠኑት ግብ እየተንቀሳቀሰች እንዳለ በየጊዜው መግለጽ አለባቸው። መሪዎች



የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚያስቡትንና የሚፈልጉትን ነገር ለማወቅ ይችሉ ዘንድ ምእመናን አሳባቸውን እንዲገልጹ ማበ ረታታት አለባቸው። ይህም መሪዎች ከአንዳንድ ተናጋሪዎች ወይም ራሳቸውን መግለጽ ለሚወዱ ምእመናን ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም አባላት መስማት በሚቻልበት መንገድ መካሄድ አለበት። ለምሳሌ ያህል፣ የአምልኮ መሪዎች ሕዝቡ ስለ አምልኮው ያለውን አሳብ ማወቅ አለባቸው። በሚዘመሩት መዝሙሮች ደስተኞች ናቸው? ሙዚቃው በጣም ይጮሃል? ሕዝቡ ቢጋራ የሚዘምርበት ሰዓት እንዲበዛና መዘምራኑ ለአጭር ጊዜ ብቻ እንዲዘምሩ ይፈልጋሉ? የአምልኮ መሪዎች የእሑድ ቀን አምልኮው ሁሉም ሰው ትርጉም የሚያገኝበት እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉት የምእመናንን አሳቦች በመረዳት ነው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናንን አሳብ መ ረዳታቸው ለምን ይጠቅማል? ለ) ቤተ ክርስቲያን የአባላትን አሳብ ለማግኘ ት ምን ዓይነት ዘዴዎችን ልትጠቀም ትችላለች? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን በተሻለ ሁኔታ አስተያየት ለመቀበል ምን ማድረግ አለባቸው ትላለህ? |

## ለይፋዊ ተግባቦት ክህሎቶች የሚሆኑ አጠቃላይ መርሖዎች

አገልጋይ መሪዎች መሆን እንዳለብን መዘንጋት የለብንም። እንደ አገልጋይ መሪዎች፣ ሰዎች በቀላሉ ሰምተው እንዲረዱን ለማድረግ የሚያስችሉትን ነገሮች ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል። ችሎታችንን ሁሉ ተጠቅመን የአሳብ ልውውጥ ለማድረግ እንችል ዘንድ የምንናገራቸውን ቃላትና የምናከናውናቸውን እንቅስቃሴዎች መምረጡ የእኛ ኃላፊነት ነው። አገልጋይ መሪ የትኛውንም የተ ሳሳተ ግንዛቤ ለመቀነስ የሚችለውን ሁሉ ጥረት በማድረግ አሳቢነቱን ያሳያል።

ተናጋሪው በሚገባ የመዘጋጀት ኃላፊነት አለበት። አሳቡን ለማስተላለፍ የፈለገው ራሱ ተናጋሪው ስለሆነ፣ ሰዎች እንዲረዱት ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። የይፋዊ ተግባቦት አንዳንድ ጠቃሚ እውነቶች ከዚህ በታች ተመልክተዋል። እውነቶቹ ቀላሎች ቢመስሉም፣ ብዙውን ጊዜ እነዚህን የይፋዊ ተግባቦት

መሠረታዊ እውነቶች ስለምንዘነጋ፣ የተሳካ የአሳብ ልውውጥ ሳናከናውን እንቀራለን።

1. በተግባቦቱ ምን መፈጸም እንደምንፈልግ ቀደም ብለን ማቀድ አለብን። መረጃ ማስተላለፍ ነው የምንፈልገው? ሰዎች አኗኗራቸውን እንዲለውጡ ለማደፋፈር እንፈልጋለን? ምእመናን ለሥራ እንደ መምጣት ያሰውን ተግባር እንዲያከናውኑ ለማደፋፈር ነው? ልናዝናናቸው እንፈልጋለን? ለአምልኮ ልናዘጋጃቸው እንፈልጋለን? በተግባቦቱ ለማከናወን ከምንፈልገው ነገር አንጻር ራሳችንን የምንገልጽበት መንገድ የተለያየ ይሆናል።

2. ለመናገር የምንፈልገውን መልእክትና ለማስተላለፍ የምንፈልገውን ስሜት በማለብ በሚገባ መዘጋጀት አለብን። አሳባችን ግልጽ ካልሆነ፣ አድማጮቻችን ግልጽ መልእክት ላያገኙ ይችላሉ። በመሆኑም፣ ቀደም ብለን ለማስተላለፍ የምንፈልጋቸውን እውነታዎች ማለብ አለብን። እነዚህ አሳቦች በአእምሯችን ውስጥ ተጠየቃዊ (ሎጂካል) ሆነው እንዲቀናበሩ በቅጡ ማለብ ይጠበቅብናል። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይዘጋጁ በሚናገሩበት ጊዜ፣ አለመዘጋጀታቸው ይታወቅባቸዋል። አንድ ዓይነት አሳብ መደጋገም፣ ግልጽ ያልሆኑ አሳቦችን መናገር፣ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊተላለፍ የሚችለውን ነገር ማንዛዛት አለመዘጋጀታቸው እንዲታወቅ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። በሚገባ ያልተዘጋጁ መሪዎች ብዙ ጊዜ ያባክናሉ።

ምን ዓይነት ስሜቶችን ለማስተላለፍ እንደምንፈልግም ማለብ አለብን። ሰዎች ተጸጽተው ንስሐ እንዲገቡ እንፈልጋለን? ወይስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን አውቀው ደስ እንዲሰኙ እንሻለን? ምእመናኑ ለመታዘዝ ራሳቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ልናደፋፍራቸው እንፈልጋለን? አንድ ሰው በተረጋጋ ስሜት እውነታዎችን ብቻ ቢዘረዝራላቸው፣ ሰዎቹ ላይለወጡ ይችላሉ። ተናጋሪው የመደነቅ፣ የደስታ ወይም የኀዘን ስሜት ማሳየት አለበት። ሌሎችም የመደነቅ፣ የደስታ ወይም የኀዘን



ስሜት ሊቋደሱ የሚችሉት እነዚህ ነገሮች በተናጋሪው ላይ የታዩ እንደ ሆነ ነው።

ንግግራችን የበለጠ አስፈላጊ በሆነ መጠን፣ ዝግጅታችንም ያን ያህል በጥንቃቄ የተሞላ መሆን አለበት። እግዚአብሔር እውነቱን በስብከት ወይም በማስተማር እንድናስተላልፍ ከፈለገ፣ የበለጠ በጥልቀት መዘጋጀት አለብን። ብዙውን ጊዜ ዐቢይ ነጥቦቻችንን፣ የምንጠቀምባቸውን ጥቅሶችና እውነቶችን ለማጠናከር የምናነሣቸውን ምሳሌዎች በወረቀት ላይ ማስፈር አለብን። ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንድናስተምር የሚፈልገውን መልእክት በትክክልና እጥር ምጥን ባለ መንገድ እንድናቀርብ ይመራናል።

> 15ኛ ጥያቄ፡- ዮሐንስ 3፡16ን ለሕዝብ ልትሰብክ ነው እንበል። ሀ) ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ለሰዎች የምታካፍላቸውን ቢያንስ አምስት ነጥቦች አዘጋጅ። ለ) በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ለማሳየት የምትፈልገው ስሜት ምንድን ነው? ሐ) እያንዳንዱ ነጥብ የበለጠ ግልጽ ስሜታዊ ኃይል እንዲኖረው ምን ዓይነት ምሳሌዎችን ትጠቀማለህ?

3. መልእክታችንን ለማስተላለፍ ትክክለኛ ቃላትንና ተግባራትን መምረጥ አለብን። ቃላት አሳባችንን ለሌሎች ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ስለሆነም፣ የምንጠቀምባቸውን ቃላት በጥንቃቄ መምረጥ አለብን። አንዳንድ ቃላት ከሌሎች በበሰጠ አሳብን የመግለጽ አቅም አላቸው። ከሌሎች በበለጠ ስሜትን የመግለጽ ብቃት ያላቸው ቃላትም አሉ። አንዳንድ ጊዜ ቃላትን በተደጋጋሚ ስለምንጠቀም፣ ትርጉማቸው ሊታጣ ይችላል። ለምሳሌ፣ ለባኪው እንደ «ጸጋ» ያለን ቃል በተደጋጋሚ ሊጠቀምና ሕዝቡ ግን ትርጉሙን ላያውቅ ይችላል። እንደ «ምሕረት» ያሉ አንዳንድ ቃላት ደግሞ የተለያዩ ትርጉሞችን ስለሚሰጡ፣ ግራ መጋባትን ይፈጥራሉ። ክህሎት ያለው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን ቃላት በማጤን አድማጮቹ በትክክል መረዳታቸውን ያረጋግጣል። አሳቡንና ስሜቱን ከሁሉም በተሻለ መንገድ የሚገልጹትን ቃላት ይጠቀማል።

እንዳንድ ተናጋሪዎች የሕዝቡን ስሜት ቢያነሣሡም፣ አድማጮቹ ለምን ስሜታቸው እንደ ተነሣሣ አያውቁም። በተ

ደጋጋሚ «ሃሌ ሉያ» ወይም «አሜን» እያሉ ቢጮሁም፣ ለምን ጉዳይ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ አያውቁትም:: እንዳንድ ተናጋሪዎች አድማጮቻቸውን ለማስደነቅ በመፈለጋቸው ምክንያት ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ በሚጠይቁበት ሰዓት ሳይቀር «ሃሌ ሉያ» እንዲሉ ይፈልጋሉ:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተናጋሪው ቃላት እንዲመጣ ከሚፈለገው ውጤት ጋር አይገናኝም:: መሪዎች ሰዎች ስሜታዊ በመሆንና መንፈሳዊ መስለው ለመታየት ብለው እንዲጮሁ ማድረግ የለባቸውም:: አማኞች የተደሰቱበትን ወይም ያዘኑበትን ምክንያት ሳያውቁ ዝም ብለው በሚጮሁበት ጊዜ የግብዝነትን ኃጢአት ሊፈጽሙ ይችላሉ::

ክህሎት ያላቸው ተናጋሪዎች ቃላቸውንና ስሜታቸውን በጥሩ ሁኔታ ሊያጠናክሩ የሚችሉትን እንቅስቃሴዎችም ያውቃሉ:: ለምሳሌ፣ ክርስቶስን በማገልገል ስለሚገኝ ደስታ እየተናገርን ሳለ የምንጮህና የድንጋጤ ገጽታ የሚታይብን ከሆነ፣ ሰዎች ክርስቶስን በማገልገላችን ደስተኞች መሆናችንን ለማመን ይቸገራሉ:: ወይም ደግሞ ድምጻችንን ዝቅ አድርገንና ከፊታችን ላይ ምንም ዓይነት ስሜት ሳይነበብ የምንሰብክ ከሆነ፣ ሰዎች ትኩረት ሰጥተው ሊያዳምጡን ሊቆዩና ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚነገሩትን እውነቶች ለማጣጣም መቸገራቸው የማይቀር ነው:: የፊት ገጽታችንን ለማስተላለፍ ከምንፈልገው መልእክት ጋር ካላጣጣምንም፣ እንዲሁ ሰዎች መልእክታችንን ለመከታተል ይቸገራሉ:: ስለሆነም ከበድ ባሉት ጉዳዮች ላይ የምንጮህና ብዙ እንቅስቃሴ የምናደርግ ከሆነ፣ ወይም ሰዎች እንደ ቀልድ ወይም ረብሻ የሚመለከቷቸውን ነገሮች የምናደርግ ከሆነ፣ ሰዎች ቃላችንን በጥንቃቄ ሊያዳምጡ አይችሉም::

የምንናገራቸውን ነገሮች ሰዎች በጽሞና እንዳይከታተሉ የሚያደርጉ ነገሮችን የማድረግ ልማድ ካለብን፣ ይህንን ልማድ ማስወገድ አለብን:: አንዳንድ ሰዎች በንግግራቸው መሐል «እህ» የሚል ቃል እየወትረው ይጠቀማሉ:: ለምሳሌ ያህል፣ «ዛሬ እህ በጣም እህ የተለየ እህ ቀን ነው» ሊሉ ይችላሉ:: አንዳንዶች ደግሞ በመፍራታቸው ምክንያት እላባቸውን ይቆራርጣሉ:: ይህ ግን ሰ



ዎች አሳባችንን እንዳይከታተሉ ሊያደናቅፋቸው ይችላል:: አለባበሳችን ከቦታው ጋር የማይጣጣም ከሆነ፣ ሰዎችም በአለባበሳችን ተረብሸው መልእክቱን ላይከታተሉ ይችላሉ:: ሱፍና ክራባት እንድናደርግ ሊጠበቅብን፣ እኛ ግን ሸሚዝ ለብሰን ብንሄድ፣ ከምንናገረው ነገር በላይ ስለ ልብሳችን ሊያስቡ ይችላሉ:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች መልእክታችንን እንዳይሰሙ የሚያደርጉትን ነገሮች ላናውቅ ስለምንችል፣ ጓደኞቻችን ችግሮቻችንን በመንገር የበለጠ ጥሩ የአደባባይ ተግባቢዎች እንድንሆን እንዲያግዙን ልንጠይቃቸው ይገባል::

> 16ኛ ጥያቄ:- አንድ የቅርብ ጓደኛህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተናገርከውን ማስታወቂያ ወይም ስብከት እንዲገመግም ጠይቀው:: ከግምገማው በፊት በምን ምን ዓይነት ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ግለጽለት:: የግምገማው ዓላማ በሕዝብ ፊት የተሻለ ተናጋሪ እንድትሆን ለማገዝ መሆኑንና ይቀየመኛል ሳይል ማንኛውንም የተመለከተውን ነገር እንዲነግርህ አስታውሰው:: ሀ) በቃላት አጠቃቀምህና በአሳብ ቅደም ተከተል፣ ለ) በፊት ገጽታህ፣ በድምጽህ ቅላጼ፣ በእንቅስቃሴዎችህ እንዴት ለውጥ ልታመጣ እንደምትችል አስተያየቱን እንዲገልጽልህ ንገረው:: ሐ) አሳብህን በሚገባ እንዳታስተላልፍ እንቅፋት የሆኑህ አንዳንድ ልማዶች ምን ምንድን ናቸው?

4. ለሕዝብ መልእክት የሚያስተላልፍ ሰው በመግቢያውና በመደምደሚያው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት:: ተናጋሪው የአድማጮቹን ቀልብ ለመያዝ የሚሞክረው ገና ከመግቢያው ላይ ነው:: ካፊቴሪያ ውስጥ ከምንጠጣው በላይ ቤት ውስጥ የሚፈላ ቡና ከሚጥምባቸው ምክንያቶች አንዱ ቤት ውስጥ ቡና ሲቆላ መዓዛውን ስለምናሸት ነው:: ገና ሲቆላ የሚያውደው ሽታ ሰዎች ጥሑም ቡና ለመጠጣት እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል:: ለዚህ ነው በባህላዊ መንገድ ቡና በሚፈላባቸው ቤቶች ውስጥ ቡናው ተቆልቶ ሊወርድ ሽታው ወደ ሁሉም ሰው እንዲደርስ የሚናፈሰው:: በተመሳሳይ መንገድ፣ ሰዎች የማዳመጥ ረሃብ እንዲይዛቸው የሚያደርገው የማስታወቂያው ወይም የስብከቱ ጅማሬ ነው:: ክህሎት ያለው ተናጋሪ ገና ከመጀመሪያው ላይ የሕዝቡን ቀልብ የሚያስገዛ አንድ ነገር ያደርጋል:: የሚናገረው ነገር ለሰሚዎቹ

በጣም አስፈላጊ መሆኑን ይናገራል:: ተናጋሪው አንድ የሚጠቅማቸው ነገር እንደሚናገር ከገመቱ፣ አድማጮቹ የሚነገ ረውን ነገር ለመረዳት መሳ ትኩረታቸውን ይሰጣሉ:: ለመስማት ፈቃደኞች ከሆኑ ደግሞ፣ ለመሰወጥም ፈቃደኞች ይሆናሉ::

ስናስተምርና ስንሰብክ ቀዳሚው ትኩረታችን መረጃ መስጠት ሳይሆን፣ ሕዝቡ እንዲሰወጡና ይበልጥ ክርስቶስን እንዲመስሉ ማደፋፈር መሆን አለበት:: ስለሆነም፣ የስብከቱ መደምደሚያም ወሳኝ ነው:: መደምደሚያ ሁለት ዐበይት ነገሮችን ያደርጋል፡-

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ያስተሳሰፍነውን መልእክት ዐበይት ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል:: ሰዎች የተነገረውን እሳብ እንዲያስታውሱ ለማገዝ ዋና ዋናዎቹን ነገሮች ብቻ በማጠቃለያ መልክ እንሰጣቸዋለን::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ይኖሩ ዘንድ መሰወጥ ያለባቸውን የተወሰኑ መንገዶች ያሳያቸዋል:: ብዙውን ጊዜ በስብከት ወቅት ሰዎችን የምንጠይቀው በክርስቶስ እንዲያምኑ ነው:: ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው አብዛኞቹ ማደፋፈሪያዎች አማኞች በተለያዩ መንገዶች እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንዲመሳሰሉ የሚጠይቁ ናቸው (ለምሳሌ፣ ኢያሱ 24:14-27):: አማኞች እንዲሰወጡ የሚጠይቁ ስብከቶችን በምናቀርብበት ጊዜ እንዲሰወጡ የምንፈልገው በምን በኩል እንደ ሆነ በግልጽ በማስቀመጥ ስብከታችንን ማጠናቀቅ አሰብን:: እነዚህ የሰውጥ ጥያቄዎች «እግዚአብሔር በምን በምን ጉዳዮች ላይ መሰወጥ እንዳለባችሁ ያሳያችሁ» የሚሉ ዓይነት ድብስብሶች ሳይሆኑ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲሰወጥ የሚፈልጋቸውን ነጥቦች በግልጽ የሚያሳዩ መሆን አለባቸው:: ምእመናን የሚያስታውሱት እነዚህን ዝርዝር ነጥቦች ነው:: መንፈስ ቅዱስም በልጆቹ ሕይወት ውስጥ ለውጥን ለማምጣት የሚጠቀመው እነዚህኑ ነጥቦች ነው:: (ለምሳሌ፣ ንግግራችን ለሚስታችን እንዴት ፍቅር ማሳየት እንዳለብን የሚያመለክት ከሆነ፣ ወንዶች በዚህ ሳምንት ሚስቶቻቸውን ለመርዳት ቤት ውስጥ ምን ምን ዓይነት ሥራዎችን ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ልንናገር እንችላለን::)



| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- በሚቀጥለው ቅዳሜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥራ ቀን እንደሚኖር ለማስታወቅ ፈልገሃል እንበል:: ሀ) ሰዎች ለማዳመጥ እንዲፈልጉ ለማነሣሣት ይህንን ማስታወቂያ እንዴት ትጀምራለህ? ለ) ሰ ዎች እንዲሰተፉ ለማነሣሣት በማስታወቂያው ማጠቃለያ ላይ የምትናገራቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? |

5. አንድ ተናጋሪ በውጤታማ መንገድ መልእክቱን እንዳያስተ ላልፍ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ማስወገድ አለበት::

ሀ. ያለ በቂ ዝግጅት መናገር፡- ብዙውን ጊዜ በቅጡ ሳንዘገጅ ብድግ ብለን ብንናገር ምንም ችግር አይፈጠርም ብለን እናስባለን:: «ስሰብክ፣ ሳስተምር ወይም ማስታወቂያ ስናገር ማስተ ላለፍ ያለብኝን መልእክት እንዳስተላልፍ መንፈስ ቅዱስ አይ ረዳኝምን?» በማለት በተሳሳተ መንገድ ማቴዎስ 10:19-20ን የሚጠቅሉ አገልጋዮች አሉ:: በርግጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ይረዳሃል-ይህንን የሚያደርገው ግን የድርሻህን ከተወጣህ ነው:: እግዚአብሔር ሁላችንም አስቀድመን ስለምናከናውናቸው ነገሮች የምናስብበትን አእምሮ ሰጥቶናል:: የምንናገረውን ነገር በጸሎት በምናዘጋጅበት ጊዜ፣ እርሱ ዝግጅታችንን ይመራል:: ለማስተማር ወይም ለመስበክ ወይም አምልኮን ለመምራት ምን ማድረግ እንዳለብ አስቀድመን በማንዘጋጅበት ጊዜ፣ ለሰሙ መናገር ትልቅ ክብደት የሚሰጠው ነገር አይደለም በማለት እግዚአብሔርን እየተሳደብን ነው:: ይህ በግድየለሽነት ሊከናወን የሚችል ነገር ነው ማለታችን ነው:: አምባሳደሮች አሳባቸውን በማቀናጀት፣ ምን መናገር ወይም መጻፍ እንዳለባቸው በጥንቃቄ ያቅዳሉ:: ይህንንም የሚያደርጉት ሰዎች የመንግሥታቸውን አቋም እንዲያውቁላቸው ስለሚፈልጉ ነው:: እኛስ የነገሥታትን ንጉሥ ስናገለግል የበለጠ ጥንቃቄ ልናደርግ አይገባምን? በሚገባ አስመዘጋጀታችን አድማጮቻችንንም እንደ መናቅ ነው:: ጥሩ መልእክት ለማስተላለፍ ጊዜ ያልሰጠን ሰው ለማዳመጥ ጊዜዬን የማባክነው ለምንድን ነው? በጥንቃቄ በመዘጋጀት ለአድማጮቻችን ያለንን ፍቅር እንገልጻለን:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ መልእክታችንን በግልጽ ከማስተላለፋችንም በላይ፣ በቀላሉና በአጭሩ ልንገልጽላቸው እንችላለን:: በአመዛኙ ሰዎች የአመራር ብቃታችንን የሚለኩት በመናገር ብቃታች ላይ ተ

መሥርተው ነው። በመሆኑም፣ ማስታወቂያ ልንናገር ወደ መድረኩ ከወጣን በኋላ ብንንተባተብና የሌላ ሰው እገዛ ብንጠይቅ፣ ሰዎች የአመራር ብቃታችንን በጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከቱታል።

ለ. አሳስፈላጊ መረጃ መስጠት፦ በአመዛኙ ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎችና ማስታወቂያ ተናጋሪዎች መልእክቱን ለማስተላለፍ ከሚያስፈልገው ያለፈ ነገር ይናገራሉ። ብዙ ነገር መስማታቸው ሰዎች በዋናው ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዳያደርጉ እንቅፋት ይሆንባቸዋል። ተገቢውን መልእክት ለማስተላለፍ መናገር ያለብንን ሁሉ ልንናገርና አሳስፈላጊ የሆነውን መረጃ ልናስቀር ይገባል።

ሐ. የምንናገረውን አሳብ ጥሩ አድርጎ አለማቀናጀት፦ በአመዛኙ ቀደም ብለው የማይዘጋጁ ሰዎች ጥሩ መልእክት የማያስተላልፉት አሳባቸውን በአግባቡ ስለማያቀናጁ ነው። አብዛኞቹ መረጃዎች በጥሩ ሁኔታ የሚተላለፉት በተወሰነ ቅደም-ተከተል ነው። ከአንድ አሳብ እንጀምራለን። እርሱም ወደ ሌላው ይወስደናል። ነገር ግን ቅደም-ተከተሉ ከተዛባ፣ ሰዎች ግራ ይጋባሉ። መረጃችንን ካላቀናጀንና እንዴት እንደምናስተላልፍ ካልተዘጋጀን፣ ምንም ጠቃሚ ነገር ሳንናገር ጊዜያችንን እናባክናለን። ሰዎች አስፈላጊ ያልሆኑትን ነገሮች ስንናገር በሚሰሙበት ጊዜ፣ ማዳመጣቸውን ያቆማሉ። ሁላችንም የሰባኪውን መልእክት ሰምተን ስናበቃ መልእክቱ ምን እንደ ነበረ ለመረዳት የተቸገርንባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ይህ አሳቡ በሚገባ አለመቀናጀቱን የሚያሳይ ምልክት ነው።

መ. ረዣዥምና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ወይም አሳቦች፦ ለጥሩ ተግባቦት ቀላል ዓረፍተ ነገሮችንና አሳቦችን መጠቀም አለብን። ረዣዥም ዓረፍተ ነገሮችን የምንጠቀም ከሆነ፣ ወይም ከባባድ አሳቦችን ብንጠቀምና ሰዎች ለመከታተል ከተቸገሩ፣ አሳባችንን በተሳሳተ መንገድ ሊረዱ ይችላሉ። ኢየሱስ እጅግ የተዋጣለት መልእክት አስተላላፊ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ እውነቶቹን አጫጭርና ቀላል አድርጎ በማቅረብ ምንም ዓይነት ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ጭምር መልእክቱን እንዲረዱ በማድረጉ ነው።



ሠ. በሚናገሩበት ጊዜ ሰውን ቀና ብሎ አለመመልከት፦ በሚናገሩበት ጊዜ ማኅበረ ምእመኑን ቀና ብለው ለመመልከት የማይደፍሩ ብዙ ሰባኪዎች አጋጥመውናል። ወደ መስኮቱ ወይም ወደ ወለሉ እየተመለከቱ ወይም ጽፈው የመጡትን ማስታወሻ እያነበቡ ስብከታቸውን ያካሂዳሉ። ሰባኪዎች ወደ እኛ የማይመለከቱ ከሆነ፣ አድማጩ በሚናገሩት ነገር ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመቆየት ይቸገራል። ተናጋሪው አድማጮቹን ፊት ለፊት በሚመለከትበት ጊዜ፣ «ይህ ለእናንተ በጣም አስፈላጊ ነገር ነውና አድምጡኝ» የሚል ያልተነገረ መልእክት ይተላለፋል። እንዲሁም ደግሞ አድማጩ በቀጥታ ከተናጋሪው ጋር የአሳብ ልውውጥ እያደረግኩ ነኝ ብሎ ያስባል።

ረ. በጣም ዝቅ ወይም በጣም ከፍ ባለ ድምጽ መናገር፦ እግዚአብሔር የተለያዩ ድምጾችን ሰጥቶናል። አንዳንድ ድምጾች በቀላሉ ሊደመጡ ሲችሉ፣ ሌሎች ደግሞ ለስላሳና በቀላሉ ሊደመጡ የማይችሉ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ያለ ድምጽ የትሕትና ምልክት ነው ብለን እናስባለን። ነገር ግን ሰዎች ሊሰሙን ካልቻሉ፣ ለብዙ ጊዜ ቀልባቸውን ሊሰጡን አይችሉም። አንድ ሰው ድምጹን በጣም ዝቅ አድርጎ በሚናገርበት ጊዜ፣ አድማጩ ቁልፉን ቃል ወይም ዓረፍተ ነገር ሳይሰማ ይቀርና የተነገረውን አሳብ ሳይረዳ ይቀራል። በሕዝብ ፊት ቆሞ አንድ ነገር መናገር የአሳብ ልውውጥ ላይሆን ይችላል። የአሳብ ልውውጥ ሊካሄድ የሚችለው አድማጩ የተናገርነውን አሳብ ሰምቶ ሲረዳ ነው። ስለሆነም፣ ሰዎች ያለ ምንም ችግር እንዲሰሙን ድምጻችንን ከፍ አድርገን መናገር አለብን።

ድምጽን ከመጠን በላይ ከፍ አድርጎ መናገሩም ጥሩ አይደለም። ሰዎች እየጮህንባቸው ከመሰላቸው፣ ወይም ድምጽ ማጉያው በጣም የሚጮህ ከሆነ፣ የምንናገረውን ቃል ለማዳመጥ ይቸገራሉ። ማናችንም ብንሆን ሰው እንዲጮህብን አንፈልግም። ስለሆነም፣ ሰዎች እንዲሰሙ በሚያመች የድምጽ መጠን መናገር አለብን። የእግዚአብሔር ቃል ኃይል በእኛ ጩኸት ላይ አይደገፍም።

ምእመናን አሳባቸው ሳይባዝን የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙና ሲረዱ፣ ቃሉ ሕይወታቸውን ይለውጣል።

ሰ. ሰዎች ስሜታችንን እንዲያዩ አለማድረግ:- ስሜታችንን ካልገለጽን፣ ሰዎች የምንናገራቸውን ነገሮች ለመስማት ይቸገራሉ። ምንም ዓይነት ስሜት ሳናሳይ ለረዥም ጊዜ በአንድ ዓይነት ድምጽ የምንናገር ከሆነ፣ ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ማዳመጣቸውን ያቆማሉ። ድምጻችንን በመቀያየር፣ ቆም በማለት፣ ከፍና ዝቅ በማድረግ አድማጫችንን ይዘን ልንጓዝ እንችላለን። በፊታችን ገጽታ፣ በእጆቻችን በምናከናውናቸው ነገሮች፣ ወዘተ. . . መደሰታችንን ልናሳይ እንችላለን።

ሸ. በቂ መረጃ ስለማንሰጥ፣ ሰዎች ምን ለማለት እንደ ፈለግን ለመገመት ይገደዳሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ማስታወቂያ በሚናገሩበት ጊዜ ሕዝቡ ቀድሞውኑ መቼ መገናኘት፣ የት መገናኘት፣ ምን ምን ነገሮችን ማምጣት እንዳለበት፣ ወዘተ. . . የሚያውቅ ይመስላቸዋል። ሁልጊዜም ሕዝቡ ሁሉንም መረጃ እንደማያውቅ በመገመት ግልጽ፣ እጥን ምጥን ያለና የተሟላ መረጃ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ትግበራው ወይም አስከትሎቱ ግልጽ ይሆን ዘንድ ነገሮችን ማብራራቱ ተገቢ ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ሰባኪዎች በሚሰብኩበት ጊዜ፣ አንድን አሳብ ለማብራራት ብዙ ጊዜ ይወስዳሉ። ከዚያም የሚከተለውን በሚመስሉ ዓረፍተ ነገሮች ስብከታቸውን ይጨርሳሉ:- «ይህ ከእናንተ ጋር እንደሚዛመድ ታውቃላችሁ።» ነገር ግን ብዙ ሰዎች እውነቱ ከእነርሱ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ለማሰብ ጊዜ አይወስዱም። ስለሆነም፣ ሰባኪው ወይም አስተማሪው የቀረበው እውነት ከሕዝቡ ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማሳየት አለበት።

ቀ. የግል መልእክቶችን ከምስባኩ በማስተላለፍ የምእመናንን ጊዜ ማባከን ተገቢ አይደለም። ከእነርሱ ጋር የማይገናኝ ብዙ መረጃ በሚነገራቸው ጊዜ፣ ሰዎች ይናደዳሉ። ስለዚህ፣ ለአብዛኛው ምእመናን የማይጠቅሙ መልእክቶች በተለየ መንገድ ወደ ተፈለጉት ሰዎች እንዲደርሱ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል። መልእክቱን ለምእመናን ሁሉ ከመናገሩ በፊት፣ «ወንጌላውያንን ወይም



መዘምራንን ለአጭር ጊዜ ለማነጋገር ስለምፈልግ እባካችሁ ከዚህ ስብሰባ በኋላ ወደ ኋላ ቅሩልኝ» ማለቱ የተሻለ ነው። በዚህ ጊዜ የሁሉም ምእመናን ጊዜ አይባክንም። የተፈለጉትም ሰዎች መረጃውን ያገኛሉ።

በ. አንድ መሪ አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በሚናገርበት ሰዓት ጊዜን ያባክናል። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ መልእክት የማስተላለፍ ዕድሎቻችንን በማስተዋል መጠቀም አለብን። ከአምልኮው በኋላ ወደ ኋላ እንዲቀሩ ጠይቀናቸው ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆነ ነገር በምንናገርበት ጊዜ፣ ሰዎች ደስ ሊሉኝ አይችሉም። ይህ ጊዜ ማባከን ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሱ፣ በሌላ ጊዜ ጠቃሚ ጉዳይ ኖሮን ብንጠራቸው አይገኙልንም። ነገር ግን ሕዝቡ ሁልጊዜም የምንናገረው ነገር ጠቃሚ መሆኑን ካረጋገጠ፣ ወደ ኋላ እንዲቀር በሚጠየቅበት ጊዜ ሁሉ ለመቅረት ጥረት ያደርጋል። ሕዝቡ የተነገረውን ማስታወቂያ ችላ ብሎ መሄዱ፣ መሪዎች ምእመናን ለመስማት የሚፈልጓቸውን ጠቃሚ ነገሮች እንደማያካፍሉ ሊያመለክት ይችላል።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ:- ላለፉት ሦስት እሑዶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሰማሃቸውን ስብከቶች አስታውስ። ሀ) ስለ ጥሩ የአሳብ ልውውጦች ከተነገሩት ነጥቦች ሰባኪዎቹ የተጠቀሙባቸው የትኞቹ ናቸው? ያልተጠቀሙባቸውስ? ይህ ስብከቱን የመስማት ችሎታህን የገደበው እንዴት ነበር? ለ) እንዴት በተሻለ ሁኔታ ስብከቱን ሊያቀርብ ይችል ነበር? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምትናገርበት ጊዜ ካለ፣ አንድ ጓደኛህ የትኞቹን የተለመዱ የሕዝባዊ ተግባቦት ስሕተቶችን እንደ ፈጸምክ እንዲነግርህ ጠይቅ። |

### ሦስተኛ ቀን

### በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት መልእክትን ማስተላለፍ እንደሚቻል

አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን አመራር በመልእክት ልውውጥ (በተግባቦት) አማካኝነት የሚከናወን መሆኑን ተመልክተናል። የእግዚአብሔር በጎች «እረኞች» እንደ መሆናችን መጠን፣ ግለሰባዊ መልእክቶችን በማስተላለፍ ሰዎችን በማበረታታት፣ በመገሠጽ፣

በመምከርና በመስተማር ወደ እግዚአብሔር መንገድ የምንመልስባቸው ጊዜያት አሉ:: በኮሚቴዎችና በቦርዶች ተሰባስበን ለእግዚአብሔር መንግሥት ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለማከናወን የምንጥርባቸው ጊዜያትም አሉ:: መጀመሪያ የማዳመጥንና ከዚያ በኋላ የመናገርን የሁለት ደረጃዎች ሂደት ተጠቅመን ሰዎችን ለመርዳት እንሞክራለን::

ይፋዊ ተግባቦት ግን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናን እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ለማስቻል የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው:: ምእመናን እግዚአብሔርን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲያመልኩና እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ዓይነት ሰዎች እንዲሆኑና እርሱ የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንደያደርጉ ለማስቻል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የይፋዊ ተግባቦት ክህሎትን ሊማሩ ይገባል:: ከዚህ በታች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሕዝባዊ ተ ግባቦት ክህሎታቸውን በመጠቀም የመልእክት ልውውጥ ሊያካሂዱ የሚችሉባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ቀርበዋል::

1. የአምልኮና የቡድን ዝማሬን መምራት:-

ወደ አንድ ግሩም ግብዣ ተጠርተህ መጥተሃል እንበል:: ነገር ግን በግብዣው ሰፍራ መጀመሪያ የጎረስከው ከተበላሸው ወጥ ነው እንበል:: ያ የተበላሸው ወጥ ፍላጎትህን ስለሚዘጋው፣ ሌላውን ግሩም ምግብ በደስታ ሳትመገብ ትቀራለህ:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አምልኮውን የሚመራው ሰው ከታላቁ አምላካችን ጋር ጥሩ ግንኙ ነት እንድናደርግ ወይም እንዳናደርግ የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይችላል:: የፕሮግራሙ መሪ በሚገባ ካልተዘጋጀና ቅዱሱ አምላካችንን በሚገባ እንድናመልክ ካልረዳን፣ የአምልኮ ጊዜያችን የምንፈልገውን ያህል በበረከት የተሞላ ላይሆን ይችላል:: አምልኮ እንደ ትንሽ ጉዳይ ታይቶ ወጣቶች ብቻ እንዲያዘጋጁት መደረግ የለበትም:: የአምልኮው መሪዎች በጥንቃቄ ተመርጠው ሊሠለጥኑና በክህሎት ፕሮግራሙን ሊመሩ ይገባል:: ስዎች አምልኮን በሚመሩበት ጊዜ የሚከተሉትን እውነቶች ማስታወሱ ጠቃሚ ነው:-



ሀ. የእሑድ አምልኮ ዓላማ በአንድነት ለእግዚአብሔር ውዳሴ ማቅረብና እግዚአብሔርም በቃሉ ሲናገረን መስማት ነው:: ይህ በቀዳሚነት ስሜታችንን ለመግለጽ የምንሰባሰብበት አይደለም:: የአምልኮ መሪው ቀዳሚ ጥያቄ፣ «ምእመናን እግዚአብሔርን በዝማሬ እንዲያከብሩትና በመካከላችን ያለውን አምላክ ይሰሙ ዘንድ ምን ማድረግ እችላለሁ?» የሚል ሊሆን ይገባል:: ከእግዚአብሔር ይልቅ በሌሎች ነገሮች ላይ ትኩረት እንድናደርግ የሚያደርግ ማንኛውም ነገር ይህንን ግብ የሚያደናቅፍ መሆኑ መታወቅ አለበት::

ለ. አምልኮ አስደሳች የሚሆነው የተለያዩ ነገሮች የተካተ ቱበት እንደ ሆነ ነው:: ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በምናነብበት ጊዜ የድልና የደስታ መዝሙሮችን ብቻ ሳይሆን፣ የንስሐ፣ የምስጋናና የአምልኮ መዝሙሮችንም ማንበብ አለብን:: በመሆኑም፣ የአምልኮ መሪው ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዴት ራሳቸውን የሚያነጹበትን መንገድ ለማመቻቸት በጥንቃቄ ማቀድ አለበት:: ከዚያም ሰዎች ታላቁ አምላካችንን በማምለክ፣ ላደረጋቸው ነገሮች እርሱን በማመስገንና እርሱን ለመስማት በመዘጋጀት ላይ እንዲያተ ኩሩ ለማድረግ የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባብ፣ መዝሙሮችና ጸሎቶች ማዋሃድ አለበት::

ሐ. የትኩረታችን እምብርት መሆን ያለበት ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው:: የአምልኮው መሪው ምእመናን በእርሱ፣ በመዘምራን ወይም በሰባኪው ላይ ትኩረት እንዳያደርጉ መጠንቀቅ አለበት:: አገልጋዮች ሰዎች ልባቸውን እንሥተው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና እንዲያዳምጡ የሚያግዙ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም::

መ. አምልኮ የሁሉም ሰው ንብረት እንጂ የጥቂቶች ብቻ አይደለም:: ስለሆነም፣ መዘምራኑ የመዝሙሩ እምብርት ከሚሆኑ ይልቅ፣ ምእመናን ሁሉ በመዝሙር አማካኝነት አምልኮአቸውን መግለጽ ይኖርባቸዋል:: አንዳንድ ወጣቶች ብቻ የሚያውቋቸውን መዝሙሮች ከመዘመር ይልቅ፣ የአምልኮ መሪው፣ «ሁሉም ሰው በአንድነት እግዚአብሔርን በደስታ እንዲያመልክ ምን ባደርግ

ይሻላል?» የሚል ጥያቄ ማንሣት አለበት። በአብዛኛው የአምልኮ መሪዎች ከእነርሱ በስተቀር ማንም ሰው የማያውቃቸውን መዝሙሮች ይመርጣሉ። ይህ ሌሎች በአምልኮው ደስ እንዲሰኙ አያግዛቸውም። በአመዛኙ አምልኮው የሚያተኩረው ወጣቶችን በማስደሰቱ ላይ ነው። ፍቅር ካለ፣ የሁሉም ሰው የአምልኮ ፍላጎት ሊከበርለት ይገባል። (ለምሳሌ፣ አንዳንድ አዛውንቶች አንዳንድ የድሮ መዝሙሮችን መዘመር የሚፈልጉ ከሆነ፣ የአምልኮ መሪዎች አንዳንድ ጊዜ የድሮ መዝሙሮችን በማዘመር ለአዛውንቶች ያላቸውን ፍቅር መግለጽ ይኖርባቸዋል።)

ሠ. የአምልኮ መሪው ሁልጊዜም ነገሮችን በተለየ መንገድና በአንድ ዓይነት መንገድ ለማከናወን ከመፈለግ መቆጠብ አለበት። ብዙ አዳዲስ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ብናስተዋውቅ፣ ምእመናን በአዲሶቹ ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ እግዚአብሔርን በሚገባ ላያመልኩ ይችላሉ። ብዙ አዳዲስ መዝሙሮችን ማቅረብ የሕዝቡን የማምለክ አቅም ይገድባሉ። በፕሮግራሙ አደረጃጀት ላይ የሚታዩ ብዙ አዳዲስ ነገሮችም ምእመናን ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘቱ ላይ ሳይሆን፣ በአዳዲሶቹ ነገሮች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይገፋፉአቸዋል። በሌላ በኩል፣ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ነገሮች የሚደረጉ ከሆነ፣ ምእመናን ትርጉሙን ከማሰብ ይልቅ መዝሙሮቹን በልማድ ብቻ ሊዘምሩ ይችላሉ። ይህ በተለይ የሕዝቡን ስሜት ለማነሣሣት ሊባል አንድ ዓይነት መዝሙር ሁሌ በሚዘመርበት ጊዜ የሚያጋጥም ችግር ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሰዎች ስለ ትርጉሙ ሳያስቡ መዝሙሩን በልማድ ወደ መዘመሩ ሊገቡ ይችላሉ (ማቴ. 6:7)። ስለሆነም፣ ሰዎች የቃላቱን ትርጉም በማሰብ ከልባቸው እንዲዘምሩ ለማስቻል የአምልኮ መሪዎች የተለያዩ መዝሙሮችን መጠቀም አለባቸው።

ረ. አምልኮ ልክ እንደ እግር ኳስ «የቡድን» አገልግሎት ነው። ማንኛውም አንድ ተጨዋች ሁልጊዜም ኳሱን ለብቻው ይዞ ሊቆይ አይችልም። ነገር ግን ቡድኑ እንዲያሸንፍ ለማስቻል እያንዳንዱ ተጫዋች የየራሱ ኃላፊነት አለው። የአምልኮው መሪና ሙዚቀኞቹ ተባብረው ካልሠሩ፣ የአምልኮው መንፈስ ይረበሻል።



የአምልኮ መሪው አዲስ መዝሙር ቢመርጥና ሙዚቀኞቹ ቅኝቱን ለማግኘት ብዙ ደቂቃ የሚፈጅባቸው ከሆነ፣ የሕዝቡ የአምልኮ ፍላጎት ይቀንሳል። ወይም ደግሞ የአምልኮ መሪው አንድን መዝሙር ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ ቢጀምርና በተደጋጋሚ እንደገና ለመጀመር ቢገደድ፣ የሕዝቡ ትኩረት ከመዝሙሩ ይልቅ ወደ ተደጋጋሚው ትእይንት ይቀለበሳል። እንዲህ ዓይነት ችግሮችን ለማስወገድ የአምልኮ መሪውና የሙዚቃ ተጫዋቾቹ ቀደም ብለው አብረው ቢለማመዱ መልካም ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሙዚቃ ተጫዋቾቹ የትኞቹን መዝሙሮች እንደሚጫወቱ ስለሚያውቁ፣ ቅኝቱን አዘጋጅተው ሊቆዩ ይችላሉ። ይህም በአምልኮው ፕሮግራም ላይ ሙከራ ሲያደርጉ ከመዋል ይልቅ ቀድሞውኑ ተዘጋጅተው ወዲያውኑ መዝሙሮቹን ለማስጀመር እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

ሰ. የአምልኮ መሪውና ሙዚቀኞቹ የድምጽ ማጉያው የመዝሙሮቹን ቃላት እንዲያሰማ አድርገው ማዘጋጀት አለባቸው። ድምጽ ማጉያው ወይም ኪቦርዱ በጣም ከፍ ብሎ የሚጮህ ከሆነ፣ የመዝሙሮቹን ቃላት ለመስማት አስቸጋሪ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ትኩረት የሚያደርገው አምልኮውን በሚገልጹት ቃላት ላይ ሳይሆን፣ በአምልኮ መሪው ላይ ይሆናል። ይህ በተለይ ሶሎ ዘማሪ ወይም መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ የሚከሰት ነገር ነው። ሙዚቃው ከሚዘመረው መዝሙር ከፍ ካለና ሕዝቡ ቃላቱን መስማት ካልቻሉ፣ አምልኮ ማካሄድ አይቻልም። እውነተኛ አምልኮ ሊካሄድ የሚችለው ሕዝቡ የመዝሙሩን ቃላት ሲሰሙ ነው። የመዝሙሩን ቃላት በሚሰሙበት ጊዜ እነዚያ ቃላት እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚጠቀሙባቸው የራሳቸው ቃላት ይሆናሉ። በመሆኑም፣ የአምልኮ መሪውና ሙዚቀኞቹ ድምጽ ማጉያውን በጥሩ ሁኔታ ማስተካከል ይኖርባቸዋል። ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከኋላ ቁጭ ብሎ ድምጽ ማጉያውንና ኪቦርዱን ለሚቆጣጠረው ሰው ምልክት በመስጠት ድምጹ ከፍ ወይም ዝቅ ማለቱን በምልክት እንዲያሳይ ቢደረግ መልካም ይሆናል።

19ኛ ጥያቄ፦ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስለሚካሄድ አምልኮ አስብ። ሀ) እነዚህ መርሖዎች የአምልኮ መሪዎች በክህሎት በመምራት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የአምልኮ ልምምድ ሊያሳድጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ አምልኮ ለሁሉም ሰው መልካም ይሆን ዘንድ ሌሎች ምን ዓይነት ነገሮች ሊደረጉ ይገባል ትላለህ?

2. ማስታወቂያዎችን መናገር፦

ማስታወቂያዎችን መናገር ለመሪዎች አጋዥ መሣሪያ ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ይህ ብዙውን ጊዜ አጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው። ሰዎች ማስታወቂያውን ሳይሰላቹ ሰምተው እንዲጨርሱ ማድረጉ አስቸጋሪ ነው። በየትኛው ሰዓት ላይ ማስታወቂያ መናገር እንዳለብን ማወቁም አስቸጋሪ ነው። ቀደም ብለን በአምልኮው ሰዓት ላይ ብንናገር፣ አንድም ሁሉም አማኞች ላይደርሱልን ይችላሉ፣ አሊያም የአምልኮውን መንፈስ ሊረብሽ ይችላል። ወደ መጨረሻው አካባቢ ብንናገር ደግሞ፣ ብዙዎቹ ሰዎች ለመሄድ ስለሚጣደፉ ማስታወቂያውን በደንብ ላይሰሙት ይችላሉ። ይህንን ጊዜ በጥንቃቄ ካልተቆጣጠርን፣ ሰዎች ላይሰሙን እና አጅግ ጠቃሚ የሆኑ ማስታወቂያዎች ሊያመልጧቸው ይችላሉ።

የማስታወቂያ ጊዜን ስለ መጠቀም ከዚህ በታች አንዳንድ ጠቃሚ አሳቦች ቀርበዋል።

ሀ. በተቻለ መጠን በአምልኮ ጊዜ ጥቂት ማስታወቂያዎችን ብቻ መናገር። ለተፈለጉት ሰዎች ማስታወቂያዎችን በሌሎች መንገዶች ማዳረስ። (ለምሳሌ፣ ስብሰባ መኖሩን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ አንዱ ኮሚቴ ለሌላው ሊናገር ይችላል።) ዕቅዶችን አውጥተን ቀደም በማለት ለሕዝቡ ከገለጽን፣ አብዛኞቹ ማስታወቂያዎች አስፈላጊዎች ላይሆኑ ይችላሉ።

ለ. ሁሉንም ምእመናን የሚመለከቱትን ጉዳዮች ብቻ በማስታወቂያ መልክ መናገር።

ሐ. በተቻለ መጠን ማስታወቂያዎችን አጭር ማድረግ። ብዙ አላስፈላጊ መረጃዎችን መስጠቱ አስፈላጊ አይሆንም። ምእመናን ማስታወቂያ በምንናገርበት ጊዜ ወሳኝ የሆኑትን ብቻ እንደምንናገር



ካወቁ፣ «እባካችሁ ማስታወቂያውን ሳትሰሙ አትውጡ» ብለን መለመን ሳያስፈልገን ራሳቸው በፍላጎት ይሰማሉ።

መ. ሰዎች ቀደም ብለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲነገርላቸው የሚፈልጉትን ማስታወቂያ እንዲያቀርቡ ማድረግ። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስታወቂያዎቻቸውን የሚጽፉት ማስታወቂያ ተናጋሪው ግለሰብ ተነሥቶ ሊቆም ሲል ነው። ማስታወቂያ ተናጋሪው ቀደም ብሎ ሁሉንም መረጃ ቢያገኝ፣ አምልኮው ከመጀመሩ በፊት ማብራሪያ ሊጠይቃቸው ይችላል። መረጃዎቹን ማወቁ በፍጥነትና ሕዝቡን በማያሰለች መንገድ የሚያቀርብበትን ዘዴ እንዲፈልግም ያስችለዋል። ነገር ግን የሚዘጋጅበት ጊዜ ከሌለው፣ ማስታወቂያው የሚነገርበት ጊዜ ከሚፈለገው በላይ ሰዓት የሚወስድ ሊሆን፣ ትክክል ያልሆኑ መረጃዎችንም ሊያስተላልፍ ይችላል።

ሠ. ማስታወቂያዎችን በምትሰጥበት ጊዜ ፈጠራን ተጠቀም። ማስታወቂያ የሚሰጥበትን ጊዜ በመጠቀም ምእመናን በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ደስ እንዲሰኙ አድርግ። በልዩ አገልግሎቶች ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ በማድረግ ሌሎች ምእመናን እግዚአብሔር በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ እያከናወነ ያለውን ተግባር እንዲገነዘቡ አድርግ። አገልግሎቱን የሚያካሂዱ ሰዎች ከሌሎች በተሻለ ፍላጎትና ስሜት ስለሚያከናውኗቸው ነገሮች ሊናገሩ ይችላሉ። ወይም ደግሞ አንድ አስፈላጊ ስብሰባ የተዘጋጀበትን ምክንያት ለማብራራት ድራማ መጠቀም ይቻላል። ማስታወቂያዎች በፈጠራ ክህሎቶች ታግዘው በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ሰዎች በደስታ ይከታተላሉ። የሚያሰለቻቸው የተለመደው ዓይነት የማስታወቂያ አቀራረብ ነው።

ረ. ማስታወቂያ ተናጋሪው በዚህ በኩል ክህሎት ያለው መሆን አለበት። ብዙ ሰዎች ይህን የማስታወቂያ ሰዓት ስለሚጠሉ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአስደሳች መንገድ ማስታወቂያዎች የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አለባቸው። በአንድ ዓይነት አስልቺ ድምጽ የሚናገሩ ሰዎች ማስታወቂያ መናገር የለባቸውም።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስታወቂያ በመናገሩ በኩል ስጦታ ያለውን ሰው ፈልገው ሊጠቀሙበት ይገባል::

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙ ሰዎች ማስታወቂያ የሚነገርበትን ሰዓት የሚጠሉት ለምን ይመስልሃል? ለ) ባለፈው እሑድ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተነገሩትን ማስታወቂያዎች አስታውስ:: ሰዎች መረጃውን ሰምተው ያስታውሱ ዘንድ የማስታወቂያን ጊዜ የበለጠ አስደሳች ለማድረግ ምን መደረግ አለበት ትላለህ?

3. ማስተማር ወይም መስበክ:-

> 21ኛ ጥያቄ:- ያዕ. 3:1-2ን አንብብ:: ሀ) ያዕቆብ ለአስተማሪዎች የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ለ) ለሰባኪዎች ይህ ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) የዚህን ምንባብ ማስጠንቀቂያዎች ብናውቅ፣ ለስብከት ያለን አመለካከት እንዴት የሚቀየር ይመስልሃል?

ለቤተ ክርስቲያን መሪ (ሽማግሌ፣ ሰባኪ፣ አስተማሪ) የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈል ልዩ ዕድል ነው:: ነገር ግን ትልቅ ኃላፊነትም አለው:: በያዕቆብ 3:1-2 ብዙ ሰዎች ይህንን ታላቅ አገልግሎት ማካሄድ እንደሌለባቸው የሚጠይቅ ክፍል አለ:: በአምልኮአችን ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለመናገር ይፈልጋል:: ነገር ግን ይህንን የሚያደርገው በቀጥተኛ መንገድ ሳይሆን፣ በዕለተ እሑድ በሚቀርብ ስብከት አማካኝነት ነው:: ሰባኪዎቹ እግዚአብሔርን ወክለው ስለሚናገሩ፣ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች የሚያቀርቡትን መልእክት በጥንቃቄ ማስተላለፍ አለባቸው::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ለማስተላለፍ የምንፈልገው መልእክት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን:: ቃሉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም እግዚአብሔርን በትክክል ሳንወክል ብንቀር፣ እውነተኛ ያልሆኑትን የተሰፋ ቃሎች በእግዚአብሔር ስም ልንሰጥ እንችላለን:: ለምሳሌ ያህል፣ የእግዚአብሔር ቃል በማይናገረው መንገድ ሰዎች ፈውስ ወይም አካላዊ በረከቶችን እንደሚያገኙ አድርገን ብንናገር፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለማድረግ የሚፈልገውን ነገር በትክክል አላቀረብንም ማለት ነው:: ብዙ አማኞች ሰባኪዎች ከእግዚአብሔር ነው በሚል የተሳሳቱ የተስፋ ቃሎችን ስለሚሰጧቸው ይናደዳሉ:: አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የላከው አምባሳደር የውሸት የተስፋ ቃል ለተላከበት አገር ቢናገር፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደስ ሊለኝ አይችልም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድ ሰባኪ የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ መንገድ ቢተረጉም፣ እግዚአብሔ ርም በስሙ የውሸት የተስፋ ቃል በመስጠቱ መቆጣቱ የማይቀር ነው::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሰዎች እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመስማት እንዲፈልጉ ለማስቻል ክህሎት ያለው የአሳብ ልውውጥ መጠቀም አለብን:: መልእክታችን የቀረበው በሚያሰለች ወይም ግልጽ ባልሆነ መንገድ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በእኛ በኩል ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ወደ ሰዎች ሳይደርስ ይችላል:: ሰባኪዎች የእግዚአብሔ ርን ቃል በክህሎት ለማስተላለፍ ጥረት ካላደረጉ፣ የማስናከያ ዓለት በመሆን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መልእክት በተሳሳተ መንገድ እንድትረዳ ልናደርግ እንችላለን:: መንፈስ ቅዱስ ድካማችንን በማለፍ ክህሎት በሌለው ሰባኪ አማካኝነት ሳይቀር ሊናገር እንደሚችል እውነት ነው:: ነገር ግን የሕዝባዊ ተግባቦት ክህሎታችንን ባለማዳበራችን ምክንያት ለብዙ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ልናደናቅፍም እንችላለን:: የአንድ አገር መሪ መልእክቱን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለማስተላለፍ በሚፈልግበት ጊዜ መልእክቱን በትክክልና ደስ በሚያሰኝ መንገድ ሊናገር የሚችል ባለሥልጣን መምረጡ የማይቀር ነው:: እኛም የነገሥታትን ንጉሥ ወክለን በምንናገርበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክልና ለዛ ባለው መንገድ ልናቀርብ ይገባል::

እግዚአብሔርን ወክለው የሚያስተምሩ ሰዎች ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ለመሆን በሚዘጋጁበት ጊዜ ሊያስታውሱ የሚገባቸው አንዳንድ ነገሮች ከዚህ በታች ተመልክተ ዋል::

ሀ. መልካም የአሳብ ልውውጥ ለማካሄድ አድማጮቻችን ምን ዓይነት ሰዎች እንደ ሆኑ ማወቅ አለብን::

አገልጋይ መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ትኩረት ማድረግ ያለብን ጥሩ ንግግር በማቅረባችን ሳይ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ምን ያህል እንደሚረዱ ጭምር ነው:: የመልእክታችን ትልቁ ውጤታማነት ሰዎች የቀረበላቸውን አሳብ ተረድተው ተግባራዊ በማድረጋቸው ሳይ የተመሠረተ ነው:: ስለሆነም፣ በምንናገርበት ጊዜ ሁልጊዜም መልእክቱን ስለሚቀበሉት ሰዎች ማሰብ አለብን::

1) መልእክታችንን የሚቀበሉት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ወጣቶች ናቸው? ከሆነ፣ ማብራሪያዎችን ማቅረብ ወይም ወጣቶች አሳቡን ተረድተው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በሚነሣሡበት መንገድ ማቅረብ አለብን:: የገጠር ሰዎች ናቸው? ከሆነ፣ እንደ ኤሌክትሪሲቲ፣ የከተማ አውቶቡሶች ወይም ሌሎች በከተማ ውስጥ ብቻ ስለሚገኙ ነገሮች በመናገር ማብራሪያ ለመስጠት መሞከሩ እርባና አይኖረውም:: ያልተማሩ ሰዎች ናቸው? እንዲህ ከሆነ፣ ለመረዳት ስለማይችሏቸው ውስብስብ ነገሮች መናገር የለብንም::

በ1ኛ ቆሮንቶስ 9:19-23 ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሆኖ በሚናገርበት ጊዜ ሰዎች አሳቡን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ለማገዝ የመልእክቱን ተቀባዮች መስሎ እንደሚቀርብ ገልጾአል:: ለአይሁዶች እንደ አይሁዳዊ፣ ለግሪክ ሰዎች ደግሞ ልክ ግሪካዊ መስሎ ይናገራል:: ጳውሎስ ለአይሁዶች በሚናገርበት ጊዜ ሁልጊዜም ከብሉይ ኪዳን ምንባቦችን ሲጠቅስ እንመለከታለን:: ለአሕዛብ በሚናገርበት ጊዜ ግን ስለ ፍጥረት ይናገራል:: ከታወቁት ገጣሚያን ሥራዎችም የጠቀሰባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ (የሐዋ. 17:22-31):: ጳውሎስ ይህንን ሲያደርግ የወንጌሉን መልእክት አልቀየረውም:: ነገር ግን እንደ ሰዎቹ ሁኔታ የወንጌሉን መልእክት እንዲረዱት አድርጎ ያብራራላቸው ነበር:: ብዙውን ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች በቅርብ ጊዜ የተመረቁ አገልጋዮች ስብከት በሚያቀርቡበት ጊዜ ይህንን መሠረታዊ መርሖ ይዘነጋሉ:: ከዚያም ሰዎች ለምን በትምህርታቸው እንዳልተደሰቱ በማሰብ ይገረማሉ:: እነዚህ ምሩቃን ያዘጋጁትን ትምህርት ቢናገሩም፣ እንዴት አሳባቸውን ለአድማጮቻቸው እንደሚገልጹ አሳወቁም::



2) ሕዝቡ ስለ ተነሣው ጉዳይ የሚያውቁት ነገር ምንድን ነው? ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ትምህርት የተሰጣቸውና አሁን የሚነገረውን አሳብ የሚረዱ ናቸው? (ለምሳሌ፣ የደኅንነት ወይም የጥምቀት ትምህርት):: እንደዚያ ከሆነ፣ ተጨማሪ አሳቦችን ልናካፍላቸው እንችላለን:: ነገር ግን የቀረበው አሳብ ለእነርሱ አዲስ ከሆነ፣ የሚነገረውን ነገር እንዲረዱ ለማገዝ ረጋ ብሎ ማስተማሩ አስፈላጊ ነው:: (ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር የሰውን ልጆች መከራ የሚያይባቸው መንገዶች::)

3) ሕዝቡ በተነሣው ርእሰ-ጉዳይ ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ዓይነት ነው? ርእሰ-ጉዳዩን የሚወዱት ከሆነ፣ የቀረበውን አሳብ እንዲረዱና እንዲቀበሉ ማድረጉ ከባድ አይሆንም:: ነገር ግን ርእሰ-ጉዳዩን የማይወዱት ከሆነ፣ ማስተማሩ አስቸጋሪ ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል፣ በቤተ ክርስቲያኖቻችን ስለ በረከት በምናስተምርበት ጊዜ ሰዎች በቀላሉ በደስታ ጦፈው «አሜን!» ማለት ይጀምራሉ:: በተቃራኒው ለክርስቶስ መከራ ስለ መቀበል ስናስተምር፣ ሰዎች ይህን አሳብ ለመቀበልና አኗኗራቸውን ለመቀየር ይቸገራሉ::

4) አንተን እንደ ተናጋሪ የሚያዩህ እንዴት ነው? የተማርክ ስለሆንክ ያከብሩሃል? ሊሰሙህስ ይጓጓሉ? ወይስ እነርሱ የሚንቁት ጎሳ አባል ነህ? ሰዎች እንዴት እንደሚመለከቱን አስቀድመን ካወቅን፣ ተቀባይነትን ለማግኘት ምን ያህል መሥራት እንዳለብን እናውቃለን:: ሰዎች ምን እውቀት አለውና ያስተምረናል? የሚል ግምት ካላቸው፣ ሊሰሙን አይችሉም:: ስለሆነም፣ ሊሰሙት የሚገባ መልእክት ይዘን እንደ መጣንላቸው ማሳመን አለብን::

5) የሰዎቹ ግንኙነት ምን ይመስላል? በመካከላቸው መከፋፈልና ጸብ አለ? ይህ እግዚአብሔርን ለመስማት ልባቸውን እንዳይከፍቱ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል:: ነገር ግን አንድነትና እግዚአብሔርን የመስማት ፍላጎት በመካከላቸው ካለ፣ የእግዚአብሔርን እውነት ማካፈሉ ቀላል ነው::

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለከተማና ገጠር ሰው የምትጠቀምባቸውን የተለያዩ ዓይነት ምሳሌዎች ግለጽ:: ለ) ክህሎት ያላቸው ሰዎች የአድማጮቻቸውን ቀልብ በመሳብ እንዴት የመደመጥን ፍላጎት ሲያሳድሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: |

ለ. ተናጋሪው የሕዝቡን ፍላጎትና ትኩረት በማግኘት መልእክቱን መጀመር አለበት:: ሁሉም ሰዎች አዲስ ነገርን የመቃወም ተፈጥሯዊ ባሕርይ ይዘው ይገኛሉ:: ከዚህም በላይ አሳባቸው በተለያዩ የግል ጉዳዮች ይጣበባል:: ስለዚህ፣ አንድ ተናጋሪ ማድረግ ያለበት የመጀመሪያው ነገር የሕዝቡን ቀልብ መያዝ ነው:: ለመስማት እንዲፈልጉ ለማነሣሣት አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብናል:: ለመናገር የምንፈልገውን አሳብ ለመስማት እንዲፈልጉ ልናነሣሣቸው ይገባል:: በመሆኑም፣ ገና ከመነሻው የምናቀርብላቸውን መልእክት መስማት ለምን እንደሚጠቅማቸው ማሳየት አለብን:: አንድ ተናጋሪ ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለራሱ ማቅረብ አለበት- «በሕዝቡ መካከል ብሆን ምን ይሰማኝ ነበር? ለመስማት እፈልግ ይሆን? መልእክቱን ለመስማት ፍላጎት ይኖረኝ ይሆን? ለማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ግልጽ ይሆንላቸዋል?» ራስህ የምታቀርበው መልእክት ደስ የማያሰኝህ ከመሰለህ፣ አድማጮችህም በምታቀርበው መልእክት ደስተኞች ላይሆኑ ይችላሉ::

ሐ. መረጃውን በሚሰጥበት ጊዜ፣ ተናጋሪው ሕዝቡ ከሚያውቁት በመጀመር ወደ አዳዲስ ነገሮች ሊወስዳቸው ይገባል:: የማያውቁትን ለማብራራት ከሚያውቁት መጀመር አለበት:: ኢየሱስ ታላቅ ተናጋሪ ነበር:: ብዙውን ጊዜ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ለማስተማር ሰዎች ከሚያውቋቸው ነገሮች ምሳሌዎችን ይጠቀም ነበር:: በአመዛኙ ሰዎች ማብራሪያ ወይም የቀረበው አሳብ እንዴት በሕይወት ውስጥ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚያሳይ ምሳሌ ካልተሰጣቸው፣ ሌጣ አሳቦችን ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ:: በምንሰበክብት ጊዜ ተግባራችን መረጃ መስጠት ብቻ አይደለም:: ነገር ግን መንፈሳዊ እውነቶች እንዴት ከግል ሕይወታቸው ጋር እንደሚዛመዱና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እንዴት መለወጥ እንዳለባቸው ለማስረዳት እንፈልጋለን:: ሰዎች በአብዛኛው የአንድን ነገር እውነተኛነት የሚፈርዱት ከራሳቸው ልምድ በመነሣት ነው:: አንድ ነገር በምንናገርበት ጊዜ፣ «ይህ ለእኔ እውነት የሚሆነው እንዴት ነው? ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር አይቼ አውቃለሁ?» ብለው ይጠይቃሉ:: ስለሆነም፣ ተናጋሪው ሰዎ



ቹ ከተስማሙዱት ነገር ጋር በሚቀራረብ መንገድ እውነቶችን ያቀርብና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንዴት መለወጥ እንዳለባቸው ያሳያቸዋል::

መ. ንግግርህን ግልጽና ቀላል አድርግ:: ብዙ ጊዜ ተናጋሪ ዎች ከሚከተሉት ሁለት ችግሮች በአንዱ ይጠመዳሉ:-

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ሕዝቡ እንዲያስታውስ የሚፈልጉት ግልጽ አሳብ የላቸውም:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ቤታቸው ውስጥ ከመጣ እንግዳ ጋር እንደሚያወሩ ሁሉ፣ ከአንዱ ጉዳይ ወደ ሌላው እየዘለሉ ያለ ምንም የአሳብ ቅንጅት እንዳሻቸው ያወራሉ:: መሪዎች እንዲህ ዓይነት ንግግር በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ:: ነገር ግን ለማስተላለፍ የሚፈልጉት አሳብ ዋና ዋና ነጥቦች ግልጽ ካልሆኑ፣ ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን ከወጡ በኋላ የተላለፈው መልእክት ምን እንደ ነበረ ሊያስታውሱ አይችሉም:: ዋናው ነገር መናገራችን ሳይሆን፣ መልእክት ማስተ ላለፋችንና የሰዎች ሕይወት መለወጡ ነው::

<u>ሁለተኛ</u>፣ አንዳንድ ተናጋሪዎች ደግሞ በጣም ብዙ መረጃ ይሰጣሉ:: ከመረጃው ብዛት የተነሣ ሕዝቡ ጠቃሚዎቹን ነገሮች ለመለየት ይቸገራል:: ተናጋሪው ከሦስት እስከ አምስት ላሉት ዐበይት ነጥቦች አጽንኦት መስጠት አለበት:: ነጥቦቹ እጅግ ከበዙ፣ ሕዝቡ ለማስተላለፍ የፈለግከውን አሳብ ሊዘነጉ ይችላሉ:: ሁሉንም ነገር ከዘነጋህ ደግሞ፣ መናገሩ ዋጋ የለውም::

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቅርብ ጊዜ ከሰማሃቸው ስብከቶች ውስጥ እነዚህን ሁለት ስሕተቶች የሚያሳዩትን ምሳሌዎች ግለጽ:: ለ) አንተ ብትሆን ኖሮ በተሻለ ሁኔታ መልእክትህን ለማስተላለፍና ሰዎች አኗኗራቸውን እንዲለውጡ ለማገዝ ስብከቱን እንዴት ታቀናብር ነበር? |

ሠ. ለማስተላለፍ የምትፈልጋቸውን ዐበይት ነጥቦች ከዘ ረዘርክ በኋላ፣ ሰዎች እነዚህን አሳቦች እንዲያምኑ፣ እንዲያስታውሱና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል ጠንክር አድርገህ አዘጋጃቸው:: ለእያንዳንዱ ነጥብ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ነገሮች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ማድረጉ ጠቃሚ ነው:

1) ተናጋሪው የመረጃውን እውነተኛነት በመግለጽ ሰዎች ማመን እንዳለባቸው ማሳየት ይኖርበታል:: ይህንን ለማድረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን፣ የራሱን ተሞክሮዎች፣ ወዘተ. . . ሊያቀርብ ይችላል:: ሰዎች፣ «ይህ እውነት እንደ ሆነ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?» የሚል ጥያቄ ሊፈጠርባቸው ስለሚችል፣ ማሳየት ይኖርብሃል:: ነገር ግን እጅግ ብዙ መረጃዎች ማቅረብ የለብህም:: ዓላማህ ሰዎች ትምህርትህን እንዲቀበሉ ማገዝ እንጂ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉትን መረጃዎች ሁሉ መዘርዘር አይደለም:: አንዳንድ ሰባኪዎች ስለሚያስተምሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በጣም ብዙ መረጃዎችን ይሰጣሉ:: ነገር ግን እነዚህ መረጃዎች ከመልእክታቸው ጋር ስለማይሄዱ እርባና ቢስ ይሆናሉ::

2) ዋና ዋና ነጥቦች ሁሉም ሰው ዋናነታቸውን አውቆ ትኩረት ሊሰጥ በሚችልበት መንገድ መጀመር አለባቸው::

3) ጠቃሚ ጽንሰ-ሐሳቦችን በተመጠነና ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራራት:: የምትናገረው ስለ ጽድቅ ከሆነ፣ ምን ለማለት እንደ ፈለግክ በጥንቃቄ አብራራ:: ሰዎች በቀላሉ አንድን ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ሊረዱ ይችላሉ:: የአድማጩ ግንዛቤ ከተናጋሪው ያፈነገጠ ከሆነ፣ ተናጋሪው መልእክቱን በግልጽ አላቀረበም ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት በጥንቃቄ ማብራራት አለበት::

4) ለማስተማር የምትፈልገውን ነገር አድማጩ ከሚያውቀው ነገር ጋር አነጻጽር:: ሕዝቡ የምኩራብን ምንነት ላያውቅ ቢችልም፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አነጻጽረህ ብትገልጸውና ልዩነቱን ብታሳየው፣ የተሻለ ግንዛቤ ሊጨብጥ ይችላል:: ሕዝቡ እውነቱን ለመረዳት የሚያግዙትን የሚመስል ነገር ካላወቀ፣ ተናጋሪው የሚያስተላልፈውን መልእክት ላይገነዘብ ይችላል::

5) እውነቱ እንዴት በሕይወት ውስጥ እውን እንደሚሆን አብራራ:: እውነቱ እንዴት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ:: አንድን እውነት አድበስብስን ካለፍን፣ ሰዎች



እንዴት በሕይወታቸው ውስጥ ተግባራዊ እንደሚሆን ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ:: ቅዱስ ስለ መሆን እየተናገሩ ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በምሳሌዎች ተጠቅመው ለአድማጮቻቸው የማያብራሩ ብዙ ሰባኪዎች አሉ:: «መቼም ምን ለማለት እንደ ፈልግኩ ይገባችኋል» ይላሉ:: ነገር ግን ሕዝቡ የሚናገሩት ነገር እንዴት ከግል ሕይወቱ ጋር እንደሚዛመድ አያውቅም:: ስለሆነም፣ ተናጋሪው የሚናገረው ነገር የሰዎችን ሕይወት እንዴት በተለያዩ መንገዶች ሊነካ እንደሚችል በምሳሌዎች ማሳየት አለበት:: (ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ሰዎች ሁሉ ባልንጀሮቻችን መሆናቸውን በመግለጽ ለሁሉም ፍቅርን ማሳየት እንዳለብን አስተምሮናል:: ይህንን ልናደርግ የምንችለው ደግሞ ችግር ሲገጥማቸው ቡና በመውሰድ፣ ወላጆች ወደ ሆስፒታል በሚሄዱበት ጊዜ ልጆቻቸውን በመንከባከብ ወይም የእድሩ አባል ባንሆንም እንኳን፣ ለቅሶ ቤት ምግብ በመውሰድ ሊሆን ይችላል::)

6) እውነቱ አንተን ወይም ሌላ ሰው እንዴት እንደ ረዳ ለማሳየት ታሪኮችን ወይም የሌሎች ሰዎችን ምስክርነቶች ተናገር:: ታሪኮችን መናገር እውነትን ለማብራራት ከሚያስችሉ እጅግ ጠቃሚ መንገዶች አንዱ ነው:: ይህ የሚሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ ሰዎች ታሪክ በሚሰሙት ጊዜ በምናብ ራሳቸውን በታሪኩ ውስጥ በመመልከት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ ምን ዓይነት እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ ያስባሉ:: <u>ሁለተኛ</u>፣ ሰዎች ታሪክ በሚሰሙበት ጊዜ ያስታውሱታል:: ሰዎች ታሪኮችን ያስታውሳሉ፣ እውነቶችን/መረጃዎችን ግን ይዘነጋሉ:: ስለሆነም፣ ታሪክ በምንናገርበት ጊዜ ለማካፈል የምንሞክራቸውን ዐበይት ነጥቦች በቀላሉ ሊያስታውሱ ይችላሉ::

ረ. ሕዝቡን ለለውጥ ለማነሣሣት ሞክር:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ ሰዎች እንዲለወጡና ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስሉ እንፈልጋለን:: በገንዘብ አጠቃቀማቸው እንዲለወጡ እንሻለን:: በዓለም ውስጥ በሚኖሩበት ሁኔታ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያከናውኗቸው ነገሮች እንዲለወጡ እንፈልጋለን:: ሰዎች መረጃ እንዲያገኙ ብቻ በማሰብ

የምናስተላልፋቸው መልእክቶች ብዙ አይደሉም። ሰዎች የተለየ ሕይወት ለመኖር የሚችሉት ለመወሰጥ ሲፈልጉ ብቻ ነው። ስለሆነም፣ ለምን መለወጥ እንደሚያስፈልጋቸው ማሳየት አለብን። እንዲሁም ደግሞ ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በማሰብ ከውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ማስቻል ይኖርብናል። ብዙ ጊዜ መሪዎች መልእክታቸውን የሰሙ ሰዎች የተግባር ለውጥ ለማድረግ ውሳኔ እንዲያደርጉ ጥሪ እናደርግላቸውም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሕዝቡ ሁሉ ለመለወጥ ቃል ኪዳን የሚገባበትን ሁኔታ እንመለከታለን። (ለምሳሌ፣ ነህ. 9-10)። ዛሬ፣ እብዛኛው ስብከት የሚጠናቀቀው ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ጥሪ በማድረግ ነው። ይህ መልካም ቢሆንም፣ መጨመር ያሰብን ነገር አለ። ይኸውም ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ከሰሙ በኋላ አኗኗራቸውን መቀየር እንዳለባቸው ማደፋፈር ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ አብዛኞቹ ስብከቶች የሚጠናቀቁት አማኞች በተወሰኑ መንገዶች አኗኗራቸውን እንዲቀይሩ በመጠየቅ ነውን? ከሆነ፣ በዚህ ባለፈው ወር ውስጥ ሰባኪዎች ሰዎች እንዲለወጡ የጠየቁባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር። ለ) ሰዎች ክርስቶስን በተሻለ ሁኔታ ለመከተል በምን በምን መንገዶች መለወጥ እንዳለባቸው የሚጠይቁ አሳቦች ቢካተቱ፣ ትምህርቱ እንዴት በበለጠ የሚሻሻል ይመስልሃል?

(ማስታወሻ፡- እግዚአብሔር በመደበኛነት ቃሉን ለሕዝቡ እንድታስተላልፍ እየጠየቀህ ከሆነ፣ በሚገባ ለመስበክ እንድትችል የሚያግዙህን ሌሎች መጻሕፍት ማንበብ አለብህ። በሕዝብ ፊት ውጤታማ መልእክት አስተላላፊ እንድትሆን የሚከተሉት መጻሕፍት ምን ምን ምክሮችን እንደሚሰጡ ለመረዳት ሞክር፡- *ገላጭ ስብከት፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለመረዳት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የስባኪው ምሳሌዎች፣* ወዘተ. . . )

4. ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር የአሳብ ልውውጥ ማድረግ፡-

እግዚአብሔር እኛ መሪዎች ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ እንድንረዳቸውና በማኅበረሰባችን ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድናስፋፋ ይፈልጋል። መሪዎች ምእመናን ሁሉ በንቃት በመሥራት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን



ራእይ እንዲፈጽሙ ማበረታታት አለባቸው። ሰዎች አብረው እንዲሠሩ ለማገዝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ጋር ቀጣይነት ያለው የመልእክት ልውውጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምእመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ ካልተረዱ፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ተሳታፊዎች ሊሆኑ አይችሉም። እንዲሁም ደግሞ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰጧቸውን ውሳኔዎች ካላወቁ፣ የመሪዎቹን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ሰውጥ ሊያመጡ አይችሉም። ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ አንድ ጉዳይ ውሳኔዎችን ሲሰጡ ይውላሉ። (ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያዊ ወንጌላዊ መላክ አለብን ወይስ የለብንም?) ነገር ግን ዕቅዱን ለምእመናን በግልጽ ስለማይናገሩ፣ ምእመናን የሽማግሌዎቹን ዕቅዶች ከሙሉ ልባቸው አይደግፉም። ይህም ለዕቅዱ አለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። መሪዎች ዕቅድ ለማውጣትና ውሳኔ ለመስጠት ያጠፉት ጊዜ ከንቱ ሆኖ ይቀራል። በመሪዎችና ምእመናን መካከል (በተለይ በገንዘብ ጉዳይ) መተማመን ስለሌለ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውጤታማ ለመሆን ይቸገራሉ። ለዚህም ምክንያቱ ምእመናን አስራታቸውና መባቸው እንዴት ከጥቅም ላይ እንደ ዋለ እስማወቃቸው ነው። ምእመናን በሽማግሌዎች ሊተማመኑ የሚችሉት የገንዘብ አጠቃቀሙን በተመስከተ ተገቢው ሪፖርት ከመሪዎቹ ሊሰጣቸው ብቻ ነው። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ጋር በመተባበር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን አገልግሎቶች እንዲያካሂዱና በመሪዎችና በምእመናን መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር የአደባባይ ተግባቦት ክህሎት ወሳኝ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ጋር ክህሎት ያለው የመልእክት ልውውጥ ሊያደርጉ የሚገባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ሀ. ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን ራእይና ዕቅዶች እንዲረዱ ማገዝ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ራእይ የማውጣትና ራእዩ ተግባራዊ የሚሆንባቸውን ዕቅዶች የመወጠን

ኃላፊነት እንዳለባቸው ቀደም ሲል ተገልጾአል። ምእመናንን እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ግብ የማድረሱ ኃላፊነት የመሪዎች ነው።

መሪዎች ውሳኔዎችን በማሳለፍ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማዘዝ የለባቸውም። ምእመናን ራእዩንና ዕቅዶቹን ለማወቅ የእግዚአብሔርን ምክር የመፈለጉ ሂደት አካል ካልሆኑ፣ እምብዛም ራሳቸውን፣ ገንዘባቸውን ወይም ጊዜያቸውን በመስጠት ለዕቅዶቹ መሳካት የበኩላቸውን ሚና አይጫወቱም። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራእይና ዕቅዶች በሚያወጡበት ጊዜ ከምእመናን ጋር አብረው መሥራት ይኖርባቸዋል። መሪዎች ራእዩን በሚመሠርቱበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይኖርባቸዋል። የቤተ ክርሰቲያን (መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን እንዴት ራእዮችንና ዕቅዶችን እንደሚያወጡ ለመረዳት ትምህርት 8 እና 9ን ተመልከት።)

1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምእመናን ከመናገራቸው በፊት፣ ከምእመናን ጋር ራእዩን ለማውጣት ሊወስዷቸው ስለሚገቧቸው ነገሮች መወያየት አለባቸው። መሪዎቹ ስለ ሂደቱ እርግጠኞች ካልሆኑ፣ ምእመናን ከእነርሱ ጋር በቅርብ ለመሥራት ዝግጁ ላይሆኑ ይችላሉ። መሪዎች ምእመናንን ከማነጋገራቸው በፊት ሊሰጥ የሚገባው ትምህርት አለ? በኋላ ከምእመናን ጋር ይሠሩ ዘንድ ውይይቶችን በመምራቱ በኩል ሥልጠና ሊሰጣቸው የሚገባቸው የቡድን መሪዎች አሉ? ሰዎች በራእዩ ላይ ለመሥራት ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማገዝ ምን ቢደረግ መልካም ነው? መሪ ዎች በራእዩና ዕቅዶቹ ላይ ከምእመናን ጋር ከመሥራታቸው በፊት ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ምላሽ መገኘት አለበት።

2) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ራእይ በሚወስኑበት ሂደት ውስጥ ምእመናንን ማሳተፍ አለባቸው። መሪ ዎች «ዛሬ እግዚአብሔር ለቤተ ክርሰቲያናችን የሰጠውን ራእይ ለመወሰን ስብሰባ እናካሂዳለን፣» የሚል አዋጅ ከሚናገሩ፣ ለብዙ ሳምንታት የታቀደው ነገር ምን እንደ ሆነ ማብራራት



ይኖርባቸዋል። ሰዎች አንድን አዲስ አሳብ ለመቀበል ብዙ ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ደጋግሞ መግለጹ አስፈላጊ ነው።

አሳቡን ለሕዝብ የሚገልጹ ሰዎችም በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው። አግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል ሊያደርግ የፈለገውን ነገር መረዳቱ ለምን እንደሚያስፈልግና መሪዎች ከምእመናን ጋር ሆነው በመሥራት ራእዩን ለመወሰን የሚወስዷቸውን ደረጃዎች በግልጽ የሚያውቁ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም ማስታወቂያውን የሚናገረው ግለሰብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመሥራት እንዲነሣሡ የማድረግ ብቃት ያለውም ሊሆን ይገባል። ምእመናን ይህ አግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገው ነገር ነው የሚል እምነት ከሌላቸውና በዚህም ምክንያት ለእግዚአብሔርና ለሥራው ራሳቸውን አሳልፈው የማይሰጡ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ራእይ ለመወሰን የሚወሰደው ሂደት እምብዛም ፍሬያማ ሊሆን አይችልም።

ክህሎት ባለው የመግባባት ስልት በመጠቀም እግዚአብሔር ቀደም ሲል እንዴት እንደ ሠራና አሁንም ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን በመጠቀም ምን ሊሠራ እንደሚፈልግ ማብራራት አለበት። ነገር ግን መሪዎች ምእመናን አንዳች ነገር እንዲያደርጉ ጫና ሊያሳድሩባቸው አይገባም። መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በማነሣሣት ሥራውን ለማከናወን እንዲፈቅዱ ያደርጋቸው ዘንድ በእምነት መጠበቅ አለባቸው። ምእመናን በውሳኔው ላይ አንድ ዓይነት አቋም ከሌላቸው፣ በአመዛኙ ሰይጣን ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ክፍፍልን ለመፍጠር ይጣጣራል፣ ወይም ደግሞ ሕዝቡ ራእዩን ለመፈጸም አይነሣሡም።

3) ምእመናን ከብዛታቸው የተነሣ ጥሩ ዕቅዶችን ለማውጣት ይቸገራሉ። በመሆኑም፣ (ምናልባት የሰፈር የጸሎት ቡድኖቻቸውን በመጠቀም) እባላትን በአነስተኛ ቡድኖች መከፋፈሉ ጠቃሚ ነው። ሁሉም ምእመናን አንድ ዓይነት ጥያቄዎች ማጥናታቸውንና መመለሳቸውን ለማረጋገጥ መሪዎች ለእያንዳንዱ ቡድን ጥያቄ ዎችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ለእያንዳንዱ ቡድን የውይይት መሪዎች መመደብ አለባቸው።

እያንዳንዱ ቡድን የሚወያይበት ጊዜና የመወያያ ጥያቄዎች ሊዘጋጁለትና ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያምኗቸውን ነገሮች ለተ ቀሩት ምእመናን የሚያስተላልፉበት መንገድ ሊመቻች ይገባል።

4) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱ ቡድን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥና እማካኝነት ሊያደርግ ይፈልጋል ብሎ የሚያምንባቸውን ነገሮች በማንሣት ከተቀሩት ምእመናን ጋር መነጋገር አለባቸው። ከዚያም ምእመናን ከስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው።

5) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን ተወያይተው ያጸደቁትን አሳብ በአስተዋጽኦ መልክ ያስፍራሉ። በመቀጠልም ግልጽ አሳቦችን በመጻፍ ዕቅዶችን ማውጣት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ዕቅዶች በመሪዎች ከጸደቁ በኋላ ለምእመናን ቀርበው ይጸድቃሉ።

6) በተቻለ ፍጥነት ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ መጀመር አለበት። ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ከስምምነት ላይ ከደረሱ፣ ለመሥራት ዝግጁዎች ናቸው። ነገር ግን ምእመናን ከስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ሥራው ሳይጀመር ብዙ ጊዜ ቢቆይ፣ የምእመናን ፍላጎት ስለሚቀዘቅዝ፣ ፈቃደኛ ሠራተኞችን ማግኘቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

7) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን አከናውናለሁ ያለችውን ዕቅድ በተመለከተ የተወሰዱትን እርምጃዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምእመናን ማሳወቅ አለባቸው። የእነዚህ ሪፖርቶች ዓላማ የሚከተሉትን የሚያካትት ነው፡- ሀ) ራእዩንና ዕቅዶቹን በምእመናኑ አእምሮ ውስጥ በማቆየት በሌሎች አነስተኛ ጉዳዮች ተ ማርከው እንዳይወሰዱ ለማድረግ፣ ለ) ለምእመናን እግዚአብሔር በመካከላቸው ምን እያደረገ እንዳለ ለማሳየት፣ እና ሐ) ምእመናን ራእዩና ዕቅዶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማገዝ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን የሚሰጡበትን መንገድ ለማሳየት። «ከዓይን የራቀ ከልብ ይርቃል» የሚል አባባል አለ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመደበኛነት ለምእመናን ሪፖርት በማቅረብ ራእዩ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ሕያው ሆኖ እንዲቆይ ማስቻል አለባቸው። ምናልባትም



ራእዩን ጽፎ በቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ መስቀል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህም ጥቅሶችን እንደምንሰቅል ማለት ነው። የምናከናውናቸው የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ካሉ (ለምሳሌ፣ ተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ግንባታ) የሚታዩትን ለውጦች የሚያመለክቱ ሠንጠረዦችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል።

8) ከፍተኛ ስኬት ላይ በሚደረስበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን በአንድነት የደስታ በዓል ማድረግ አለባት። እግዚአብሔር በመካከላችን እየሠራ ነው። እርሱ ራእዩን ለመፈጸም እየተ ጠቀመብን ነው። እርሱ አንድ ነገር በሚያደርግበት ጊዜ አብረን ደስ መሰኘት አለብን። አንድ ሰው በሚያምንበት ጊዜ የሰማይ መላእክት ደስ የሚሰኙ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በመካከላችን አንድን ነገር በሚያደርግበት ጊዜ እኛስ ደስ ሊለን አይገባም ትላላችሁ?

> 25ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ማኅበረ ምእመናን በአንድነት ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ጉዳዮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ሽማግሌዎች ለእነዚህ አስፈላጊ ጉዳዮች የምእመናንን አስተዋጽኦ ሊያገኙ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) ምእመናን በእነዚህ አስፈላጊ ውሳኔዎች ላይ በበለጠ ተ ሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚያግዙ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው ብለህ ታስባለህ?

ለ. ለምእመናን በየጊዜው ሪፖርት ማቅረብ፡- ምእመናን የእግዚአብሔርን ራእይ እውን በማድረጉ ሂደት ደስ ሊሰኙ የሚችሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ለእነርሱና በእነርሱ አማካኝነት ምን እያከናወነ እንደ ሆነ የሚያመለክቱ ሪ ፖርቶች የሚያቀርቡላቸው ከሆነ ብቻ ነው። ብዙውን ጊዜ መረጃው በማይተላለፍበት ጊዜ፣ ሰይጣን ይህንን ሁኔታ በመጠቀም ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንዲጠራጠሩ ያደርጋል። ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች በተ መለከተ በተደጋጋሚ ለምእመናን መረጃ ሊሰጡ ይገባል፡-

1) በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ስለ ተሰጡት ዋና ዋና ውሳኔዎች ሪፖርት ማቅረብ። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን እንደ አንድ ቤተሰብ ተሳስረው እንዲኖሩ ለማስቻል ሽማግሌዎች የሚወስኑባቸው ጉዳዮች ሊያስደስቷቸው ይገባል። በመሆኑም፣

በአማኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ለምእመናን ማካፈሉ ተገቢ ነው። ይህ ሽማግሌዎች ከምእመናን ነገሮችን እየደበቁ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ ያስወግዳል። ሰይጣን ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር እንዳይሠሩ ለማድረግ ጥርጣሬን በመሣሪያነት ይጠቀማል።

2) የሥራ ሂደቶችን የሚመለከቱ ሪፖርቶች። እግዚአብሔር በመካከላችን አንድ ነገር እያደረገ ከሆነ፣ ምእመናን ስለዚህ ጉዳይ መስማት አለባቸው። በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር አንድን ሰው በሚያስገርም መንገድ ወደ ክርስቶስ መርቶታል? ይህንን በሚሰሙበት ጊዜ፣ ምእመናን እምነታቸውን ለሌሎች ለማካፈል ይነቃቃሉ። እግዚአብሔር በልጆች ሕይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የሰንበት ትምህርት ቤቱን አስተማሪ እየተ ጠቀመበት ነውን? ይህንን መናገሩ ሰዎች ልጆችን ወደ ሰንበት ትምህርት ለምን መላክ እንዳለባቸውና ጊዜያቸውንና እገዛቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው ያሳያቸዋል። ሽማግሌዎች ስላቀዷቸው ነገሮች፣ እንዲሁም ከዕቅዶቻቸው ምን ያህሉቹ እንደ ተከናወኑና ምን ያህሉቹ እንደሚቀሩ በማነጻጸር ለምእመናን ሪፖርት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ምእመናን ላጋጠሙት ችግሮች ሊጸልዩ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በጥሩ ሁኔታ አለመካሄዳቸውን በመመልከት ምእመናን ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ይሰጣሉ።

3) የገንዘብ ሪፖርቶች። ሰይጣን በተለይ በገንዘብ አካባቢ አለመተማመንን በመፍጠር የሚፈነጭ ይመስላል። ምእመናን አስራታቸውና መባቸው እንዴት ከጥቅም ላይ እየዋለ እንደ ሆነ በማያውቁበት ጊዜ፣ ገንዘቡ አላግባብ እየባከነ ነው የሚል ግምት ሊያድርባቸውና መስጠታቸውን ሊያቆሙ ይችላሉ። ይህንን ችግር ለማስወገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በየጊዜው ለምእመናን ሪ ፖርት መስጠት አለባቸው።

26ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚሰጡትን የሪፖርት ዓይነቶች ዘርዝር። ለ) ሪፖርቶቹ የሚሰጡት በየስንት ጊዜው ነው? ሐ) ሽማግሌዎች እነዚህን ሪፖርቶች የሚሰጡት ለምን ዓላማዎች ነው? መ)



የሚሰጡት ሪፖርቶች ዓላማውን ያሳካሉ? ለምን? ሐ) ሰዎች እነዚህን ሪ ፖርቶች በደስታ ይከታተላሉ? ለምን? ሠ) እነዚህ ሪፖርቶች የሚሰጡባቸው ጊዜያት ለምእመናን የበለጠ አስደሳችና ጠቃሚ እንዲሆኑ ምን ቢደረግ ጥሩ ይሆናል ትላለህ?

እነዚህ ሪፖርት የሚሰጥባቸው ጊዜያት ለምእመናን ጠቃሚ ዎች ይሆኑ ዘንድ ሪፖርቶቹን በክህሎት መስጠቱ ጠቃሚ ይሆናል። የሪፖርቱ አሰጣጥ የሰዎችን ትኩረት የማይስብ ከሆነ፣ የመሪዎቹም የምእመናንም ጊዜ እየባከነ ነው ማለት ነው። ሪ ፖርቶች አስፈላጊዎች ናቸው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር ምእመናን በሰጡት ገንዘብ አማካኝነት ያከናወናቸውን ተግባራት የምንነግራቸው። ነገር ግን ሪፖርቶቹ አሰልቺ ከሆኑ፣ ምእመናን አይሰሟቸውም። ይህም በአመራራችን ውስጥ እንዲገኝ የምንፈልገውን መተማመን እንዳናገኝ ያደርገናል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምእመናን ሪፖርት በሚያቀርቡበት ጊዜ ሊያስታውሷቸው የሚገቧቸው አንዳንድ ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል:-

1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሪፖርቱን ዓላማና ሪፖርቱ ለማን መቅረብ እንዳለበት በግልጽ መረዳት አለባቸው። ሀ) ሪፖርቱ ሰዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎቶች በሚገባ እንዲገነዘቡ የሚያስችል ታሪካዊ ሰነድ ነው? እንዲህ ዓይነት መረጃዎች በዝርዝር መቅረብ አለባቸው። ለ) ሪፖርቱ መሪዎች ውሳኔ እንዲሰጡ የሚያግዝ ነውን? እንደዚህ ከሆነ፣ ሪፖርቱ መሰጠት ያለበት ጉዳዮቹን ለሚያውቁ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ብቻ ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራ ስለሚበዛባቸው፣ ሁሉንም ነገር ለማንበብ የሚበቃ ጊዜ የላቸውም። ነገር ግን ጥሩ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ማግኘት አለባቸው። ሐ) መረጃው የአገልግሎት ዘርፍ ሪፖርት ነውን? የአገልግሎት ዘርፉ ምን ለማከናወን እንደ ፈለገ፣ የትኞቹን በተሳካ ሁኔታ እንዳከናወነና የትኞቹ እንዳልተከናወኑ፣ በምን ምክንያት ሊከናወኑ እንዳልቻሉ ሪፖርት ማድረግ አለበት። ወደፊት ምን ለማድረግ እንደ ተፈለገም መገለጽ አለበት። ይህ ሽማግሌዎች

ሁሉንም የአገልግሎት ዘርፎች እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ይህ መሪዎች የአገልግሎት መሪዎችን ለሥራቸው ተጠያቂ የሚያደርጉበትም መንገድ ነው። መ) ሪፖርቱ ለምእመናን የሚቀርብ ነው? እንዲህ ከሆነ፣ ዝርዝር ጉዳዮችን ማጠቃለል የለበትም። እግዚአብሔር ያከናወናቸውንና ወደ ፊትም ያከናውናል ብለው ሽማግሌዎች የሚያምኑባቸውን ዐበይት ነገሮች ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያቀርብ መሆን አለበት።

ምንም እንኳ ለማየት ለሚፈልጉ ሰዎች ሪፖርቶቹ ክፍት መሆን ቢኖርባቸውም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምእመናን አስደሳች ሪፖርቶችን ለመስጠት ክህሎት ባለው መንገድ ማዘጋጀት አለባቸው። ይህ ምእመናን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያከናውነው ሥራ አካል ነን ብለው እንዲያስቡ ያስችላቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሪፖርት በመጠቀም በሆነ መንገድ እንዲያገለግሉ ወይም ገንዘባቸውን እንዲሰጡ ሊያበረታታቸው ይችላል።

2) ለምእመናን ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ብቻ መናገር። ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ከቀረቡላቸው፣ ሰዎች ሊሰላቹና ጠቃሚዎቹን ነገሮች ላይሰሙ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ለአባላት በሚሰጥ ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ሽማግሌዎች ስንት ጊዜ እንደ ጸሙ መናገር አያስፈልጋቸውም።

ሁለት ዓይነት ሪፖርቶችን ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው። አንደኛ፣ ለመሪዎች ሁሉ የሚቀርብና ለማንበብ ለሚፈልጉ ምእመናን ሊሰጥ የሚችል ሙሉ ሪፖርት። ለምእመናን ይህ ሪፖርት በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ውስጥ እንዳለና ፍላጎቱ ካላቸው መጥተው ሊያነብቡት እንደሚችሉ መናገሩ ጠቃሚ ነው። ይህ ሪፖርት ከተደበቀባቸው፣ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ሥራ እንዳልሠሩ ወይም የሆነ «ለመደበቅ» የሚፈልጉት ነገር እንዳለ ሊያስቡ ይችላሉ። ይህ ደግሞ አለመተማመንን ሊያስከትልና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተገቢውን አመራር የሚሰጡበትን መንገድ ሊገድብባቸው ይችላል።



ሁለተኛ፣ በዓመቱ ውስጥ የተከናወኑትን ዐበይት ጉዳዮች ብቻ የሚዘረዝር ጠቅለል ያለ ሪፖርት። ለማኅበረ ምእመናን መቅረብ ያለበት ይሄኛው ሪፖርት መሆን አለበት። ሪፖርቱን የሚያቀርበው የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ «ይህ በዓመቱ ውስጥ ሽማግሌዎች ያሳለፉአቸውን ዋና ዋና ውሳኔዎች የሚያሳይ ነው። ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ ግን ወደ ቢሮ ብቅ ብላችሁ ሙሉውን መረጃ ልታነብቡ ትችላላችሁ፣» ማለት አለበት። ይህ ከምእመናን ለመደበቅ የሚሞከር መረጃ አለመኖሩን ያሳያል። ይህ በተለይ ስገንዘብ መረጃ አስፈላጊ ነው። ሰዎች ገንዘባቸው እንዴት ከጥቅም ላይ እየዋለ እንዳለ ካላወቁ፣ ለመስጠት ፈቃደኞች አይሆኑም።

3) የተከናወኑትን ነገሮች ሁሉ ከመዘርዘር ይልቅ መሪዎች ለመድረስ የፈለጉአቸውን ግቦች፣ ከእነዚህ ግቦች የትኞቹ እንደ ተከናወኑና የትኞቹ እንዳልተከናወኑ፣ በምን ምክንያት እንዳልተከናወኑ ቢገልጹ መልካም ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምእመናን መሪዎች ምን ዓይነት ነገሮችን ለማከናወን እንደ ፈለጉ ለመረዳት፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በሚከናወነው ሥራና እድገት ደስ ለመሰኘትና አንዳንድ ነገሮች ለምን እንደማይከናወኑ ለመገንዘብ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ነገሮች የማይከናወኑት ምእመናን ባለመሳተፋቸው ወይም ገንዘብ ባለመስጠታቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ የቀረበውን ሪፖርት በመጠቀም ምእመናንን ለተሳትፎ ሊያነሣሣቸው ይችላል።

4) የገንዘብ ሪፖርት በሚቀርብበት ጊዜ ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ይልቅ ሕዝቡ አጠቃላዩን ሁኔታ በሚገነዘብበት መንገድ ማቅረቡ የበለጠ ጠቃሚ ነው። ባለፈው ዓመት መሪዎች ምን ያህል ገንዘብ እናገኛለን ብለው ተስፋ አድርገው ነበር? ምእመናን የሰጡት ምን ያህል ነበር? ለቤተ ክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ዘርፎች የተሰጠው ስንት ብር ነበር? በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሳይከናወኑ የቀሩት ሥራዎች የትኞቹ ነበሩ? በቀጣዩ ዓመት ሽማግሌዎች ለማከናወን የፈለጉት ምንድን ነው? ስንት ብር ያስፈልጋቸዋል?

5) አንዳንድ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ግብን ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ፣ ምእመናን ሁለት ወንጌላውያን ለመላክ ወይም ቤተ ክርስቲያናቸውን ቆርቆሮ ለማልበስ ከፈለጉ፣ አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ሠንጠረዥ መስቀሉ ጠቃሚ ነው:: ሠንጠረዡ ሁለት ወንጌላውያንን ለመላክ ስንት ብር እንደሚያስፈልግ ያሳያል:: ከዚያም በየሳምንቱ ሽማግሌዎች ስንት ብር እንደ ተገኘና ምን ያህል ወደተፈለገው ግብ እየቀረቡ እንዳሉ የሚያሳይ ምልክት በሠንጠረዡ ላይ ያደርጋሉ:: እንዲህ ዓይነት ተጨባጭ ነገር ማየቱ ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልጉትን ነገር ለማሳካት ምን ያህል እየሠራ እንደ ሆነ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል::

6) በአብዛኛው ቀጣይነት ስላላቸው ነገሮች በየጊዜው (በየሦስት ወሩ ወይም በየስድስት ወሩ) ሪፖርት ማድረጉ አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ ያህል፣ ምእመናን የሚሰጡት ገንዘብ ቢቀንስና የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ደመወዝ መክፈል አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ ቢፈጠር፣ ይህንኑ መረጃ ለምእመናን መግለጹ አስፈላጊ ነው:: ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልጉ ዐበይት ነገሮች ለምእመናን መግለጹ ምእመናን መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ያግዛል:: ነገር ግን ይህ በማስተዋል መከናወን አለበት:: መሪዎች በተደጋጋሚ ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆነ፣ ምእመናን ገንዘብ የመስብሰብ ፍላጎት አላቸው ወደሚል ድምዳሜ ሊያመሩ ይችላሉ::

> 27ኛ ጥያቄ:- ባለፈው ዓመት የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች ለምእመናን ያቀረቧቸውን ሪፖርቶች አስብ:: ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሪፖርቶቹን ለምእመናን አስደሳችና ጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው?

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናን ተሳትፎ የሚጠይቅ መረጃ ለመስጠት ከፈለጉ፣ በተቻለ መጠን ቀደም ብለው መረጃውን መስጠት ይኖርባቸዋል:: ይህ ምእመናን የጊዜ ሰሌዳቸውን እስተካክለው ለመሳተፍ እንዲችሉ ያግዛቸዋል:: በአብዛኛው ሰዎች በሥራ ቀናት የሚካሄዱትን ስብሰባዎችና የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች የማይሳተፉት ቀደም ብለው ስለማይሰሙ ነው:: ቀደም ሲል የያዟቸው ፕሮግራሞች ስለሚኖሩ፣ ለመምጣት ሳይችሉ ይቀራሉ:: አንድ ጊዜ አንድ ግለሰብ፣ *«የእናንተ ማቀድ አለመቻል በእኔ በኩል ድንገተኛ ሁኔታ ሊፈጥር አይችልም፣»* ብሏል:: ስለሆነም፣ ቀደም ብለን በማቀድ ሰዎች ፕሮግራማቸውን የሚያስተካክሉበትን ሁኔታ ካላመቻቸን፣ ላለመምጣታቸው ጥፋቱ የእኛው ነው ማለት ነው:: ምእመናን የእኛን ዕቅዶች ለማሳካት ብለው ቀደም ሲል የያዟቸውን ፕሮግራሞች ይሰርዛሉ ብለን መጠበቅ የለብንም:: ይህ የአገልጋይ መሪነት መንፈስ አይደለም:: ዕቅዶቻችንን ቀደም ብለን ማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ ስለሚካሄዱት ስብሰባዎች በየጊዜው ለምእመናን መግለጽ አለብን::

መ. ለቤተ ክርስቲያን ምእመናን ስብሰባዎችን በምናዘጋጅበት ጊዜ፣ ከምእመናን የሚጠበቁትን ነገሮች የሚያሳዩ መረጃዎች በሙሉ መስጠት አለባቸው:: በስብሰባው ላይ መገኘት ያለባቸው በስንት ሰዓት ነው? ቦታው የት ይሆናል? ወደ ስብሰባው ይዘው መምጣት ያለባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መሪዎች ምእመናን ቀደም ብለው እንዲዘጋጁ ስለማያደርጉ፣ ብዙ ስብሰባዎች ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሥራ ቀን በሚያውጁበት ጊዜ ሕዝቡ የቁፋሮ ወይም የሣር መቁረጫ መሣሪያዎችን ይዘው እንዲመጡ ሳይናገሩ ይቀራሉ:: ሕዝቡ ሥራውን ለማከናወን በሚመጣበት ጊዜ፣ አስፈላጊው መሣሪያ ስለማይኖር፣ ብዙ ሥራ ሳይሠራ ይቀራል:: ይህ ለምእመናን የሚያናድድ ነገር ስለሆነ፣ በቀጣዩ ጊዜ ለሥራ ስንጠራቸው ሳይመጡልን ይችላሉ:: ምእመናንን ለየትኛውም ስብሰባ ከመጥራት አስቀድሞ ሁሉንም ነገር በአግባቡ ማዘጋጀት የመሪዎች ኃላፊነት ነው:: እንዲሁም መሪዎች ምእመናንን ለመቀበልና የተሰያዩ ኃላፊነቶችን ለመስጠት ከሰዓቱ ቀደም ብለው በስፍራው መገኘት አለባቸው:: መሪዎቹ ካረፈዱ፣ ሰዎቹ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ሊሄዱ ይችላሉ:: ከዚያም በኋላ ለእግዚአብሔር የመሥራት ፍላጎታቸው ሊቀንስ ይችላል::

> 28ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች ግልጽ መመሪያ ባለመስጠታቸው የፈለጉት ተግባር አለመከናወኑን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ:: ለ) መሪዎች የቡድን ስብሰባዎችን በጥሩ ሁኔታ አለማዘጋጀታቸው ምእመናንን ያሳዘነበትንና ሥራው በተፈለገው መንገድ እንዳይካሄድ መሰናክል የፈጠረበትን ሁኔታ ግለጽ::